፯ ፤ ተንሥኢ ፡ እግዚኦ ፡ አምላኪየ ፡ ወአድኅንኒ ።
ብሉዩን ፡ ይዘ ፡ ይሄዳል ፤ አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ በሥራ ፡ በመፍረድ ፡ ተነሥተህ ፡ አድነኝ ።

እስመ ፡ አንተ ፡ ቀሠፍኮሙ ፡ ለኵሎሙ እለ ፡ ይፃረሩኒ ፡ በከንቱ ።
ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ እለ ፡ ሳአልን ፡ አጥፍተህ ፡ አድነኸኛልና ፤ ፩ ፡ ላሙ ፡ ፸፬ ፡ ፩ - ፭ ።

አሁንም ፡ እለ ፡ አቤሴሎምን ፡ አጥፍተህ ፡ አድነኝ ።

ስነኒሆሙ ፡ ለጋጥአን ፡ ሰበርከ ።
ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ የሳአልን ፡ ሥልጣን ፡ አጥፍተህ ፡ አድነኸኛልና ፡ አሁንም ፡ የአቤሴሎምን ፡ ሥልጣን ፡ አጥፍተህ ፡ አድነኝ ።

ዘእግዚአብሔር ፡ አድኅኖ ፡ ላዕለ ፡ ሕዝብከ ፡ ወበረከትከ ፡ ዘፍ ፡ ፲፯ ፡ ፩ ፭ ። የእግዚአብሔርነትህ ፡ ትድግና ፡ በረከትህም ፡ ለኔ ፡ ለልጅ ፡ ልጅህ ፡ ይደረግልኛል ፡ ይደረግልኝ ፤ አንድም ፡ (ላዕለ ፡ ሕዝብከ) ፡ ለኔ ፡ ለልጅህ ፡ (ወበረከትከ) ፡ ባርከ ፡ እባርከከ ፡ ወአስተባዝኖ ፡ አስተባዝኅከ ፡ ብለህ ፡ ባርከህ ፡ ለሰጠኸኝ ፡ ለወገኖችህ ፡ ይደረግላቸው ። ዘፍ ፡ ፲ ፭ ፡ ፭ ። ሕዝብ ፡ ብሎ ፡ ልጅ ፡ ይሆናል ፤ ፪ቱ ፡ አንጋድ ፡ ሀለዉ ፡ ውስጥ ፡ ማኅፀንኪ ፡ ወፂ ፡ ሕዝብ ፡ ይወጽኡ ፡ እምከርሥኪ ፡ ዘየዓቢ ፡ ሕዝብ ፡ ይትቀነይ ፡ ለዘይንዕስ ፡ ሕዝብ ፡ እንዲል ፤ ዘፍ ፡ ፳፭ ፡ ፳፫ ። አንድም ፡ (ላዕለ ፡ ሕዝብከ) ፡ ለኔ ፡ ለልጅህ ፤ (ወበረከትከ) ፡ ባርከ ፡ እባርከከ ፡ ወአስተባዝኖ ፡ አስተባዝኅከ ፡ ብለህ ፡ ባርከህ ፡ ለሰጠኸኝ ፡ ለወገኖችህ ፡ ይደረግላቸዋል ፡ ብለህ ፡ ነበር ፡ ቀረን ፡ ይላል ፤ የችኰላ ፡ አኀጋገር ፤ ከዚያ ፡ ሁሉ ፡ አብርሃም ፡ ላምስቱ ፡ ነገሥታት ፡ ሰዶም ፡ ረድቶ ፡ አራቱን ፡ ነገሥተ ፡ ከሎዶጎምርን ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፡ ሲመለስ ፡ ደስ ፡ ቢለው ፡ በመዋዕልየኑ ፡ ትፌኑ ፡ ቃለከ ፡ ወሚመ ፡ ታርእየኒሁ ፡ ኪያሃ ፡ ዕለተ ፡ አው ፡ አልቦ ፡ እንዳለ ፤ ዘፍ ፡ ፲፬ ፡ ፲፫ - ፳ ።

መዝሙር ፡ ፬ ።

፩ ፤ ሶበ ፡ ጸዋዕኩዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰምዐኒ ፡ ጽድቀየ ።
ስለመነናውያን ፡ ተናግሮታል ፡ ከሥሩ ፡ አርእስት ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ ነው ። በማኒ ፡ መነናውያን ፡ ተብለዋል ፤ በሰዶቅ ፡ ሰዱቃውያን ። በሜቦር ፡ ዕብራውያን ። በፋሬስ ፡ ፈሪሳውያን ። በይሁዳ ፡ አይሁድ ። እንደተባሉ ። ሳዶቅ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ። ሰው ፡ ሙዶ ፡ መቃብር ፡ ከገባ ፡ በኋላ ። ፈርሶ ፡ በስብሶ ፡ ይቀራል ። ነፍሱም ፡ እንደጉም ፡ ሽንት ፡ በንና ፡ ትቀራለች ። የሚል ፡ ነው ። የሱን ፡ ባህል ፡ የያዙ ሁሉ ፡ ሰዱቃውያን ፡ ተብለዋል ።

ዘዳ፡፳፭፡፭። ማቴ፡፳፪፡፳፫። ማር፡፲፪፡ ፲፱። ሉቃ፡፳፡፳፭።ግብ፡፳፫፡፰።ማኒም ፣ ማለት ፣ ዝጉሐዊ ፣ ባሕታዊ ፣ ጸዋሚ ፤ ተሐራሚ ፣ ማለት ፣ ነው ። ገንዘብ ፣ ጠፋበት ፥ ገንዘቡም ፣ አህያ ፣ ነው ፤ በጸም ፣ በጸሎት ፣ በቀኖና ፣ ስኖር ፣ እንዴት ፣ የኔ ፣ ገንዘብ ፣ ይጥፋ ፣ ብሎ ፣ በጸሎቱ ፣ ተመክቶ ፣ የሐሰት ፣ መሥዋዕት ፣ ሠውቶ ፣ ቀኖና ፣ ገባ ፥ ገንዘቤ ፣ (አህያዬ) ፣ ቢገኝ ፣ ሠራሚ ፣ መጋቢ ፣ አለ ፥ እላለሁ ፥ ባይገኝ ፣ ግን ፣ የለም ፣ እላለሁ ፣ ብሎ ፤ ጌታም ፣ በትህትና ፣ ቢለምኑት ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ በሐሰት ፣ ቢለምኑት ፣ አይሰማምና ፥ ይገኝ ፣ የነበረውን ፣ አጠፋበት ፥ ይቀርብ ፣ የነበረውን ፣ አራቀበት ፤ ዘፍ፡፩፡፩ ።

ሱባዔው ፣ ሲፈጸም ፣ ወጥቶ ፣ አልባቲ ፣ ሠራሚ ፣ ወመጋቢ ፣ ለዛቲ ፣ ዓለም ፥ ለዚህች ፣ ዓለም ፣ ሠራሚ ፣ መጋቢ ፣ የላትም ፤ ብርሃናት ፣ በልማድ ፣ ይመላለሳሉ ፤ አፍላጋት ፣ በልማድ ፣ ይፈሳሉ ፥ ክረምትና ፣ በጋ ፣ ቀንና ፣ ሌሊት ፣ በልማድ ፣ ይፈራረቃሉ ፤ ሰውም በልማድ ፣ ይወለዳል ፣ በልማድ ፣ ይሞታል ፣ ብሎ ፣ ተነሣ ፥ እንዲህ ፣ ብሎ ፣ የተነሣ ፣ በማን ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ ቢሉ ፥ በዳዊት ፣ ጊዜ ፣ ነው ፣ ይላሉ ፥ ምነው ፣ ዳዊትን ፣ ያህል ፣ ሰው ፣ በዘመኑ ፣ እንዲህ ፣ ያለ ፣ መናፍቅ ፣ ሲነሣ ፣ አያጠፋውም ፣ ነበርን ፣ ቢሉ ፥ በሃይማኖታችሁ ፣ ሙቱበት ፣ እንጂ ፣ ግዶ ሉበት ፣ አይልምና ፤ እንዲህስ ፣ እንዳንል ፣ መምለኬ ፣ ጣዖት ፣ ነቢየ ፣ ሐሰት ፣ የተነሣ ፣ እንደሆነ ፣ በእሳት ፣ ተቃጥሎ ፣ በድንጋይ ፣ ተወግሮ ፣ ይሙት ፣ ትላለች ፣ አሬት ፣ ብሎ ፣ ዘሌ፡፳፡፭-፮። በኋላ ፣ ተነሥቷል ፣ ይላሉ ፤ የሕዝቅያስን ፣ የትሩፋንን ፣ የመቃብያንን ፣ አስቀድሞ ፣ እንደተናገረ ፣ አስቀድሞ ፣ ተገልጸለት ፣ ተናግሮታል ። አንተ ፣ ማኒ ፣ ሠራሚ ፣ መጋቢ ፣ የለም ፣ ብለህ ፥ ብትለምነው ፣ ልመናህን ፣ ሳይሰማህ ፣ ቀረ ፣ እንጂ ፥ እኔስ ፣ ሠራሚ ፣ መጋቢ ፣ አለ ፣ ብዬ ፣ ብለምነው ፣ የእውነት ፣ ልመዬን ፣ ሰማኝ ።

መዝ ፡ ፻፲፯ ፡ ፭ ።

ወእምንዳቤየ ፡ አርኀበ ፡ ሊተ ።

ከመከራዬ ፣ አውጥቶ ፤ በተድላ ፣ በደስታ ፣ አኖረኝ ፤ አንድም ፣ ከመከራዬ ይልቅ ፣ ደስታዬን ፣ አበዛልኝ ፥ መጽሐፍ ፣ ለልማዱ ፣ መከራን ፣ በጠባብ ደስታን ፣ በሰፊ ፣ መስሎ ፣ ይናገራልና ።

ተሣሃለኒ ፡ ወስምዐኒ ፡ ጸሎትየ ።

ይቅር ፣ ብሎ ፣ ልመናዬን ፣ ሰማኝ ፣ አንድም ፣ ልመናዬን ፣ ሰምቶ ፣ ይቅር ፣ አለኝ ።

፪ ፤ ደቂቀ ፡ እጓለ ፡ እመሕያው ፡ እስከ ፡ ማዕዜኑ ፡ ታከብዱ ፡ ልበክሙ ።

የማኒ ፣ ልጆች ፣ ሠራሚ ፣ መጋቢ ፣ የለም ፣ በማለት ፣ እስከ ፣ መቸ ፣ ልቦናችሁን ፣ ታፀናላችሁ ፥ ወአኒ ፣ አከብድ ልቦ ፣ ለፈርዖን ፣ እንዲል ፥

ለምንት ፡ ታፈቅሩ ፡ ከንቶ ፡ ወተኃሡ ፡ ሐሰተ ።

ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ የለም ፡ ማለትን ፡ ለምን ፡ ትወዳላችሁ ።

፫ ፡ አእምሩ ፡ ከመ ፡ ተሰብሐ ፡ እግዚአብሔር በጻድቁ ።

አዬ ፡ እግዚአብሔርስ ፡ ኑሮ ፡ በጻድቁ ፡ በኖኅ ፡ በጻድቁ ፡ በሎጥ ፡ እንደ ፡ ተመሰገነ ፡ እወቁ ፡ ዘፍ ፡ ፲፱ ፡ ፲፭ ።

እግዚአብሔር ፡ ይሰምዓኒ ፡ ሶበ ፡ ጸራኅኩ ፡ ኀቤሁ ። ዮና ፡ ፪ ፡ ፫ ።

እግዚአብሔር ፡ ወደርሱ ፡ መልሼ ፡ የለመንሁትን ፡ ልመናዬን ፡ ይሰማኛል ፤

፬ ፤ ተምዑ ፡ ወኢተአብሱ ።

ኢትተምዑ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ አትቆጡ ፤ አንድም ፡ እንዳለ ፡ ይሆናል ፤ (ተምዑ) ካራቱ ፡ በሕርያት ፡ የተፈጠረ ፡ ሰው ፡ ቊጣ ፡ ይስማማዋልና ፤ ጊዜ ፡ ቢያጋጥማችሁ ፡ ተቈጡ ፡ (ወኢተዓብሱ) ፡ ሳትታረቁ ፡ ግን ፡ አትደሩ ፤ ወዘእን በለ ፡ ይዕርብ ፡ ፀሐይ ፡ አቊርሩ ፡ መዓተክሙ ፡ እንዲል ፤ ኤፌ ፡ ፬ ፡ ፳፮ ።

አንድም ፡ (ተምዑ) ፡ በሚገባ ፡ ተቈጡ ፡ የሚገባ ፡ ቊጣ ፡ አለና ፤ በ ፡ መዓት ፡ ዘበርትዕ ፡ እንዲል ።

ሕፃናት ፡ የተማሩትን ፡ እንዳይገድፉ ፡ ያልተማሩትን ፡ እንዲማሩ ፤ መናፍቃን ፡ ሃይማኖት ፡ እንዳይነቅፉ ፡ (እንዳያጠፉ) ፡ ክህደት ፡ እንዳያሰፉ ፤ ተቆጡ ፤ (ወኢተዓብሱ) ፡ ሕፃናት ፡ ያልተማሩትን ፡ ሲማሩ ፤ የተማሩትን ፡ ሳይገድፉ ፤ መናፍቃን ፡ ሃይማኖት ፡ ሳይነቅፉ ፤ ክህደት ፡ ሳያሰፉ ፡ አትቆጡ ፡ አንድም ፡ (ተምዑ) ፡ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ የለም ፡ የሚለውን ፡ ተቈጡ (ወኢተዓብሱ) ፡ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ የለም ፡ አትበሉ ፤ ያዕ ፡ ፭ ፡ ፲፱ - ፳ ።

ወዘትሔልዩ ፡ በልብክሙ ፡ ውስተ ፡ ምስካበክሙ ፡ ይትዐወቅሙ ።

ይትዓወቀክሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ቀን ፡ ያሰባችሁት ፡ ሌሊት ፡ በመኝታችሁ ፡ ይገለጽላችኋል ። የቀን ፡ አእምሮ ፡ ዝርው ፡ ነው ፤ ዓይነ ፡ ሥጋ ፡ ክብርሃነ ፡ ፀሐይ ፡ ጋር ፡ ተዋህዶ ፡ ፀሐይ ፡ ከደረሰችበት ፡ ይደርሳል ፡ ሐሳብ ፡ ይበተናል ፤ የሌሊት ፡ አእምሮ ፡ ግን ክት ፡ ነው ፤ ያን ፡ ብርሃን ፡ ወስዶ ፡ ይህን ፡ ጭለማ ፡ ያመጣ ፡ ዘፍ ፡ ፩ ፡ ፬ - ፭ ፡ ሰብአ ፡ ትካትን ፡ አጥፍቶ ፡ ኖኅን ፡ ዘፍ ፡ ፮ ፡ ፭ - ፰ ። ሰብአ ፡ ሰዶም ፡ ሰብአ ገሞራን ፡ አጥፍቶ ፡ ሎጥን ፡ ዘፍ ፡ ፲፱ ፡ ፳ - ፳፱ ። ሰብአ ፡ ግብፅን ፡ አጥፍቶ ፡ ኀኤልን ፡ ዘፀ ፡ ፲፬ ፡ ፳፰ - ፳፱ ። ያዳነ ፡ እሱ አይደለምን ፡ ብሎ ፡ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ እንዳለ ፡ ለልቡና ፡ ይረዳልና ፤ ሠ፬ ፡ ማንሽ ፤ አንድም ፡ (ይትዓወቅሙ) ፡ በመዓልት ፡ ያሰባችሁት ፡ ሌሊት ፡ በመኝታችሁ ፡ ይገለጽላችሁ ፡ ዘንድ

፭ ፤ ሠ፬ ፡ መሥዋዕተ ፡ ጽድቅ ፡ ወተወከሉ ፡ በእግዚአብሔር ።

ሠ፬ ፡ ካልኸ ፡ ብሎ ፡ መሥዋዕት ፡ አለ ፡ እንጂ ፡ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ አለ ፡

ብላችሁ ፡ እውነት ፡ ተናገሩ ፤ በእግዚአብሔርም ፡ እመኑ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ አንድም ፡ ማኒን ፡ የሐሰት ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዋ ፡ ብሎት ፡ ነበርና ፡ እውነተኛ ፡ መሥዋዕት ፡ ሠዉ ።

፫ ፤ ብዙኃን ፡ እለ ፡ ይቤሉ ፡ መኑ ፡ ያርእየነ ፡ ሠናይቶ ።

ህልውናውን ፡ ማን ፡ በነገረን ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ ናቸው ፤ ከቀደሙ ፡ ሰዎች ፡ አብርሃም ፡ ከኋላ ፡ ሰዎች ፡ ሙሴ ፡ ጸሊም ።

ተፀውቀ ፡ በላዕሌነ ፡ ብርሃነ ፡ ገጽከ ፡ እግዚኦ ።

ለነ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ተነበዩ ፡ ላዕሌኪ ፡ እንዲል ፤ የአክልህ ፡ መኖር ፡ ለኛ ፡ ተገለጸ ፤ አንድም ፡ በዘላዕሌነ ፡ ከኛ ፡ በላይ ፡ ባለ ፡ በፀሐይ ፡ ታወቀ ፡ በክበቡ ፡ አብ ፡ በብርሃኑ ፡ ወልድ ፡ በሙቀቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይመሰላልና ።

፮ ፡ ወወደይከ ፡ ትፍሥሕተ ፡ ውስተ ፡ ልብነ

ደስታን ፡ በልባችን ፡ ውስጥ ፡ አሳደርክልን ።

እምፍሬ ፡ ሥርናይ ፡ ወወይን ፡ ወቅብዕ ፡ በዝኃ ።

ከስንዴ ፡ ከወይን ፡ ከዘይት ፡ ይልቅ ፡ ደስታ ፡ በዛልን ፤ አንድም ፡ ስንዴ ፡ በልቶ ፡ ወይን ፡ ጠጥቶ ፡ ዘይት ፡ ተቀብቶ ፡ ደስ ፡ ከሚለው ፡ ሰው ፡ ይልቅ ፡ ደስታ ፡ በዛልን ፤ አንድም ፡ (ወወደይከ) ፡ ሃይማኖተ ፡ አሪትን ፡ ሠራሀልን ፤ (እምፍሬ ፡ ሥርናይ) ፡ ይኸውም ፡ ሃይማኖት ፡ ከስንዴ ፡ ከወይን ፡ ከዘይት ፡ ይልቅ ፡ በዛልን ፡ የሃይማኖት ፡ ብዛት ፡ ሌላ ፡ የለውም ፡ አንዱ ፡ ላንዱ ፡ አብነት ፡ ሆኖ ፡ የሚያስረዳ ፡ ስለሆነ ፡ እየቀደመ ፡ የሚረዳ ፡ ስለሆነ ፡ የሰሚው ፡ ከርእይ ፡ የሚያደርስ ፡ ስለሆነ ፡ በሃይማኖት ፡ ፀንቶ ፡ የሚሠራ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፡ አንድም ፡ (ብዙኃን ፡ እለ ፡ ይቤሉ ፡ መኑ ፡ ያርእየነ ፡ ሠናይቶ) ፡ ተሠግዎቶ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ሰው ፡ መሆኑን ፡ ማን ፡ በነገረን ፡ የሚሉ ፡ ብዙ ፡ ናቸው ፤ ተአውቀ ፡ በላዕሌነ ፡ ብርሃነ ፡ ገጽከ ፡ እግዚአ) ፡ የአካልህ ፡ መታወቂያ ፡ ወልድ ፡ ለኛ ፡ ተገለፀ ፡ በዘአምኔነ ፡ ይላል ፡ ከእኛ ፡ በነሣው ፡ ሥጋ ፡ ተገለጸ ።

፮ ፡ ወወደይከ ፡ ትፍሥሕተ ፡ ውስተ ፡ ልብነ (ወወደይከ ፡ ትፍሥሕተ ፡ ውስተ ፡ ልብነ) ።

ሃይማኖተ ፡ ወንጌልን ፡ ሠራህልን ። (እምፍሬ ፡ ሥርናይ ፡ ወወይን ፡ ወቅብዕ ፡ በዝኃ) ፡ ይኸውም ፡ ሃይማኖት ፡ ከስንዴ ፡ ከወይን ፡ ከዘይት ፡ ፍሬ ፡ ይልቅ ፡ በዛልን ። ሐተታ ፡ እንዳለፈው ፡ አንድም ፡ (ወወደ ፡ ትፍ ፡ ውስ ፡ ል ፡ እም ፡ ሥር ፡ ወወ ፡ ወቅ ፡ በዝኃ) ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ልጅነትን ፡ ከመቀበላችን ፡ የተነሣ ፡ ሃይማኖት ፡ ፀናልን ፤ አንድም ፡ (ወወደይከ) ፡ ጸጋ ፡ ክብርን ፡ ሰጠኸን ፤ (እምሥርናይ) ፡ ይኸውም ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ ከስንዴ ፡ ከወይን ፡ ከዘይት ፡ ይልቅ ፡ በዛልን አንድም ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ሃይማኖትን ፡ ከመቀበላችን ፡ የተነሣ ፡

ጸጋ ፡ ክብር ፡ ፀናልን ፤ ቅዱሳን ፡ እየቀ
ደም ፡ እየበቁ ፡ የሚያገኙት ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡
ይህ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ አይነገርምና ።

፮ ፤ በሰላም ፡ ቦቱ ፡ እሰክብ ፡ ወእነውም ።

ማኒ ፡ አንተ ፡ ሠራዒ ፡ መጋቢ ፡ የለ
ም ፡ በማለትህ ፡ ከፈጣሪህ ፡ ጋራ ፡ ሳ
ትስማማ ፡ ሳትታረቅ ፡ ትሞታለህ ፡ ት
ቀበራለህ ፡ እንጂ ፤ እኔስ ፡ ሠራዒ ፡
መጋቢ ፡ አለ ፡ ብዬ ፡ ከፈጣሪዬ ፡ ጋራ ፡
ታርቄ ፡ ተስማምቼ ፡ እሞታለሁ ፡ እ
ቀበራለሁ ።

እስመ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ በተስፋ ፡ ባሕ
ቲትከ ፡ አኅደርከኒ ።

የብቻህ ፡ በተስፋ ፡ ህልውና ፡ አንድ
ም ፡ ባሕቲተከ ፡ ብቻህን ፡ በተስፋ ፡
ህልውና ፡ በብቻህ ፡ ተስፋ ፡ ህልው
ና ፤ አፅንተኸኛልና ፤ መኑ ፡ አስተደ
ኃረ ፡ ማዕዘኒሃ ፡ ለምድር ፡ እንዲል ።

ኢዮ ፡ ፴፰ ፡ ፬ ። አንድም ፡ (በሰላም ፡
ቦቱ ፡ እሰክብ ፡ ወእነውም) ፡ ማኒ ፡ አ
ንት ፡ ከሦስቱ ፡ አካል ፡ አንዱ ፡ ሰው ፡
ሆኖ ፡ ያድነኛል ፡ ሳትል ፡ ትሞታለህ ፡
ትቀበራለህ ፡ እንጂ ፡ እኔስ ፡ ከሦስቱ ፡
አካል ፡ አንዱ ፡ ሰው ፡ ሆኖ ፡ ያድነኛ
ል ፡ ብዬ ፡ እሞታለሁ ፡ እቀበራለሁ ፤
(እስመ ፡ አንተ ፡ እግዚኦ ፡ በተስፋ ፡
ባሕቲትከ ፡ አኅደርከኒ) ፡ ብቻህን ፡
በተስፋ ፡ ትንሣኤ ፡ አጽንተኸኛልና ።

መዝሙር ፡ ፭ ።

፭ ፤ ቃልየ ፡ አጽምዕ ፡ እግዚኦ ።

ስለ ፡ ትሩፋን ፡ ተናግሮታል ፤ ከአሥ
ሩ ፡ አርእስት ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ ነው ፤ ት
ሩፋን ፡ የሚላቸው ፡ አሥሩ ፡ ነገድ ፡
ተማርከው ፡ በኢየሩሳሌም ፡ የቀሩ ፡
ሁለቱ ፡ ነገድ ፡ ናቸው ። ፪ ፡ ሐፀ ፡ ፴፮ ፡ ፭-
፳፫ ። አንድም ፡ ሁሉም ፡ ተማርከው ፡
አበው ፡ አልቀው ፡ የቀሩ ፡ ውሉድ ፡
ናቸው ፤ የአምስቱን ፡ ነገሥት ፡ ታሪክ ፡
የሚተርኩ ፡ አሉ ፤ ያስተርካል ፡ እን
ደ ፡ ወንጌል ። ማቴ ፡ ፭-፲፩ ። ትሩፍ ፡
ማለት ፡ ፍጹም ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ረ
ድዕ ፡ ትሩፍ ፡ እንዲል ።

አቤቱ ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

ወ ለ ቡ ፡ ጽ ራ ኅ የ ።

ልመናዬን ፡ ልብ ፡ አድርገህ ፡ ስማኝ ።

፪ ፤ ወአጽምዐኒ ፡ ቃለ ፡ ስእለትየ ።

ነገረ ፡ ስእለትየ ፡ ሲል ፡ ነው ፤ የልመ
ናዬን ፡ ነገር ፡ ስማኝ ፡ የልመና ፡ ስ
ልቱ ፡ ብዙ ፡ ነውና ፡ መላልሶ ፡ ተና
ገረ ።

ንጉሥየኒ ፡ ወአምላኪየኒ ።

የባቢሎናውያን ፡ ንጉሣቸው ፡ ብል
ጣሶር ፡ አምላካቸው ፡ ቤል ፡ ዳጎን ፡
ነው ፤ የኔ ፡ ንጉሤም ፡ ፈጣሪዬም ፡ አ
ንተ ፡ ነህ ፤ አንድም ፡ ንጉሥ ፡ ሠራዊ
ቱን ፡ ፈጣሪ ፡ ፍጥረቱን ፡ እንዲረዳ ፡
ፈጥነህ ፡ እርዳኝ ።

እስመ ፡ ጎቤከ ፡ እጼሊ ፡ እግዚኦ ።
እቤቱ ፡ ወዳንተ ፡ መልሼ ፡ እጸልያለሁ ፡ እለምናለሁና ።

፫ ፤ በጽባሕ ፡ ስምዐኒ ፡ ቃልየ ።

ዕለት ፡ ዕለት ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ፤ አንድም ፡ ፈጥነህ ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

ብጽባሕ ፡ እቀውም ፡ ቅድሜከ ፡ ወአስተርኢ ፡ ለከ ።

ዕለት ፡ ዕለት ፡ አንድም ፡ ፈጥኜ ፡ በመሥዋዕት ፡ በጸሎት ፡ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡ ገብቼ ፡ እገለጻለሁና ።

፬ ፤ እስመ ፡ ኢኮንከ ፡ አምላክ ፡ ዘዐመፃ ፡ ያፈቅር ።

(አናበህ) ፡ ዓመፅን ፡ የሚወድ ፡ የባቢሎናዊ ፡ አንድም ፡ የብልጣሶር ፡ አምላክ ፡ አይደለህምና ። አንድም ፡ (እስመ ፡ አከ ፡ አምላክ ፡ ዘዓመፃ ፡ ታፈቅር) ፡ አምላክ ፡ ዓመፅን ፡ የምትወድ ፡ አይደለህምና ።

ወኢያኅድሩ ፡ እኩያን ፡ ምስሌከ ።

እኩያን ፡ ባቢሎናውያን ፡ አንድም ፡ ሴዴቅያስ ፡ ኢኮንያን ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ አይኖሩም ፡ ማለት ፡ አድረህባቸው ፡ አትኖርምና ፡ ሲል ፡ ነው ።

፭ ፤ ወኢይነብሩ ፡ ዐማፅያን ፡ ቅድመ ፡ አዕይንቲከ ።

ዓመፀኞች ፡ ባቢሎናውያን ፡ አንድም ፡ ሴዴቅያስ ፡ ኢኮንያን ፡ በባለሟልነትህ ፡ ፀንተው ፡ አይኖሩም ።

ጸላዕከ ፡ እግዚኦ ፡ ኵሎሙ ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ

ዓመፅ ፡ የሚሠሩ ፡ ባቢሎናውያንን ፡ ሁሉ ፡ አንድም ፡ ሴዴቅያስ ፡ ኢኮንያንን ፡ ጠላህ ።

፮ ፤ ወትገድፎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ እለ ይነቡ ፡ ሐሰተ ።

ከሰብዓ ፡ ዘመን ፡ አትርፈን ፡ እንገዛቸዋለን ፡ የሚሉ ፡ ባቢሎናውያንን ፡ ታጠፋቸዋለህ ።

ብእሴ ፡ ደም ፡ ወጕህላዌ ፡ ያስቈርር ፡ እግዚአብሔር ።

ደመ ፡ በግዕን ፡ ሰጣዖት ፡ አንድም ፡ የሰው ፡ ደም ፡ የሚያፈስ ፡ ከዳተኛ ፡ የሚሆን ፡ ባቢሎናዊን ፡ አንድም ፡ ብልጣሶርን ፡ አንድም ፡ ሴዴቅያስ ፡ ኢኮንያንን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፀየፈዋል ፡ ማለት ፡ አያድርበትም ፡ አንድም ፡ መፀያየፍ ፡ የጋራ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይጸየፈዋል ፡ ማለት ፡ ያይብኛል ፡ ይሰማብኛል ፡ አይለውም ።

ወአንሰ ፡ በብዝኀ ፡ ምሕረትከ ፡ እበውእ ቤተ ከ ።

እኔ ፡ ግን ፡ በይቅርታህ ፡ በቸርነትህ ፡ ብዛት ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እገባለሁ ።

ወእሰግድ ፡ ውስተ ፡ ጽርሐ ፡ መቅደስከ በፈሪሆትከ ።

አንተን ፡ በመፍራት ፡ አንተን ፡ በማምለክ ፤ ወሶበ ፡ አከ ፡ በፍርሃት ፡ ይስሕቅ ፡ እምፈነውከኒ ፡ ዕራቅየ ፡ እንዲል ፡ ዘፍ ፡ ፴፩ ፡ ፵፪ ።

መመስገኛህ ፡ የምትሆን ፡ ደብረ ፡ መቅደስህ ፡ በተሠራችባት ፡ የአብርሃም ፡ ዕፃ ፡ ክፍል ፡ በምትሆን ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እሰግዳለሁ ፤ አብርሃምን ፡ መቅ

ደስ ፡ አለው ፡ ማኅደረ ፡እግዚአብሔ ፡ ር ፡ ነውና፤ ወአስተፍሣሕከ፡ በኃይል ከ ፡ ተረፈ ፡ መቅደስከ ፡ እንዲል ፡ ዘፀ ፡ ፲፭ ፡ ፲፫ ።

፮ ፡ እግዚአ ፡ ምርሐኒ ፡ በጽድቅከ ።

አቤቱ ፡ ወሰብዓ ፡ ዓም ፡ ኀሊቆ ፡ እት ዜቀሎ ፡ ለንጉሠ ፡ ባቢሎን ፡ ወለዝ ሉ ፡ ሕዝባ ። ብለህ ፡ በተናገርከው ፡ በጽኑ ፡ ቀጠሮህ ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ መንገድ ፡ መርተህ ፡ አውጣኝ ።

ወበእንተ ፡ ጸላዕትየ ፡ አርትዕ ፡ ፍናትየ፡ ቅድሜከ ።

ከሰብአ ፡ ዘመን ፡ አትርፈን ፡ እንገዛቸ ዋለን ፡ የሚሉ ፡ በቢሎናውያንን ፡ ደስ አይበላቸው ፡ ብለህ ፡ የኢየሩሳሌምን ፡ መንገዴን ፡ አቅናልኝ ።

፱ ፡ እስመ ፡ አልቦ ፡ ጽድቅ ፡ ውስተ ፡ አፉሆሙ ።

በንደበታቸው ፡ እውነት ፡ የለምና ፡ ማለት ፡ አይነገርምና ።

ልቦ ሙ ኒ ፡ ከ ን ቱ ።

ልቦናቸውም ፡ ከንቱ ፡ ነውና ፡ አን ድም ፡ ይኄሊ ፡ ከንቶ ፡ ይላል ፡ ከንቱ ፡ ነገርን ፡ ያስባልና ።

ከመ ፡ መቃብር ፡ ክሡት ፡ ጕራዔሆሙ ።

የተከፈተ ፡ አንደበታቸው ፡ እንደመ ቃብር ፡ ነው ፡ ሞት ፡ ቢገድል ፡ መቃ ብር ፡ ቢቀበል ፡ በቃኝ ፡ ጠገብሁ ፡ እን ዳይል ፡ እነሱም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ሲናገሩ ፡ በቃን ፡ ጠገብን ፡ አይሉምና ፤ አንድ ም ፡ አንደበታቸው ፡ እንደተለሰነ ፡ መቃብር ፡ ነው ፤ ያንን ፡ በላይ ፡ ሱሳን ፡ ወርድ ፡ ይስሉበታል ፡ ሐረግ ፡ ይስቡ በታል ። አበባ ፡ ያፈነዱበታል ። ከፍ ተው ፡ ያዩት ፡ እንደሆነ ፡ መግነዙ ፡ ተበጣጥሶ ፡ እገር ፡ ፈሶ ፤ ሥጋው ፡ ተል ከስክሶ ፤ አጥንቱ ፡ ተከስክሶ ፤ ለዓይን ፡ ያስጸይፋል ፡ ላፍንጫ ፡ ይከረፋል ፤ እ ነሱም ፡ ሰውንም ፡ እግዚአብሔርንም ፡ የሚያሳዝን ፡ ነገር ፡ ሲናገሩ ፡ ይኖራ ሉና ። ኤር ፡ ፭ ፡ ፲፮ ። ማቴ ፡ ፳፫ ፡ ፳፯-፳፰ ። ሮሜ ፡ ፫-፲፫ ።

ወጸልሐዉ ፡ በልሳናቲሆሙ ።

በንደበታቸው ፡ ከዱ ፡ ለጊዜው ፡ እላ ንተማ ፡ የዳዊት ፡ የሰሎሞን ፡ ልጆች ፡ አይደላችሁም ፡ ይሏቸዋል ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ እኒህ ፡ ባሮች ፡ እውነት ፡ መስ ሏቸው ፡ አትወጡም ፡ ከሰባ ፡ ዘመን ፡ አትርፈን ፡ እንገዛችኋለን ፡ ይሏቸዋ ልና ።

፲ ፤ ኰንኖሙ ፡ እግዚአ ፡ ወይደቁ ፡ በውዴሆ ሙ ።

ነገር ፡ በመሥራታቸው ፡ አንድም ፡ እኔን ፡ ካንተ ፡ በማጣላታቸው ፡ አጥ ፋቸው ፡ እስመ ፡ አንተ ፡ ትኬንኖ ፡ ለእኑከ ፡ እንዲል ።

ወበከመ ፡ ብዝኀ ፡ ኃብሎሙ ፡ ስድዶሙ ።

ሀሰት ፡ እንደመናገራቸው ፡ መጠን ፡ ከሀገራቸው ፡ ወደሰው ፡ ሀገር ፡ ከሕ ይወት ፡ ወደሞት ፡ ከተድላ ፡ ወደመ ከራ ፡ አውጥተህ ፡ ስደዳቸው ።

እስመ ፡ አምረሩከ ፡ እግዚአ ።

አቤቱ ፡ አንተን ፡ አሳዝነዋልና ፡ ሰው ን ፡ መበደል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማሳ

ዘን ፡ ነውና ፤ አንድም ፡ ጣዖት ፡ አም
ልከው ፡ አንተን ፡ አሳዝነዋልና ።

፲፩ ፤ ወይትፈሥሑ ፡ ብኪ ፡ ዅሎሙ ፡ እለ ፡ ይትዌከሱከ ።

አንተን ፡ ያመኑህ ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ በንተ ፡ አምነው ፡ በተሠራላቸው ፡ ሥራ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

ለዓለም ፡ ይትኃሠዩ ፡ ወትነድር ፡ ላዕሌሆሙ ።

ተጎድር ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ለዓለም ፤ ይት
ኃሠዩ ፡ ለዓለም ፡ ብለህ ፡ ግጠም' ፤ ለዘ
ላለም ፡ አድረጎባቸው ፡ ትኖራለህ ፤
ለዘለዓለም ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ይኖ
ራሉ ፤ ራእ ፡ ፲፩ ፡ ፲፰ ።

ወይትሜክሁ ፡ ብኪ ፡ ዅሎሙ ፡ እለ ፡ ያፈቅሩ ፡ ስመኪ ።

ስምህን ፡ የሚወዱ ፡ ሁሉ ፡ ይከብራሉ ፤
እምከመ ፡ አድማዕኑ ፡ መንግሥተ ፡
ንትሜካህ ፡ እንዲል ።

፲፪ ፤ እስመ ፡ አንተ ፡ ትባርኦ ፡ ለጻድቅ ።

ከሰብዓ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ትሩፍን ፡ ታበ
ዛዋለህ ፡ ዘሩባቤልን ፡ በመንግሥት ፡
ታከብረዋለህና ፤

እግዚኦ ፡ ከመ ፡ ወልታ ፡ ሥሙር ፡ ከለልከኑ

እስከዚያውም ፡ ድረስ ፡ እንዳላባሽ ፡
ጋሻ ፡ ወወርኽን ፡ ያ ፡ ከተወረወረ ፡
ጦር ፡ ከተጣለ ፡ ጠጠር ፡ እንዲያድን ፤

መዝሙር ፡ ፭ ።

፩ ፤ እግዚኦ ፡ በመዓትኪ ፡ ኢትቅሥፈኒ ።

በአርዮ ፡ ጊዜ ፡ ስለራሱ ፡ ተናግሮታ
ል ፤ ይህስ ፡ እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፤
በ ፡ አመ ፡ ይወጽኡ ፡ ። ወበ ፡ አመ ፡
ይበውኡ ፡ ነገሥት ። ነገሥታት ፡ የሚ
ዘምቱበት ፡ የሚመለሱበት ፡ ጊዜ ፡ ደ
ረሰ ። አንድም ፡ ወበጽሐ ፡ መዋዕል ፡
አመ ፡ ይወጽኡ ፡ ወአመ ፡ ይበውዑ ፡
ነገሥት ፡ ይላል ፡ አብነት ። ነገሥታቱ ፡
የሚወጡበት ፡ የሚገቡበት ፡ ጊዜ ፡
ደረሰ ፤ ስለምን ፡ ይወጡ ፡ ነበር ፡ ቢሉ ፤
መንግሥት ፡ ለማዳረስ ፤ የሀገራችን ፡
ነገሥታት ፡ መንግሥት ፡ ለማዳረስ ፡
አክሱም ፡ ይሄዱ ፡ እንደነበረ ፤ ሠራ
ዊት ፡ እንዳይራብ ፡ ደዌ ፡ እንዳይናኝ ፡
ጠላት ፡ እንዳይሠለጥንባቸው ፡ በግን
ቦት ፡ በሰኔ ፡ ዘምተው ፡ በመስከረም ፡
በጥቅምት ፡ ይመለሳሉ ፤ በሀገራችን ፡
ነገሥታቱ ፡ በመስከረም ፡ በጥቅምት ፡
ዘምተው ፡ በግንቦት ፡ በሰኔ ፡ እንዲመ
ለሱ ፤ አራት ፡ ወር ፡ ካንዱ ፡ ከተማ ፡
አራት ፡ ወር ፡ ካንዱ ፡ ከተማ ፡ ይኖ
ራሉ ። ያላመነውን ፡ አሳምነው ፤ ከመ
ነው ፡ ግብር ፡ ተቀብለው ፡ ይመለሳ
ሉ ። ተራ ፡ ጠላት ፡ የተነሣባቸው ፡
እንደሆነ ፡ ጦር ፡ ሰደው ፡ ያስወጉ
ታል ። ኃይለኛ ፡ ጠላት ፡ የተነሣባቸ
ው ፡ እንደሆነ ፡ ክተት ፡ ሠራዊት ፡
ምታ ፡ ነጋሪት ፡ ብለው ፡ ይዘምቱበ
ታል ፤ እነሱስ ፡ ዳዊትንም ፡ ያዘምቱ
ት ፡ ነበር ፡ የቀረበት ፡ ምክንያት ፡ አል

ታወቀም ፤ አንድም ፣ ታውቋል ፥ ከዕ
ለታት ፣ በንዳቸው ፣ ከአሕዛብ ፣ ጋር ፣
ገጥሞ ፣ ሲዋጋ ፥ ካራቱ ፣ ረፋይን ፣
አንዱ ፣ የጎልያድን ፣ በቀል ፣ ደገል ፣
እመልሳለሁ ፣ ብሎ ፣ ባጭር ፣ ታጥቆ ፣
ዘገር ፣ ነቅንቆ ፣ መጣበት ፥ የአዕላፈ ፣
ሺኤል ፣ ያለህ ፣ ብሎ ፣ ዝልፍልፍ ፣
አለ ፥ ወወውዐ ፣ ሎቱ ፣ እቢሳ ፣ ወል
ደ ፣ ሶርህያ ፣ እኅቱ ፣ አቢሳ ፣ ጋሻ ፣
መክቶ ፣ ዘገሩን ፣ ነጥቆ ፣ አድኖታል ።
ደንግያ ፣ የማያውቅ ፣ መደንገፁ ፣ ስለ
ምን ፣ነው ፣ ቢሉ ፥ ጦር ፣ ሲሠሩ ፣ ውሎ ፣
መድኃኒት ፣ ቀምሶ ፣ ከሴት ፣ ደርሶ ፣
ደክሞት ፣ ነበርና ፥ ምሥጢሩ ፣ ግን ፣
ኃይል ፣ የባሕርዬ ፣ ነው ፣ እንዳይል ፣
ነው ፥ በዚህ ፣ ምንክያት ፣ ኢትጥፋዕ ፣
ማኅቶቶሙ ፣ ለሺኤል ፥ የንጉሥ ፣
ሞት ፣ የፀሐይ ፣ ዕርበት ፣ በሁሉ ፣ ነው ፤
ፀሐይ ፣ ከጠፋ ፣ መተካት ፥ ንጉሥ ፣
ከሞተ ፣ ማስነሣት ፣ ይቻላልን ፥ ከእ
ንግዲህ ፣ ወዲህ ፣ ንጉሥ ፣ ከግንቡ ፣
አይውጣ ፣ ብለው ፣ ሥራት ፣ ሠርተ
ው ፣ ነበርና ።

በዚህ ፣ ምክንያት ፣ ኢዮአብን ፣ የጦ
ር ፣ አበጋዝ ፣ አድርጎ ፣ አቢሳን ፣ አዕ
ላፈ ፣ እስራኤልን ፣ ካህናቱን ፣ ታቦተ ፣
ጽዮንን ፣ አስይዘ ፣ አራቦት ፥ ዘደቂቀ ፣
አሞንን ፣ ወግታችሁ ፣ ኑ ፣ ብሎ ፣ ሰድ
ዷቸው ፣ እሱ ፣ ቀርቷል ፥ በዚያን ፣
ጊዜ ፣ በልቶ ፣ ጠጥቶ ፥ ተኝቶ ፣ ተን
ሥቶ ፣ በሰገነት ፣ ሲመላለስ ፥ ቤርሳ
ቤህ ፣ ብእሲተ ፣ አርዮ ፣ በተክል ፣
ቦታ ፣ ገብታ ፣ ስትታጠብ ፣ የገላዋ ፣
ዕርየት ፣ ፀዳለ ፣ ፀሐይ ፥ የብርቱ ፣ የወ
ሀው ፣ ጽርየት ፣ ከሰውነቷ ፣ ተዋህዶ ፣
እንደፀሐይ ፣ ስትፈልቅ ፣ አይቶ ፣ በሐ
ፀ ፣ ዝሙት ፣ ተነደፈ ፥ ብእሲተ ፣ መኑ ፣
ይእቲ ፣ ዛቲ ፥ ይህቺ ፣ የማን ፣ ሚስት ፣
ናት ፣ ብሎ ፣ ጠየቀ ፥ አኮኑ ፣ ቤርሳቤህ ፣
ብእሲተ ፣ አርዮ ፣ ገብርከ ፣ ኬጥያዊ ፥ የ
ባሪያህ ፣ የአርዮ ፣ ሚስት ፣ ቤርሳቤህ ፣
ይሉሃል ፣ እንጂ ፣ ይህች ፣ ናት ፣ አሉት ፥
ከተክል ፣ ቦታ ፣ ለምን ፣ ገባች ፣ ቢሉ ፣
የተክል ፣ ወሀ ፣ ገላ ፣ ያፀራልና ፤ ከግ
ዳጅዋ ፣ የፀራችበት ፣ ወራት ፣ ነበርና ፤
ብዙ ፣ የምትዘግበው ፣ ሽቱ ፣ ነበራ
ትና ። እሱም ፣ ዝናዋን ፣ ይሰማ ፣ ነበ
ርና ፣ አስጠርቶ ፣ ኢትሑር ፣ ኀበ ፣
ብእሲተ ፣ ብእሲ ፣ ያለውን ፣ አፍርሶ ፣
ዘፀ ፡ ፳፬-፲፯ ። ዘዳ ፡ ፭ ፤ ፳፫-፳፭ ። ተጨዋ
ውቶ ፣ ሰደዳት ፣ ፀነሰች ፤ ሙሴ ፣ አ
ንድ ፣ ወንድ ፣ ላንድ ፣ ሴት ፣ አንዲት ፣
ሴት ፣ ላንድ ፣ ወንድ ፣ ይሁን ፣ ከዚህ ፣
የወጣ ፣ በድንጋይ ፣ ተወግሮ ፣ በእ
ሳት ፣ ተጠብሶ ፣ ይሙት ፣ ያለውን ፣
ቃል ፣ ታውቃለችና ፤ ዘሌ ፡ ፳ ፤ ፲ ። እን
ተ ፣ በሠራኸው ፣ እኔ ፣ ልሞት ፣ ነው ፣
ለዚህ ፣ነገር ፣ብልሃት ፣ፈልግለት ፣ብላ ፣
ትልክበታለች ፤ በምን ፣ አውቃ ፣ ቢሉ ፣
ብልሆች ፣ ሴቶች ፣ ሲፀንሱ ፣ ያውቁ
ታል ፤ ግራ ፣ ቀኝ ፣ ኩላሊታቸው ፣
ይጮሃል ፤ ጡታቸው ፣ ይጠቁራል ፣
ከንፈራቸው ፣ ያራል ፣ ጺቅ ፣ ጺቅ ፣
ያሰኛቸዋልና ፣ በዚህ ፣ አውቃ ፣ አን

ድም ፣ ፅንስ ፣ አታሳስትም ፣ ነበርና ፤
፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፭ ፡ ፮ ። ፳ ፡ ፳ ።
ዳዊትም ፣ ያርዮን ፣ የጦር ፡ ወሬ ፣ የም
ጠይቀው ፡ ነኝና ፣ ላክልኝ ፡ ብሎ ፡
ወደ ፡ ኢዮአብ ፡ ይልክበታል ፡ ፅንስ ፡
ያሳስትልኛል ፡ ብሎ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡
ለፀብዕ ፡ አይደለም ፤ ሲመጣ ፡ እንደ
ምን ፡ ናችሁ ፡ አለው ። አምላክ ፡ ፳
ኤል ፡ ፈጣሪህ ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ፡
አንባውን ፡ ከበን ፤ ወሀውን ፡ ደፍ
ነን ፤ ደንጊያውን ፡ ኰልኵለን ፡ አስ
ጨንቀን ፡ አስጠብበን ፡ ይዘናቸዋል ፤
ድል ፡ የምንነሣቸው ፡ ይመስለኛል ፡
አለው ፤ አብልቶ ፡ አጠጥቶ ፡ ከቤት
ህ ፡ ግባ ፡ አለው ፤ እንደጃን ፡ ተከል ፡
ድንኳን ፡ አስተክሎ ፡ ድንክ ፡ አልጋ ፡
አስመጥቶ ፡ ከዘበኛው ፡ ጋራ ፡ አደረ ፤
ኢወረደ ፡ ያርዮ ፡ ከቤቱ ፡ አልገባም ፡
ብለው ፡ ይልኩበታል ፡ አንድም ፡
እሷ ፡ ትልክበታለች ፡ በነጋውም ፡ ከ
ዚያ ፡ አደረ ፤ በሦስተኛው ፡ የሚያ
ስጠማ ፡ ምግብ ፡ መግቦ ፡ የሚያሰክር ፡
ጽኑ ፡ መጠጥ ፡ ስጠው ፡ ሲል ፡ አመሸ ፡
ያም ፡ የሚጠጣ ፡ መስሎ ፡ እየተቀ
በለ ፡ ለብላቴኖች ፡ ሲሰጥ ፡ አመሸ ።
ወጽአ ፡ ስኩሮ ፡ የሰከረ ፡ መስሎ ፡ እ
የተንገደገደ ፡ ወጣ ፡ ለዳዊት ፡ ስለመ
ሰለው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ከአእምሮው ፡
አልተለየም ፡ ማለት ፡ የሰከረ ፡ ሰው ፡
ስንኳን ፡ ከምትገባው ፡ ከሚስቱ ፡ ከማ
ትገባው ፡ ከሰው ፡ ሚስት ፡ ይሄዳል
ና ፤ አኩኑ ፡ እትወትከ ፡ እምሐቅል ፡
የመጣህ ፡ ከዘመቻ ፡ አይደለምን ፡
ከቤትህ ፡ ግባ ፡ የልጅ ፡ ከንፈር ፡ የሴ
ት ፡ ፍቅር ፡ አይናፍቅህምን ፡ በዚያ
ውስ ፡ ላይ ፡ ለሴቶች ፡ ንጽሕና ፡ ይስማ
ማቸዋልን ፤ ይቻላቸዋልን ፡ አለው ፤
ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ጌታዬ ፡ ኢ
ዮአብ ፡ ወንድሜ ፡ አቢሳ ፡ አዕላፈ ፡
እስራኤል ፡ የቀን ፡ ሐሩር ፡ የሌሊት ፡
ቍር ፡ እየወረደባቸው ፡ እኔ ፡ ከቤቴ ፡
ተድላ ፡ ደስታ ፡ አደርጋለሁን ፡ አ
ለው ፡ ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፩ ፡ ፮ ። ፲፩ ።ለካ ፡ ይህ ፡
ባርያ ፡ አውቆብኛልሳ ፡ ይካተታት ፡
ብሎኝ ፡ አይደለምን ፡ ብሎ ፡ ጦማረ ፡
ሞቱን ፡ አሲይዘ ፡ ይሰደዋል ፤ ቅድ
መ ፡ አብዕዎ ፡ ለኦርዮ ፡ ውስተ ፡ ዓቢ
ይ ፡ ቀትል ፡ ወበሀየ ፡ ይሙት ፡ ብሎ ፡
ምነው ፡ ከመንገድ ፡ አይመለከተው
ም ፡ ነበርን ፡ ቢሉ ፤ መልክዐ ፡ ፊደል ፡
የማያውቅ ፡ ጨዋ ፡ ነበርና ፤ ከኟኤ
ልስ ፡ ለደብዳቤ ፡ ያህል ፡ ያልተማረ ፡
ጨዋ ፡ የለባቸውም ፡ ብሎ ፡ በፍቅር ፡
ተቀብሎ ፡ በፍቅር ፡ ስለሸኘው ፡ ባይ
ጠራጠር ፤ አንድም ፡ ዳዊትና ፡ ኢዮ
አብ ፡ የሚነጋገሩበት ፡ እንደ ፡ እንቆ
ቅልኽ ፡ ያለ ፡ ነበርና ፡ ቋንቋ ፡ ቢለወጥ
በት ፤ አንድም ፡ ራስ ፡ ራሱን ፡ የሚያ
ይ ፡ ብላቴና ፡ ተከትሎት ፡ ነበርና ፤ አ
ንድም ፡ የንጉሥ ፡ ደብዳቤ ፡ በወርቅ ፡
ቀለም ፡ ተጽፎ ፡ በአንበሳ ፡ ማኅተም ፡
ታትሞ ፡ ከደረሰበት ፡ ተሰብሮ ፡ ይታ
ያል ፡ እንጂ ፡ ከመንገድ ፡ አይታይ
ምና ፤ ወስዶ ፡ ለኢዮአብ ፡ ሰጠው ፡

እሱም ፡ ተመልክቶ ፡ ያለቅስ ፡ ጀመር ፡ ምነው ፡ ታለቅሳለህ ፡ አለው ፤ ያመጣሃት ፡ ደብዳቤ ፡ አፅንታችሁ ፡ ተዋጉ ፡ ከነዚያ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አይትረፍ ፡ ባችሁ ፡ ከናንተ ፡ አንድ ፡ አይሙት ፡ ባችሁ ፡ ትላለች ፡ የድል ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ላንዱ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ላንዱ ፡ ነው ፤ አሕዛብ ፡ ድል ፡ ያደረጉ ፡ እንደሆነ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ይጐዳል ፡ ብዬ ፡ ነዋ ፡ አለው ፤ ጠላት ፡ ሴት ፡ ይመስል ፡ ቢያለቅሱለት ፡ ይመለሳልን ፡ ባጭር ፡ ታጥቆ ፡ ዘገር ፡ ነጥቆ ፡ ቢሄዱበት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አሁንም ፡ አንተ ፡ ጌታዬ ፡ ላም ፡ እንዳየ ፡ አንበሳ ፡ ነህ ፡ ወንድሜ ፡ አቢሳ ፡ ፍየል ፡ እንዳየ ፡ ነብር ፡ ነው ፤ እኔም ፡ እንዳቅሜ ፡ በግ ፡ እንዳየ ፡ ተኵላ ፡ ነኝ ፡ ኃያላኑ ፡ ባሉበት ፡ በዕኑ ፡ ስፍራ ፡ አውለኝ ፡ አለው ፤ ይህንንስ ፡ አንተም ፡ በትለኝ ፡ ያመጣሃት ፡ ደብዳቤ ፡ ነግራኛለች ፡ አለው ፱፡ሳሙ፡፲፩-፲፪ በልቦናው ፡ ሠውረህ ፡ አድርግ ፡ ያለውን ፡ ሰላሳ ፡ ስድስት ፡ መማክርት ፡ ነበሩት ፤ ከረድኤት ፡ እግ ዚ አብሔር ፡ ጋራ ፡ የዳዊትን ፡ መንግሥት ፡ ያፀኑ ፡ ናቸው ፡ ከጌታችን ፡ ከዳዊት ፡ አርዮን ፡ ግደሉ ፡ የሚል ፡ ደብዳቤ ፡ መጥቷልና ፤ የሚድንበትን ፡ ምክንያት ፡ ፈልጉለት ፡ አላቸው ፤ እስመ ፡ ኃያል ፡ ቃለ ፡ ንጉሥ ፡ እንዲል ፡ የንጉሥ ፡ ቃል ፡ አነሰ ፡ ብለው ፡ አይጨምሩበት ፤ ረዘመ ፡ ብለው ፡ አያሳጥሩት ፡ የራቀውን ፡ ያቀርባል ፤ የቀረበውን ፡ ይጠቅሳል ፤ በዚያውም ፡ ላይ ፡ ዳዊት ፡ ልበ ፡ አምላክ ፡ ነው ፤ ከኛ ፡ ከተለየ ፡ የተገለፀለት ፡ እንዳለ ፡ እናውቃለንን ፡ ይልቅስ ፡ ያዘዘህን ፡ አድርግ ፡ አሉት ፡ ሄደው ፡ ገጠሙ ፤ አርዮም ፡ ጦር ፡ ሲያይ ፡ እንደተጠማ ፡ ዋልያ ፡ ላም ፡ እንዳየ ፡ አንበሳ ፡ ነውና ፤ እየደነፋ ፡ ሄዶ ፡ ገጠመ ፤ ባይን ፡ ጥቅሻ ፡ በከንፈር ፡ ንክሻ ፡ አለንጋ ፡ አጩኸው ፡ ጥለውት ፡ ሸሹ ፡ ምንተ ፡ ከንክሙ ፡ አዕላፈ ፡ ሺኤል ፡ እያለ ፡ ብቻውን ፡ ተደብድቦ ፡ ሙቷል ፡ ምንተ ፡ ከንክሙ ፡ ማለቱ ፡ ስለምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ልማድ ፡ ቢለወጥበት ፡ ለልማዱ ፡ ሺኤል ፡ ድልም ፡ ቢሆኑ ፤ ድልም ፡ ቢያደርጉ ፡ እንደሐማሴን ፡ ሰው ፡ ወደፊት ፡ ጥሰው ፡ ይሄዳሉ ፡ እንጂ ፡ ወደኋላ ፡ አይመለሱም ፡ ነበርና ፤ ይኸውም ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፤ አርዮ ፡ የጌታ ፡ ጦማረ ፡ ሞቱን ፡ ይዘ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ አራበት ፡ እንደሄደ ፡ ጌታም ፡ ከሊቶስጥራ ፡ ወደ ፡ ቀራንዮ ፡ መስቀሉን ፡ ተሸክሞ ፡ ሄዷልና ።

ኋላ ፡ ግን ፡ አግባ ፡ መልስ ፡ ብለው ፡ ድል ፡ አድርገዋቸዋል ፤ ኢዮአብም ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ ከጦር ፡ ያልዋለ ፡ ብላቴና ፡ ይልካል ፡ አሽከሮችህ ፡ እነዕገሌ ፡ እነዕገሌ ፡ አለቁ ፡ ብለህ ፡ ንገረው ፡ ይቂጣል ፡ አርዮ ፡ ባሪያህም ፡ እንጂ ፡ ሞተ ፡ በለው ፡ ነገር ፡ በዚህ ፡ ይወሰናል ፡ ብሎ ፡ ሰው ፡ እንደነገሩት ፡ በቅሎ ፡

እንዳሰገሩት ፡ ነውና ፤ ያውም ፡ አፈ ሌ ፡ ወታደር ፡ ያልነገሩትን ፡ ጨምሮ ፡ መናገር ፡ ልማዱ ፡ ነውና ፤ ሞውነ ፡ ወአውጽኡነ ፡ ውስተ ፡ ገዳም ፡ ወ ድኅረ ፡ ተመየጥናሆሙ ፡ ወአግባዕና ሆሙ ፡ እስከ ፡ ቅዕረ ፡ ሀገር ፡ አስቀ ድመው ፡ ድል ፡ ነስተው ፡ ወደ ፡ ዱር ፡ አባረሩን ፡ ኋላ ፡ ግን ፡ አግባ ፡ መል ስ ፡ ብለን ፡ ድል ፡ አደረግናቸው ፡ ወነደፉነ ፡ ሰብአ ፡ ሐፅ ፡ ወጎልቁ ፡ ደ ቅከ ፤ በጦር ፡ በጠጠር ፡ ብለው ፡ እ ሽከሮችህ ፡ አለቁ ፡ አለው ፡ ዳዊትም ፡ ሰምቶ ፡ ዛሬስ ፡ ኢዮአብ ፡ አረጀና ፡ የጦር ፡ መላ ፡ ያጠፋል ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡ ተቈጣ ፡ ለምንት ፡ ቀረብክሙ ፡ ኀበ ፡ ዓረፍት ፡ ኢተአምሩኑ ፡ ከመ ፡ ትቋ ስሉ ፡ ወትመውቱ ፤ መኑ ፡ ቀተሎ ፡ ለአቤሜሌክ ፡ ወልደ ፡ ሮብዓም ፡ አ ክኑ ፡ ብእሲት ፡ ወገረት ፡ ላዕሌሁ ፡ ስባረ ፡ ማሕረፅ ፡ ወሞተ ፡ በቴምናስ ፡ ሀገር ። መሳ፡፱-፶፫። በቅዕር ፡ ተጠግ ታችሁ ፡ ለምን ፡ ተዋጋችሁ ፡ የሮብዓ ምን ፡ ልጅ ፡ አቤሜሌክን ፡ ማን ፡ ገደ ለው ፡ ሴት ፡ የወፍጮ ፡ ስባሪ ፡ በመስ ከት ፡ አዝልቃ ፡ የገደለችው ፡ አይደ ለምን ፡ አለው ፡ ፳ኤል ፡ ከዚህ ፡ የተነ ሣ ፡ ቅጽር ፡ ተጠግታችሁ ፡ አትዋጉ ፡ ብለው ፡ ሥርዓት ፡ ሠርተው ፡ ነበርና ፤ ባሪያህ ፡ አርዮም ፡ እንጂ ፡ ሞተ ፡ አለ ው ፡ ደስ ፡ አለው ፡ ጠላት ፡ የጠፋል ኝ ፡ መስሎት ፡ ኢዮአብን ፡ እንዲህ ፡ በለው ፡ በ ፡ አመ ፡ ከመዝ ፡ ወበ ፡ አመ ፡ ከማሁ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እንደአባቱ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ እ ናቱ ፡ ነው ፤ አንድም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ ሲለው ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሲያዝን ፡ ነው ፤ ድል ፡ አደረግሁ ፡ ብለህ ፡ ደስ ፡ አይበልህ ፤ ሰው ፡ አለቀብኝ ፡ ብለህ ፡ አትዘን ፤ ጦርም ፡ አንሰህ ፡ እንደሆነ ፡ እጨምርልሃለሁ ፡ በለው ፡ ብሎ ፡ ይ ልክበታል ። ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፩-፲፯-፳ ።

በዳዊት ፡ ጊዜ ፡ የነበረ ፡ ነቢይ ፡ ናታ ን ፡ ይባላል ፤ ጌታ ፡ በዳዊት ፡ ናታንን ፡ ያዳኝበታል ፡ የዳዊትን ፡ ነገር ፡ አየ ህ ፡ የበጉ ፡ አብነት ፡ ይሆናል ፤ ብዙ ፡ ሳአልን ፡ ገድዬ ፡ ባነግሠው ፡ የክፉ ፡ አብነት ፡ ሲሆን ፡ እኔማ ፡ ምን ፡ ዕዳዬ ፡ ለርሱ ፡ ይበሰው ፡ እንጂ ፡ አለው ፡ ቀ ድሞ ፡ ነቢያት ፡ ዘመነ ፡ ሣህል ፡ ወር ኃ ፡ ሰላም ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ኩፋር ፡ ለብሰ ው ፡ ኩፋር ፡ ጠምጥመው ፡ በአምባሳ ይ ፡ ፈረስ ፡ ተቀምጠው ፡ መነሳንስ ፡ ይዘው ፡ ይታያሉ ፤ ዘመነ ፡ ፀብዕ ፡ ወ ርኀ ፡ ጎዘን ፡ ነው ፡ ሲሉ ፡ ከል ፡ ለብሰ ው ፡ ከል ፡ ጠምጥመው ፡ ዘገር ፡ ይዘ ው ፡ ይታያሉ ፤ በዚህ ፡ ልማድ ፡ እን ዲህ ፡ ሆኖ ፡ ሄደ ፡ ሰላምኑ ፡ ። ምጽአ ትከ ፡ ነቢየ ፡ እግዚአብሔር ፡ አመጣ ጥህ ፡ ለደህና ፡ ነውን ፡ አለው ፤ ደህና ስ ፡ ደህና ፡ ነኝ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጥቂት ፡ ነገር ፡ እነግርህ ፡ ብዬ ፡ አለው ፡ ንገረኝ ፡ አለ ው ፡ በዚህ ፡ በከተማህ ፡ ሁለት ፡ ሰዎ ች ፡ አሉ ፤ አንዱ ፡ ባለፀጋ ፡ አንዱ ፡

ድኃ ፡ ለባለፀጋው ፡ መቶ ፡ በጕች ፡ አ
ሉት ፡ ለድኃው ፡ አንዲት ፡ በግ ፡ አለ
ችው ፡ እምዘበልዐ ፡ ያበልዓ ፡ ወእም
ዘሰትየ ፡ ያሰትያ ፡ ከበላው ፡ ያበላታ
ል ፡ ከጠጣው ፡ ያጠጣታል ፡ ካጠገቡ ፡
ያስተኛታል ። ወይሬእያ ፡ ከመ ፡ ወለ
ቱ ፡ እንደልጁ ፡ ያያታል ። እንዲህ ፡
ሲለው ፡ ያውቅበታል ። አንድም ፡ ከ
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የተለየበት ፡ ወራት ፡
ነውና ፡ አያውቅበትም ። አደራ ፡ አስ
ጠብቆት ፡ ሄዶ ፡ እንግዳ ፡ ቢመጣበ
ት ፡ መቶ ፡ በጎች ፡ እያሉት ፡ ከመንጋ
ው ፡ ያንሱብኛል ፡ ከቍጥር ፡ ይጐሉብ
ኛል ፡ ብሎ ፡ አንዲቱን ፡ የድኃ ፡ በግ ፡
አርዶ ፡ አወራርዶ ፡ እንግዳውን ፡ ሸኘ
በት ። እርሱንም ፡ ለሰው ፡ ይነግርብ
ኛል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያዳኝብኛል ፡
ብሎ ፡ ገደለው ። በዚህ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ አዝኗል ፡ አለው ። ዳዊትም ፡
ተቈጣ ። ሕያው ፡ እግዚአብሔርን ፡ የ
ጦር ፡ ምሳ ፡ እንዳደርገው ፡ ህየንተ ፡
አሐቲ ፡ በግዕት ፡ ይትፈደይ ፡ ትርብዕ
ተ ፡ ወህየንተ ፡ አሐቲ ፡ ላሕም ፡ ይትፈ
ደይ ፡ ትሕምስተ ፡ ዘፀ ፡ ፳፪ ፡ ፩ ። በጠፋ
ውም ፡ ገንዘብ ፡ ባንድ ፡ አራት ፡ አምስ
ት ፡ ይከፈላል ፡ አለው ። ፩ ፡ ሳሙ ፡ ፲፪ ፡ ፩-፮
አንጉሥ ፡ ፈታሕከ ፡ በርእስከ ፡ አኮኑ ፡
አንተ ፡ ገባሪሁ ፡ ለዝ ፡ ኵሉ ፡ ንጉሥ ፡
በራስህ ፡ ፈረድህ ። ይህን ፡ ሁሉ ፡ ያ
ደረግህ ፡ አንተ ፡ ነህ ። አንተ ፡ ገበር
ከ ፡ በጎቡዕ ፡ ወእነ ፡ እከሥቶ ፡ በቅ
ድመ ፡ ዝንቱ ፡ ፀሐይ ፡ አንተ ፡ በስው
ር ፡ ያደረግሁት ፡ ይመስልሃል ። እኔ ፡
ግን ፡ በጣይ ፡ በጉባይ ፡ እንዲሉ ፡ በጉ
ባዔ ፡ እገልጽብሃለሁ ፡ ብሏል ። ባለ
ፀጋ ፡ የተባልህ ፡ አንተ ፡ ነህ ። ድኃ ፡
የተባለ ፡ አርዮ ፡ ነው ። መቶ ፡ በጎች ፡
የተባሉ ፡ አሥሩ ፡ ዕቁባቶችህ ፡ ናቸ
ው ። አንዲት ፡ በግ ፡ የተባለች ፡ ቤር
ሳቤህ ፡ ናት ። እንግዳ ፡ የተባለ ፡ ፊቃ
ደ ፡ ሥጋ ፡ ነው ። ፊቃደ ፡ ሥጋ ፡ ቢኑ
ሣብህ ፡ አሥር ፡ ዕቁባት ፡ እያሉህ ፡
በአንዲት ፡ በኦርዮ ፡ ሚስት ፡ በቤርሳ
ቤህ ፡ ደረስህ ። እሱንም ፡ ለሰው ፡ ይ
ነግርብኛል ። ለእግዚአብሔር ፡ ያዳ
ኝብኛል ፡ ብለህ ፡ አስገደልከው ። በ
ዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ አዝኖብሃል ፡
አለው ። ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፪ ፡ ፯-፲፩ ።

ከእግዚአብሔርማ ፡ ተጣልቼ ፡ የም
ወጣበት ፡ ቀዳዳ ፡ የምሮጥበት ፡ ሚዳ ፡
የምንጠለጠልበት ፡ ቅጠል ፡ የምጠ
ጋበት ፡ ገደል ፡ የምመክተው ፡ ጋሻ ፡
የምሠወርበት ፡ ዋሻ ፡ የለኝ ። ምን ፡
ይበጀኛል ፡ እያለ ፡ ከእግሩ ፡ በታ
ች ፡ ይወድቅ ፡ ይነሣ ፡ ጀመረ ። መር
ዙንማ ፡ ነግሬ ፡ መድኃኒቱን ፡ ሳል
ነግርህ ፡ እቀራለሁን ። ንስሐ ፡ ብትገ
ባ ፡ ይቅር ፡ ይልሃል ፡ አለው ። በዚህ ፡
ጊዜ ፡ ጉድጓድ ፡ ምሶ ፡ አመድ ፡ ነስን
ሶ ፡ ማቅ ፡ ምንጣፍ ፡ ለብሶ ፡ ጕበ
ቶ ፡ ተናግሮታል ። ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፪ ፡ ፲፪-፲፫ ።
አቤቱ ፡ ሰብአ ፡ ትካትን ፡ ባጠፋህበ
ት ፡ መዓትህ ፡ አታጥፋኝ ። ዘፍ ፡ ፯ ፡
፲፯ - ፳፬ ።

ወበመቅሠፍትከ ፡ ኢትገሥፀኒ ።
ሰብአ ፡ ሰዶም ፡ ሰብአ ፡ ገሞራን ፡ ባ
ጠፋህበት ፡ መዓትህ ፡ ፡አታጥፋኝ ።
ዘፍ ፡ ፲፱ ፡ ፳፬- ፳፭ ።
አንድም ፡የጉልማሳ ፡ሚስት ፡ነሣ ፡ጉ
ልማሳ ፡ገደለ ፡ብለህ ፡አታጥፋኝ ።
፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፩ ፡ ፬-፲፮ ።
አንድም ፡ በነፍስ ፡ በሥጋ ፡ አታጥ
ፋኝ ፡ ለማለት ፡ ደጋገመው ።
፪ ፡ ተማሃለኒ ፡ እግዚኦ ፡ እስመ ፡ ድውይ
እ ነ ።
አቤቱ ፡ ድውየ ፡ ኃጢአት ድውየ ፡
ንስሐ ፡ነኝና ፡ ይቅር ፡ በለኝ ፡ ማረኝ ።
ወፈውሰኒ ፡ እስመ ፡ ተሀውካ ፡ አዕዕምትየ

ሥጋዬም ፡ ባለመከራ ፡ ሆኗልና ፤ አ
ድነኝ ።
፫ ፤ ነፍስየኒ ፡ ተሀውከት ፡ ፈድፋደ ።

ነፍሴም ፡ ፈጽማ ፡ ባለመከራ ፡ ሆናለ
ችና ፡ አንድም ፡ (ወፈውሰኒ ፡ እስመ ፡
ተሀውካ ፡ አዕዕምትየ) ፡ ነፍሴም ፡ ባለ
መከራ ፡ ሆናለችና ፡ አዕም ፡ በሥጋ ፡
ተሠውሮ ፡ ለሥጋ ፡ ኃይል ፡ ፅንዕ ፡ እን
ዲሆን ፡ ነፍስም ፡ በሥጋ ፡ ተሠውራ ፡
ለሥጋ ፡ ኃይል ፡ ፅንዕ ፡ ትሆናለችና ፡
ዓዕም ፡ አላት ፡ ዓቃቤ ፡ ሥራይ ፡ ኀሥ
ሥ ፡ ፈውሰ ፡ ለሥጋከ ፡ ወሥራየ ፡ ለ
አዕዕምቲከ ፡ እንዲል ።
(ነፍስየኒ ፡ ተሀውከት ፡ ፈድፋደ) ፡ ሥ
ጋዬም ፡ ባለመከራ ፡ ሆናለች ።
ወአንተኒ ፡ እግዚኦ ፡ እስከ ፡ ማዕዜኑ ።

አንተም ፡ እንደሰው ፡ መች ፡ ይረዳኛ
ል ፡ የሚሉህ ፡ ሆንህን ፡ ሰውን ፡ እር
ዳኝ ፡ ያሉት ፡ እንደሆነ ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡
በዚህ ፡ ወር ፡ በዚህ ፡ ዓመት ፡ ይላል
ና ። አንድም ፡ አንተም ፡ እንደሰው ፡
አንዠተ ፡ ጽኑ ፡ ሆንህን ። አንድም ፡
ካንተማ ፡ ጋራ ፡ ተጣልቼ ፡ እስከ ፡ መ
ቼ ፡ ድረስ ፡ ነዋ ። ሰው ፡ የሆነ ፡ እንደ
ሆነ ፡ ሲሞት ፡ ሲሻር ፡ አርፈዋለሁ ፡
ይበላል ፡ ሲሞት ፡ አርፈዋለሁ ፡ እንዳ
ልልህ ፡ በባሕርይህ ፡ ሞት ፡ የለብህ ፡
ሲሻር ፡ አርፈዋለሁ ፡ እንዳልልህ ፡ በ
መንግሥትህ ፡ ጎልፈት ፡ ሽረት ፡ የለ
ብህ ።

፬ ፤ ተመየጥ ፡ እግዚኦ ፡ ወባልሃ ፡ ለነፍስየ

እንዲህ ፡ ነውና ፡ አቤቱ ፡ ከመዓት ፡
ወደ ፡ ምህረት ፡ ከቁጣ ፡ ወደ ፡ ትዕግ
ሥት ፡ ተመልሰህ ፡ ነፍሴን ፡ አድናት ።

ወአድኅነኒ ፡ በእንተ ፡ ምሕረትከ ።

ስምየኒ ፡ መሐሪ ፡ ወመስተሣህል ፡ ስ
ላልህ ፡ በስምህ ፡ ስለአመንኩ ፡ ስምህ
ን ፡ አማላጅ ፡ ስለአደረግህ ፡ አድነኝ ።
፮ ፤ እስመ ፡ አልቦ ፡ በውስተ ፡ ሞት ፡
ዘይዜከረከ ።
ከሞት ፡ በኋላ ፡ ዝናም ፡ ለዘር ፡ ጠል ፡
ለመከር ፡ ስጠኝ ፡ ብሎ ፡ የሚለምን
ህ ፡ የለምና ።

ወበሲኦልኒ ፡ መኑ ፡ የአምነከ ።

በመቃብርም ፡ ልብስ ፡ ጉርስ ፡ ስጠኝ ፡
ብሎ ፡ የሚያመሰግንህ ፡ የለምና ፡ እ
መኖ ፡ ወልድየ ፡ እንዲል ፤ አእዩቶ
ሲል ፡ ነው ፤ አንድም ፡ አልቦና ፡ መ
ኑ ፡ ይመራረሳሉ ፡ እስመ ፡ መኑ ፡ ዘ

ዜነዎ ፣ መኑ ፣ ዘይክል ፣ ነቢበ ፣ ዕበ የኪ ፣ እንዲል ፤ (እስመ ፣ አልቦ ፣ በ ውስተ ፣ ሞት ፣ ዘይዜከረከ ፣ ወበሲ አልኒ ፣ (መኑ) ፣ አልቦ ፣ ዘየአምነከ ፣ ከሞተ ፣ በኋላ ፣ በመቃብር ፣ ዝናም ፣ ለዘር ፣ ጠል ፣ ለመከር ፣ ልብስ ፣ ጉ ርስ ፣ ስጠኝ ፣ ብሎ ፣ የሚያመሰግንህ ፣ የለምና ፣ ኑሬ ፣ አመሰግንህ ፣ ዘንድ ፣ አድነኝ ፣ እንጂ ። እኔማ ፣ ከሌለሁ ፣ የ ሚያመሰግንህ ፣ ማነው ፣ በዚህም ፣ መ ጻሕፍት ፣ ተባብረውበታል ፤ ሲራክ ፣ መኑ ፣ ዘይሴብሖ ፣ ለልዑል ፣ በውስተ ፣ መቃብር ፣ ብሎ ። ሲራ ፣ ፲፯ ፣ ፳፯ ። ዮ ሐንስ ፣ ኤጲስ ፣ ቆጶስ ፣ ዘኢየሩሳሌም ፣ መኑ ፣ ዘይሴብሖ ፣ ለእግዚአብሔር ፣ እምዓላውያን ፣ በእንተ ፣ ዓሊዎታ ፣ ለነፍሱ ፣ ብሏል ።

፯ ፤ ሠራኅኩ ፣ በምንዳቤየ ።

ወድኀ ፣ በሠራሁት ፣ ሥራ ፣ ጠፋሁ ።

ወአኀዝብ ፣ ዝሉፉ ፣ ሌሊተ ፣ ዓራትየ ።

በሌሊት ፣ አልጋዬን ፣ አፀብኩ ።

ወበአንብዕየ ፣ አርኀስኩ ፣ ምስካብየ ።

በዕንባዬ ፣ መኝታዬን ፣ አራስኩ ። አሁ ን ፣ ጉድጓድ ፣ ምሰ ፣ አመድ ፣ ነስንሰ ፣ ማቅ ፣ ለብሰ ፣ ንስሓ ፣ ገባ ፣ ብሎ ፣ አል ነበረምን ፣ ቢሉ ። ንጉሥ ፣ የተቀመ ጠበት ፣ ሁሉ ፣ ዙፋን ፣ ይበላልና ። እንድም ፣ ሥርዓተ ፣ (ዓራተ) ፣ መን ግሥት ፣ አይጥፋ ፣ ብለው ፣ ድንክ ፣ አልጋ ፣ አስቀምጠውለት ፣ ነበር ። ያን ፣ ተጠግቶ ፣ ሲያለቅስ ፣ ዕንባው ፣ እየ ተፈነጠቀ ፣ ይረጪው ፣ ነበርና ፣ እን ዲህ ፣ አለ ። የዕንባውንም ፣ መጠን ፣ ከዚህ ፣ ይናገሩታል ። ተቀምጦ ፣ ሲያ ለቅስ ፣ ክንድ ። ቆሞ ፣ ሲያለቅስ ፣ ስን ዝር ፣ ከመሬት ፣ ይገባ ፣ ነበር ፤ ይህ ም ፣ ሊታወቅ ፣ በእንባው ፣ የበቀለ ፣ ሰርዶ ፣ ሰውነቱን ፣ ተብትቦ ፣ ይዘት ፣ ብላቴኖቹ ፣ በመቀስ ፣ እያረሩ ፣ አው ጥተውታል ፣ ይላሉ ፤ ይኸውም ፣ በ ዜና ፣ እስክንድር ፣ ታውቋል ።

፰ ፤ ወተሀውክት ፣ እመዓት ፣ ዓይንየ ።

ሰብአ ፣ ትካትን ። ሰብአ ፣ ሰዶም ። ሰብአ ፣ ገሞራን ፣ ባጠፋህበት ፣ መዓትህ ፣ ታጠ ፍኝ ፣ ይሆን ፣ ከማለቴ ፣ የተነሣ ፣ ዓይኔ ፣ ባከነች ። እንደ ፣ ሴት ፣ እንደ ፣ ልጅ ፣ ጨንገር ፣ ያነሱበቸው ፣ እንደሆነ ፣ ከ አሁን ፣ አሁን ፣ ጣሉብን ፣ ይሆን ፣ እያሉ ፣ ዓይናቸው ፣ እንዲባክን ። አን ድም ፣ ከመፍረድህ ፣ የተነሣ ፣ ሰው ነቴ ፣ በለመከራ ፣ ሆነች ፤ አንድም ፣ (እመዓተ ፣ አንብዕየ ፣ ወይንየ) ፣ ይላል ፤ ከቀጡ ፣ ዕንባዬ ፣ የተነሣ ፣ ዓይኔ ፣ ሠለተ ፤ ቁጡ ፣ ዕንባ ፣ ፈት ፣ ያንጣ ጣል ፣ ቅንድብ ፣ ይመልጣልና ፣ እን ዲህ ፣ አለ ።

ወበለይኩ ፣ በጎበ ፣ ዝሉሙ ፣ ጸላዕትየ ።

በጠላቶቼ ፣ ሁሉ ። ዘንድ ፣ ጠፋሁ ፤ ወበልየ ፣ ነገር ። እምአፉክሙ ፣ እን ዲል ። ሰለሁ ፣ እንደሌለሁ ፣ ሰልሞት ፣ እንደሞትኩ ፣ ሆንሁ ።

፮ ፤ ረኃቁ ፡ እምኔየ ፡ ዘልክሙ ፡ ኅበርተ ዓመግ ። ማቴ ፡ ፭ ፤ ፳፫ ።
ጉልማሳ ፡ ገደለ ፡ የጉልማሳ ፡ ሚስት ነሣ ፡ እያላችሁ ፡ ከፈጣሪዬ ፡ ጋራ ፡ የምታጣሉኝ ፡ (አጋንንት) ፡ ከኔ ፡ ራቁልኝ ።
እስመ ፡ ሰምኣኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃለ ፡ ብካይየ ።
እግዚአብሔር ፡ አልቅሼ ፡ የለመንሁትን ፡ ልመናዬን ፡ ሰምቶኛልና ።

፱ ፤ ሙተወክፈ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስእለትየ
እግዚአብሔር ፡ ልመናዬን ፡ ሰምቶኛልና ፥ ናታን ፡ ነቢዩ ፡ መጥቶ ፡ ተግደዋ ፡ ለኃጢአትከ ፥ በነፍስህ ፡ ይቅር ብሎሃል ፥ በሥጋህ ፡ ግን ፡ ኃጢአት ፡ ያለፍዳ ፡ አይነፃምና ፥ ከአብራክህ ፡ የተከፈለ ፡ ልጅህ ፡ መንግሥትህን ፡ ይቀማሃል ፡ እዋጋለሁ ፡ አትበል ፡ ብሎ ታል ። ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ። በምንት ፡ አአምር ፡ ከመ ፡ ይከውን ፡ ዝንቱ ፤ ይህ ፡ እንዲደረግ ፡ በምን ፡ አውቃለሁ ፡ አለው ፤ የተፀነሰው ፡ ብላቴና ፡ ይሞታል ። ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፪ ፡ ፲፬ ። እሷን ፡ አግባት ፥ ንጉሥ ፡ የደረሰበትን ፡ አንበሳ ፡ የሰበረውን ፡ የሚደፍረው ፡ የለምና ፤ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ትወልድልሃለች ፡ ስሙንም ፡ ሰሎሞን ፡ በለው ፤ ሰሎሞንም ፡ ማለት ፡ መስተሳልም ፡ ማለት ፡ ነው ፤ ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፩ ፡ ፳፭ - ፳፮ ። ያም ፡ ብላቴና ፡ ታመመ ፤ ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፪ ፡ ፲፭ ። ዳዊትም ፡ እንደገና ፡ ጉድጓድ ፡ ምሶ ፥ አመድ ፡ ነስንሶ ፥ ማቅ ፡ ለብሶ ፡ ሱባዔ ፡ ገባ ፤ ስለምን ፡ ቢሉ ፥ ግደልልኝ ፡ ብሎ ፡ ዳዊትን ፡ ያህል ፡ ሰው ፡ ልጄን ፡ ግደልልኝ ፡ ብሎ ፡ አያመለክትም ፡ ብሎ ፡ እኔን ፡ በነፍሴ ፡ ይቅር ፡ እንዳልከኝ ፡ ብላቴናውንም ፡ በሥጋው ፡ ይቅር ፡ በለው ፡ ብሎ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ብላቴናው ፡ ሞተ ፥ ታመመ ፡ ብንለው ፡ ሱባዔ ፡ የገባ ፡ ሞተ ፡ ብንለውማ ፡ ዮጊ ፡ ይገብር ፡ እኩየ ፡ ዲበ ፡ ነፍሱ ፤ በገዛ ጦሩ ፡ ተወግቶ ፡ ይሞት ፡ የለምን ፡ ብለው ፡ ቀስ ፡ ቀስ ፡ እያሉ ፡ ሲጨዋወቱ ፡ ሰምቶ ፡ ያ ፡ ብላቴና ፡ ሞትን ፡ አላቸው ፤ አዎን ፡ አሉት ፡ ከሞተማ ፡ ብሎ ፡ በሱባዔ ፡ ጊዜ ፡ የለበሰውን ፡ ጥሎ ፡ ልብሰ ፡ መንግሥት ፡ ለብሶ ፡ ከአዳራሽ ፡ ተገኝላቸው ፤ ግብር ፡ ምላሽ ፡ ሲሆን ፡ መኳንንቱ ፡ ተመራርጠው ፡ ገብተው ፤ ንጉሥ ፡ ፍርድ ፡ ልበስ ፡ ሥርዓት ፡ ተለወጠብን ፡ ጥንቱን ፡ ለልማዱ ፡ ሰው ፡ ሲሞት ፡ አጥብቆ ፡ ይታዘንለታል ፡ ይለቀስለታል ፤ አንተ ፡ ግን ፡ ታመመ ፡ ብንልህ ፡ ያን ፡ ያህል ፡ መከራ ፡ ተቀበልክ ፥ ሞተ ፡ ብንልህ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ አደረግህ ፡ አሉት ፤ ምን ፡ ላድርግ ፡ እኛ ፡ ወደሱ ፡ እንሄዳለን ፡ እንጂ ፡ እሱ ፡ ወደኛ ፡ ይመጣልን ፥ ይገብዕኑ ፡ ማይ ፡ ድኅረ ፡ ተክዕወ ፥ ወሀ ፡ ከፈሰሰ ፡ ይታፈሳልን ፥ ወፍስ ፡ ከበረረ ፡ ይያዛልን ፤ አላቸው ፡ ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፪ ፡ ፲፭ - ፲፫ ።
ወተወክፈ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸሎትየ ።
እግዚአብሔር ፡ ልመናዬን ፡ ተቀብሎኛልና ፥ አንድም ፡ (ረኃቁ ፡ እምኔየ ፡

ኵልክሙ ፡ ገበርተ ፡ ዓመፃ) ። ዕፀ ፡ በለ ስን ፡ በላ ፡ እያላችሁ ፡ ከፈጣሪዬ ፡ ጋራ ፡ የምታጣሉኝ ፡ አጋንንት ፡ ከኔ ፡ ራቁ ልኝ ። (እስመ ፡ ሰምዓኒ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ቃለ ፡ ብካይየ) ፤ እግዚአብ ሔርአልቅሼ ፡ የለመንኩትን ፡ ልመና ዬን ፡ ሰምቶልኛልና ።

፲ ፤ ለይትኃፈሩ ፡ ወይኅሠሩ ፡ ኵሎሙ ፡ ጸላዕተ ፡ ዮ ። ጠላቶቼ ፡ ሁሉ ፡ ይፈሩ ፡ ይዋረዱ ።

ለይግብኡ ፡ ድኅሬሆሙ ፡ ወይትኃፈሩ ፡ ፈድፋደ ፡ ፍጡነ ። አድኅ ፡ አነስ ። አድሮ ፡ አነስ ፡ ይኹኑ ። ፈጽመው ፡ ፈጥነው ፡ ይፈሩ ፡ ይዋ ረዱ ።

መዝሙር ፡ ፯ ።

፩ ፤ እግዚኦ ፡ አምላኪየ ፡ ብከ ፡ ተወከ ልኩ ፡ ኢትግድፈኒ ።

ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ርእሱ ። ነው ። በአቤሴሎም ፡ ጊዜ ፡ ስለራሱ ፡ ተናግ ሮታል ። ታሪኩ ፡ እግዚአ ፡ ሚበዝ ኁ ፡ እለ ፡ ይሣቅዩኒ ፡ ካለው ፡ የተያ ያዘ ፡ ነው ፤ በአርእስቱ ፡ በእንተ ፡ አኪጦፌል ፡ የሚል ፡ ይገኛል ፤ ይህ ስ ፡ እንደምን ፡ ነው ፡ ቢሉ ። ተራ ፡ ጫማ ፡ ተጫምቶ ፡ ነጠላ ፡ ልብስ ፡ ለ ብሶ ፡ ከቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ወጥቶ ፡ ጥቂት ፡ እልፍ ፡ ብሎ ፡ ሰፈረ ። ስለ ምን ፡ ቢሉ ፤ ሠራዊት ፡ እስኪከተት ለት ፡ ድረስ ። ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፭ ፡ ፲፬-፲፰ ።

ካህናቱ ፡ ሳዶቅ ፡ አብያታር ፡ ታቦተ ፡ ጽዮንን ፡ ይዘው ፡ መጥተው ፡ ከፍ ፡ ካለ ፡ ከትይዩ ፡ ቦታ ፡ ሰፈሩ ። ስለም ን ፡ ቢሉ ። ካህናት ፡ ፈሊጥ ፡ አዋቆ ች ፡ ናቸውና ፡ አይቶ ፡ ተመለሱ ፡ ይ ለናል ፡ ብለው ። አንድም ፡ ስንኳን ፡ ንጉሥና ፡ ማናቸውም ፡ ሰው ፡ ቢሆ ን ፡ ከቤቱ ፡ ከወጣ ፡ ብዙ ፡ የማይገ ባው ፡ ይከተለዋልና ፡ እንዳይነካኩ ።

፪ ፡ ሳሙ ፤ ፲፭ ፡ ፴፩ ። አይቶ ፡ እሊህ ፡ እለማ ናቸው ፡ አለ ። ካህናቱ ፡ ሳዶቅ ፡ አብ ያታር ፡ ታቦት ፡ ጽዮንን ፡ ይዘው ፡ መጥተዋል ፡ አሉት ። እንደወጣሁስ ብቀር ፡ የሚነግረው ፡ ልጄ ፡ አይደ ለምን ። ከቦታዋ ፡ ለምን ፡ አወጣች ኋት ። ይልቅስ ፡ ጧት ፡ ማታ ፡ የተመ ከረውን ፡ ላኩብኝ ። ፈጣሪዬ ፡ ለመ መለስ ፡ ቢያበቃኝ ፡ ውለታችሁን ፡ አላጠፋም ፡ እከፍላለሁ ፡ አላቸው ። ትላንቱን ፡ ሴት ፡ ጌትያዊ ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ራሱን ፡ ሆኖ ፡ አድሮለት ፡ ነበ ረና ፡ ጥቂት ፡ እልፍ ፡ ሲል ፡ አገኘ ው ። አንተሳ ፡ ለምን ፡ መጣህ ፡ በመ ንግሥት ፡ ሳለሁ ፡ አልተሾምህ ፡ አ ልተሸለምህ ፡ በመከራ ፡ ጊዜ ፡ ትከ ተለኛለህን ። ይልቅስ ፡ ሕፃን ፡ ንጉ ሥ ፡ ነግሦልሃልና ፡ ሂደህ ፡ ተሾም ፡ ተሸለም ፡ አለው ። አሕዛብ ፡ በገንዘ ብ ፡ ምኩሐን ፡ ናቸውና ፡ እኔ ፡ ሹመ ት ፡ ሽልማት ፡ ሽቼ ፡ መች ፡ መጣሁ ።

እንተን ፣ ጌታዬን ፣ ብዬ ፣ ነው ፣ እን
ጂ ፣ አለው ፤ ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፭ ፡ ፳፭ ።
ሁለተኛም ፡ ኩሲ ፣ አረጋዊን ፣ አገ
ኘው ፣ አንተስ ፣ ለምን ፣ መጣህ ፣ አ
ለው ፤ ሞትህን ፣ ሞት ፤ ሕይወትህን ፣
ሕይወት ፣ አደርግ ፣ ብዬ ፣ አለው ፤
አንተስ ፣ ትከውነኒ ፣ ያረ ፣ ክቡደ ፤
አንተስ ፣ ዕኑ ፣ ሽክም ፣ ትሆንብኛለ
ህ ፤ ጥዬህ ፣ አልሄድ ፣ አንተን ፣ ሳስ
ዘግም ፣ ከመያዝ ፣ እደርስ ፣ የለምን ፤
ይልቅስ ፣ ሽማግሌ ፣ ከምክር ፣ አይለ
ያምና ፤ የተመከረውን ፣ ለካህናቱ ፣
ንገራቸው ፣ ይልኩብኛል ፣ አለው ።
፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፭ ፡ ፳፪-፴፯ ።
ከዚህ ፣ በኋላ ፣ አቤሴሎም ፣ ነጋሪቱን ፣
እያስጐሰመ ፣ ከከተማ ፣ ገብቶ ፣ ምክ
ሩ ፣ ምክረ ፣ ዘንገብር ፣ ኢዮአብ ፣ አ
ቢሳን ፣ ዳዊትን ፣ ያህል ፣ ጠላት ፣ ከመ
ንግሥት ፣ አስወጥተን ፣ ሰደን ፣ ዝም
ትላላችሁን ፤ የምንሠራውን ፣ ምከሩ
አላቸው ፤ አኪጦፌል ፣ አሁን ፣ አባት
ና ፣ ልጅ ፣ ፊት ፣ ተጣቄሩ ፣ ብለን ፣ እ
ንመክራለንን ፣ ዕገሌ ፣ እንዲህ ፣ ብሎ ፣
ነበር ፤ እገሌም ፣ እንዲህ ፣ ብሎ ፣ ነበ
ር ፣ እያላችሁ ፣ ነገራችንን ፣ ፌዝ ፣ ለ
ማድረግ ፣ ነው ፣ እንጂ ፣ ይልቅስ ፣ ቍ
ርዕ ፣ ነገር ፣ ሥራ ፣ አለው ፣ ከመንግ
ሥት ፣ አስወጥቶ ፣ ከመስደድ ፣ የበለ
ጠ ፣ ፀብ ፣ አለን ፣ አለው ፤ እንኪያስ ፣
ባዕ ፣ ኅበ ፣ ዕቁባቲሁ ፣ ዘኃደጎን ፣
ከመ ፤ ይዕቀባ ፣ ቤቶ ። ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፭-
፲፮ ። ዕቁባቱ ፣ ቢከተሉት ፣ እላንተን
ማ ፣ ምን ፣ ያደርጋችኋል ፣ ተመልሳች
ሁ ፣ ከተማውን ፣ ጠብቁ ፣ ብሎ ፣ መል
ሷቸው ፣ ነበርና ፣ ገብተህ ፣ በግብር ፣
እወቃቸው ፤ ከዚህ ፣ በኋላ ፣ ዮኤል ፣
በቃላቸው ፣ ከመምከር ፣ በእጃቸው ፣
ከመግደል ፣ አያርፉም ፣ አለው ። ድ
ንኳን ፣ አስተክሎ ፣ ባዳራሽ ፣ እያገባ ፣
ተጨዋውቶ ፣ በእልፍኝ ፣ እያስወጣ ፣
ስድዷቸዋል ። ዘሌ ፡ ፳ ፡ ፲፩ ። ነገሩን ፣ እ
ንደተቀበለለት ፣ አይቶ ፣ መቸስ ፣ አን
ተ ፣ የምትሻው ፣ የአባትህን ፣ ቸብቸ
በ ፣ አይደለምን ፣ አለው ፤ እንግዲ
ያ ፣ ምን ፣ እሻለሁ ፣ አለው ፤ ሀበኒ ፣
ዕልፈ ፣ ወሷየ ፣ እምሕዝበ ፣ ፳ኤል ፣ ካ
ሥራ ፣ ሁለቱ ፣ ነገደ ፣ እሥራኤል ፣ ዕል
ፍ ፣ ከኹለት ፣ ሽህ ፣ ጦር ፣ ስጠኝ ፣ የምት
ሻውን ፣ ያባትህን ፣ ቸብቸቢ ፣ ቁርጩ ፣
አመጣልሃለሁ ፣ አለው ። ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፯
፳፩-፳፪ ። ፲፯ ፣ ፩-፬ ። አቤሴሎምም ፣ እ
ስኪ ፣ ባአደባባይ ፣ ሽማግሌ ፣ እንዳ
ለ ፣ እዩ ፣ አለ ፤ ኩሲ ፣ አረጋዊ ፣ አለ ፣
አሉት ፤ አስጠርቶ ፣ አንተ ፣ ዳዊት ፣
ወዳጅህ ፣ አልነበረምን ፣ አለው ፤ እ
ውነት ፣ እንጂ ፣ ወዳጄ ፣ ነው ፣ አለው ፤
እንኪያ ፣ ለምን ፣ ቀረህ ፣ አለው ፤ ማ
ን ፣ ነገሠ ፣ ብዬ ፣ እሄዳለሁ ፤ ጥንቱን
ም ፣ አባት ፣ ሲሞት ፣ ልጅ ፣ ሲተካ ፣
ነው ፤ እሱን ፣ እንዳገለገልሁ ፣ አንተ
ን ፣ አገለግላለሁ ፣ ብዬ ፣ ቀረሁ ፣ አለ
ው ፤ ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፮ ፡ ፲፱-፳፱ ። እንኪያስ ፣
ምከር ፣ አለው ፣ ቆይታ ፣ ካደረጋች
ሁ ፣ ምክር ፣ ከጀመራችሁ ፣ ብዙ ፣ (አ

ያሌ)፡ ጊዜ ፡ ነው ፤ ነገሩን ፡ አልበላሁት ፡ ምን ፡ ብዬ ፡ እመክራለሁ ፡ አለው ፡ ከመ ፡ ከመዝ ፡ መከረ ፡ አኪጦፌል ፡ አኪጦፌል ፡ እንዲህ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መከረ ፡ አለው ፤ ምክርከሙ ፡ አሐቲ ፡ ወእኪት ፡ ይእቲ ፡ ምክራችሁ ፡ አንዲት ፡ ናት ፤ ያችውም ፡ የፀናች ፡ ናት ፤ እኪትን ፡ አይሻም ፡ ዳዊት ፡ አባትህን ፡ ታውቀዋለህ ፡ የዕልፍ ፡ ጌታ ፡ ነው ፤ የጦር ፡ አበጋዞቹ ፡ ኢዮአብ ፡ እቢሳን ፡ ታውቃቸዋለህ ፡ የሺህ ፡ የሺህ ፡ ጌቶች ፡ ናቸው ፤ አሁን ፡ በዚህ ፡ በደም ፡ አፍሳሽ ፡ በሥብ ፡ አጢያሽ ፡ ካህን ፡ እጅ ፡ ይያዛል ፡ ብለህ ፡ ነውን ፡ እንዲያው ፡ ጦሩን ፡ ቅሞት ፡ ይቅር ፡ ብለህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እንደኔስ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ከዳን ፡ እስከ ፡ ቤርሳቤህ ፡ ያሉ ፡ አሥራ ፡ ሁለቱ ፡ ነገደ ፡ ፀኤል ፡ እስከ ፡ ፫ ፡ ወር ፡ ይሰብሰቡ ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ኰከብ ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ አሸዋ ፡ ይብዙ ፡ ኣንተስ ፡ ቀርተህ ፡ ምን ፡ ሥራ ፡ ሊሠራ ፡ ነው ፤ ወላጅቱ ፡ ከቤት ፡ ኣዋላጅቱ ፡ ከሜዳ ፡ እንዲሉ ፡ አንተ ፡ በፊት ፡ በፊት ፡ እኛ ፡ በኋላ ፡ በኋላ ፡ ሁነን ፡ እንገሠግሰለን ፤ ከተራራ ፡ ላይ ፡ ያገኘናቸው ፡ እንደሆነ ፡ በኃብል ፡ ስበን ፡ ካሸዋ ፡ እንቀላቅላቸዋለን ፤ ከሜዳ ፡ ላይ ፡ ያገኘናቸው ፡ እንደሆነ ፡ እንደ ፡ በረድ ፡ እንዘንምበቸዋለን ፡ አለው ፤ መኳንንቱ ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ተያይተዋል ። እምክረ ፡ አኪጦፌል ፡ ይኄይስ ፡ ምክረ ፡ ኩሲ ፡ ብለዋል ፤ መሆኑንስ ፡ ለአቤሴሎም ፡ የአኪጦፌል ፡ ምክር ፡ ይሻለው ፡ ነበረ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ዳዊት ፡ አ ፡ እግዚአ ፡ ዕልዋ ፡ ለምክረ ፡ አኪጦፌል ፡ ሚጣ ፡ ወልጣ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እያለ ፡ ይጸልይ ፡ ነበርና ፤ የኩሲን ፡ ምክር ፡ እንዲቀበልለት ፡ አደረገ ፡ ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፮ ፡ ፴፩ ። ፲፯ ፡ ፲፬ ኩሲም ፡ ለጊዜው ፡ የኔን ፡ ምክር ፡ ተቀብሎኛል ፤ ከዋለ ፡ ካደረ ፡ ግን ፡ የአኪጦፌል ፡ ምክር ፡ ፅኑ ፡ ነው ፤ አሁን ፡ ገብቶ ፡ ያስለውጠዋልና ፤ ኢትቢት ፡ ውስተ ፡ አራቦት ፡ አላ ፡ አፍጥን ፡ ዓዲወ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ከአራቦት ፡ አትዋል ፡ አትደር ፡ ፈጥነህ ፡ ዮርዳኖስን ፡ ተሻገር ፡ ብላችሁ ፡ ላኩበት ፡ ብሎ ፡ ለካህናቱ ፡ ይነግራቸዋል ፤ ካህናቱም ፡ ጽፈው ፡ ለወሀ ፡ ቀጂዎች ፡ ሰጧቸው ። ወሀ ፡ ቀጂዎችም ፡ አኪማሆስና ፡ ዮናታን ፡ አገር ፡ ለመጐብኘት ፡ መጥተው ፡ ነበርና ፡ ሰጧቸው ፤ ተቀብለው ፡ ሲሄዱ ፡ የአቤሴሎም ፡ ወገን ፡ ጠባቂ ፡ አይቶ ፡ ወይ ፡ ከኛ ፡ ወይ ፡ ከነዚያ ፡ አይሆኑ ፡ በመኻል ፡ ለመጐብኘት ፡ ቁመዋል ፡ አለው ፤ ያዟቸው ፡ አያምልጧችሁ ፡ አለ ፤ የዳዊት ፡ ወገን ፡ የምትሆን ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ ነበረች ። ሂደው ፡ ሠውሪን ፡ አሏት ፤ በክረምት ፡ ወሀ ፡ የበላው ፡ ጉድጓድ ፡ አለ ፡ ከዚያ ፡ አስተኝታ ፡ ወሰጥሀት ፡ በሙ ፡ አረፎተ ፡ ወዓረበናተ ፤ ክክም ፡ ፍትግም ፡ ቢሉ ፡ አሰ

ጣችበቸው ፤ በዳውጃ ፡ ጠቀለለቻቸው ፤ ከጋዘና ፡ አገባቻቸው ፤ መጥተው ፡ አኪማሆስና ፡ ዮናታን ፡ ከዚህ ፡ ገብተዋልን ፡ አሏት ፤ መግባትስ ፡ ገብተው ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አሁን ፡ ሄዱ ፡ አለቻቸው ፡ መግባታቸውን ፡ ብታምንላቸው ፡ መውጣታቸውን ፡ አምነውላት ፡ ገብተን ፡ እንይ ፡ ሳይሉ ፡ ሂደዋል ፤ አኪማሆስና ፡ ዮናታንም ፡ በኋላ ፡ ወጥተው ፡ ሄደው ፡ ኢትቢት ፡ ውስጥ ፡ አራቦት ፡ አላ ፡ አፍጥን ፡ ዐዲወ ፡ ዮርዳኖስ ፡ ብሎሃል ፡ ኩሲ ፡ አሉት ፡ ዮርዳኖስን ፡ ተሻግሮ ፡ ከ ወይራ ፡ ስር ፡ ሆኖ ፡ ተናግሮታል ፡

፱ ፡ ሳሙ ፡ ፲፯፡፲፭-፳፪ ።

አቤቱ ፡ ፈጣሪየ ፡ አንተን ፡ አመንኩ ፡ እንዲህም ፡ ከሆነ ፡ በመከራው ፡ አት ጣለኝ ፤ አንድም ፡ በመከራው ፡ እን ዳትጥለኝ ፡ አንተን ፡ አመንሁ ።

ወአድኅነኒ ፡ እምኵሎሙ ፡ እለ ፡ ሮዱኒ ፡ ወባልሐኒ ።

ከከበቡኝ ፡ ጸላቶቼ ፡ ሁሉ ፡ ፈጽመህ ፡ አድነኝ ፡ አድኅኖ ፤ በመከራው ፡ ሳይ ያዙ ፡ (ባልሑ) ፡ ከተያዙ ፡ በኋላ ፡ ነው ፤ (አድኅነኒ) ፡ ከንጉሡ ፡ (ባልሐኒ) ፡ ከ ሠራዊቱ ፡ ነው ።

፱፤ ከመ፡ኢይምሥጥዋ፡ከመ፡አንበሳ፡ለነፍስየ ። እንዘ፡ አልቦ፡ዘያድኅን፡ወዘይባልሕ ፡ነበ ፡ አልቦ ፡ ሲል ፡ ነው ። የሚያድን ፡ ከሌለ ፡ ዘንድ ፡ አንበሳ ፡ ከፀፈቀ ፡ ዱር ፡ ከገደገደ ፡ ምድር ፡ ቆይቶ ፡ ላምን ፡ እንዲነጥቅ ፡ የኔንም ፡ ሰውነት ፡ እለ ፡ አቤሴሎም ፡ እንዳይነጥቃት ።

፲ ፤ እግዚኦ ፡ አምላኪየ ፡ አመሰ ፡ ከመዝ ፡ ገበርኩ ።

አቤቱ ፡ ፈጣሪየ ፡ እንዲህ ፡ እንደሚ ሉኝ ፡ አድርጌ ፡ እንደሆነ ፤ ምን ፡ አ ደረገ ፡ ብለውታል ፡ ቢሉ ፤ የጉልማሳ ፡ ሚስት ፡ ነሣ ፤ ጉልማሳ ፡ ገደለ ፡ ብለ ውታልና ፤ ፪፡ሳሙ ፡ ፲፩፡፬-፲፯ ይህንማ ፡ አድርጎት ፡ የለምን ፡ ቢሉ ፡ በንስሓ ፡ ከታረቅሁ ፡ ብሎ ፡ ዕርቅ ፡ ደም ፡ ያደ ርቅ ፡ እንዲሉ ፡ ፪፡ሳሙ ፡ ፲፪፡፲፫ ። አን ድም ፡ ስንኳን ፡ ንጉሥና ፡ ማናቸው ም ፡ ቢሆን ፡ ሰው ፡ ከቤቱ ፡ ከወጣ ፡ ብዙ ፡ ስም ፡ የሚወጣለት ፡ ስለሆነ ፡ ያላደረገውን ፡ ማማለጃ ፡ በላ ፡ ፍርጁ ፡ አደላ ፡ ብለውታልና ። ፪፡ሳሙ ፡ ፲፮፡፪-፯

ወእመኒ ፡ ዓመፃ ፡ ውስተ ፡ እደውየ ።

በጀ ፡ ነፍስ ፡ መግደል ፤ በቃሌ ፡ መ በደል ፤ በልቡናየ ፡ ቂም ፡ በቀል ፡ ቢኖርብኝ ።

፭ ፤ ወእመኒ ፡ ፈደይክዎሙ ፡ ለእለ ፡ ይፈድዩኒ ፡ እኩየ ።

ክፉ ፡ ላደረጉብኝ ፡ ሰዎች ፡ ክፉ ፡ እን ዳያደርጉብኝ ፡ ክፉ ፡ ላድርግ ፡ ብዬ ፡ እንደሆነ ።

ለያውድቁኒ ፡ ጸላዕትየ ፡ ዕራቅየ ።

ጠላቶቼ ፡ ዕራቁቴን ፡ ይጣሉኝ ፡ ማለ ት ፡ ከሠራዊቱ ፡ ይለዩኝ ፡ ምነው ፡ ተለ ይቶ ፡ የለምን ፡ ቢሉ ፤ እንደተለየሁ ፡ ልቅር ፡ ሰ ል ፡ ነው ፤ አንድም ፡ ከነዚ ሁ ፡ ከጥቂቶቹ ፡ ልለይ ፡ ሲል ፡ ነው ።

፮ ፤ ወይዴግና ፡ ፀራዊ ፡ ለነፍስየ ፡ ወይርከባ ።

ፀራዊ ፡ አቤሴሎም ፡ (አኪጦፌል) ፡

ነፍሴን ፣ ይከተላት ፣ ተከትሎ ፣ ማጣት ፣ አለና ፣ አይጣት ፣ ያግኛት ።

ወይኪዳ ፣ ውስተ ፣ ምድር ፣ ለሕይወትየ።

ሰውነቴን ፣ በዚህ ፣ ዓለም ፣ ያዋርዳት ።

ወያጎሥሮ ፣ ውስተ ፣ መሬት ፣ ለክብርየ ።

ዘውዴን ፣ በዚህ ፣ ዓለም ፣ ያዋርደው።

፮ ፤ ተንሥእ ፣ እግዚኦ ፣ በመዓትከ ።

አቤቱ ፣ በሥራ ፣ በመፍረድ ፣ ተነሣ ።

ወተለዓል ፣ መልዕልቶሙ ፣ ለጸላዕትየ ።

እኔን ፣ አድነህ ፣ ጠላቶቼን ፣ አጥፍተህ ፣ ልዕልናህን ፣ ግለጽ ።

፯ ፤ ተንሥእ ፣ እግዚኦ ፣ አምላኪየ ፣ በሥርዓት ፣ ዘአዘዝከ ። ኢሳ ፣ ፷፫-፷፭ ።

በእንተ ፣ ሥርዓት ፣ ሲል ፤ ነው ፣ የኔስ ፣ የኔ ፣ ነውና ፣ ያዘዝከው ፣ ሥርዓት ፣ ስለፈረሰ ፤ በሥራ ፣ ለመፍረድ ፣ ተነሣ ፤ አቤሴሎም ፣ ሦስት ፣ ሥርዓት ፣ አፍርሷል ፣ ኢትክሥት ፣ ጎፍረተ ፣ ብእሲተ ፣ አቡከ ፣ ዘሌ፲፰፡፰ ። ኢትዕርግ ፣ ምስካበ ፣ አቡከን ፣ ኢትዘሙን ፣ ዘዐ፡፳፡፲፩።ኢትዕርግና ፣ ኢትክሥትስ ፣ አንድ ፣ ነው ፣ ብሎ ፤ አክብር ፣ አባከ ፣ ወእመከ ፣ ያለውን ፣ አፍርሷልና ፣ ዘዐ፡፳፡፲፪። ሦስቱ ፣ ወር ፣ ሲፈጸም ፣ ዳዊት ፣ ጦሩን ፣ በሦስት ፣ ወገን ፣ አድርጎ ፣ ይሰዳል ፤ ኢዮአብን ፣ በንድ ፣ ወገን ፣ አቢሳን ፣ በንድ ፣ ወገን ፤ ሴት ፣ ጌትያዊን ፣ በንድ ፣ ወገን ፣ አድርጎ ፣ ባለቤቱን ፣ አስቀርተውታል ፤ ስለምን ፣ ቢሉ ፣ አፅንተው ፣ ይዋጉናል ፣ ብለው ፣ አንድም ፣ ጌታቸው ፣ ሳይኖር ፣ ድል ፣ አደረጉ ፣ ተብሎ ፣ መከበሪያ ፣ ይሆነናል ፣ ብለው ፣ ፪ ፡ ሳሙ ፲፰ ፡ ፩-፲ ።

ሲያሠማራቸው ፣ አቤሴሎምሃ ፣ ወልድየ ፣ መሀኩ ፣ ልጄን ፣ አቤሴሎምን ፣ ያገኛችሁት ፣ እንደሆነ ፣ አትግደሉብኝ ፣ በሽሽ ፣ አንቃችሁ ፣ አምጡልኝ ፣ አላቸው ፤ ሄደው ፣ ገጠሙ ። እለ ፣ አቤሴሎም ፣ ድል ፣ ሆኑ ፤ ሲሸሽ ፣ የተቀመጠባት ፣ በቅሎ ፣ ይዛው ፣ ወደዱር ፣ ገባች ፤ ወተሰቅለ ፣ ማዕከለ ፣ ሰማይ ፣ ወምድር ፣ ወጎለፈት ፣ በቅል ፣ በታሕቴሁ ፣ ጋንቢሎም ፣ ቢሉ ፣ ቀንጠፉም ፣ ቢሉ ፤ የራስ ፣ ፀጕሩ ፣ ከግንድ ፣ ላይ ፣ የተጠመጠመ ፣ ዘንዶ ፣ ይመስል ፣ ነበር ፣ ጠልፎ ፣ አስቀርቶታል ።

ከጦር ፣ ምላሽ ፣ ሲሆን ፣ ኢዮአብ ፣ ከቶ ፣ ዛሬ ፣ አቤሴሎምን ፣ ያየው ፣ የለምን ፣ አለ ፤ አንድ ፣ ሰው ፣ እኔ ፣ አይቼዋለሁ ፣ አለ ፤ ገድለኸው ፣ ቢሆን ፣ የምትታጠቀው ፣ አፋ ፣ የምትመክተው ፣ ጋሻ ፣ አሥር ፣ ግርሻ ፣ እሰጥህ ፣ ነበር ፤ ዳሩ ፣ ምን ፣ ይሆናል ፣ ቀረና ፣ አለው ፤ ስንኳን ፣ አሥር ፣ ግርሽ ፣ ሺህ ፣ ግርሽ ፣ ብትሰጠኝ ፣ አልገድለውም ፣ ነበር ፤ በማን ፣ ደም ፣ ማን ፣ ይገበል ፣ ብዬ ፣ ጌታዬ ፣ ዳዊት ፣ አቤሴሎምን ፣ ያገኛችሁት ፣ እንደሆነ ፣ አትግደሉብኝ ፤ በሽሽ ፣ አንቃችሁ ፣ አምጡልኝ ፣ ሲል ፣ ሰምቻለሁ ፣

አለው ፤ ያለበትንሳ ፡ ታውቃለህን ፡ አለው ፡ አዎን ፡ አለው ፤ አድርሰኝ ፡ አለው ፤ ቢደርስ ፡ ደክሞ ፡ ነፍሱ ፡ ከሥጋው ፡ እለይ ፡ እለይ ፡ ስትል ፡ አገኘው ፤ በሦስት ፡ ዘገር ፡ መሐል ፡ ልቡን ፡ ወጋው ፤ የተከተሉትም ፡ ብላቴኖች ፡ አሥር ፡ ናቸው ፤ በሥር ፡ ፍላፃ ፡ ወግተውታል ፤ ሦስቱ ፡ የሦስትነት ፡ አሥሩ ፡ የአሥሩ ፡ ቃላት ፡ ምሳሌ ፡ ቸብቸቦውን ፡ ቄርጤ ፡ ግንዱን ፡ አገላብጠ ፡ ጥሎ ፡ ቸብቸቦውን ፡ ይዘ ፡ ሄዷል ። ፪፡ሳሙ፡፲፰፡፬-፲፭ ። አኪማሆስ ፡ አሰናብተኝ ፡ የልጁን ፡ ሞት ፡ ላርዳው ፡ አለው ፤ አይሆንም ፡ የዛሬ ፡ መልእክት ፡ ያንተ ፡ አይደለም ፡ ኩሲ ፡ አረጋዊ ፡ ይንገረው ፡ ብሎታል ፡ ደግሞ ፡ ጥቂት ፡ ቆይቶ ፡ ልሂድ ፡ አለው ፡ ልሂድ ፡ ልሂድ ፡ ትላለህ ፡ ልጅህ ፡ ሞተ ፡ ብትለው ፡ አይሾምህ ፡ አይሾልምህ ፡ ሂድ ፡ አለው ፡ ኩሲ ፡ አረጋዊ ፡ ነውና ፡ ዙሮ ፡ ሲሄድ ፡ ወቀደሞ ፡ በፍኖተ ፡ ኬልቃ ፡ ይላል ፡ አኪናሆም ፡ በስርጥ ፡ ጐዳና ፤ አንድም ፡ በዚያው ፡ ጥሶት ፡ ሄዷል ።

ያን ፡ ጊዜ ፡ ዳዊት ፡ ሁለት ፡ በር ፡ ባላት ፡ ሰገነት ፡ (አልፍኝ) ፡ ተቀምጦ ፡ ነበረ ፡ ሰላዮች ፡ አሉትና ፡ አንድ ፡ ፈጣን ፡ ሰው ፡ እየሮጠ ፡ መጣ ፡ አሉት ፤ አኪማሆስ ፡ ይሆናል ፡ ግባ ፡ በሉት ፡ አለ ፡ ገብቶ ፤ ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘአግብአ ፡ ፀረከ ፡ ውስተ ፡ እዴከ ፤ ጠላቶችህን ፡ በእጅህ ፡ የጣለልህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ፡ አለው ፡ ልጄ ፡ አቤሴሎምሳ ፡ እንደምን ፡ ሆነ ፡ አለው ፡ የሱ ፡ ነገር ፡ አልተገለጸልኝም ፡ ጦር ፡ ይሂድ ፡ ሲሉ ፡ ነበር ፡ አለው ፡ አሁንም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ መጣ ፡ አሉት ፡ ኩሲ ፡ አረጋዊ ፡ ይሆናል ፤ ግባ ፡ በሉት ፡ አለ ፡ አገብቶ ፡ ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘአግብአ ፡ ፀረከ ፡ ውስተ ፡ እዴከ ፡ አለው ፡ ልጄ ፡ አቤሴሎምሳ ፡ አለው ፡ ከመ ፡ አቤሴሎምሰ ፡ ወልዱ ፡ ለንጉሥ ፡ ይኩኑ ፡ ጸላዕቱ ፡ ለንጉሥ ። ጠላቶችህ ፡ አቤሴሎምን ፡ ይሁኑ ፡ አለው ፡ ቤቱን ፡ ዘግቶ ፡ ያለቅስ ፡ ጀመረ ። ፪፡ሳሙ፡፲፰ ፲፱ - ፴፫ ።

ሽኤል ፡ ግዳይ ፡ እንጥላለን ፡ ብለው ፡ ቢሄዱ ፡ በር ፡ ተዘግቶባቸው ፡ እያዘኑ ሲመለሱ ፡ ኢዮአብ ፡ አገኛቸው ፡ ወዴት ፡ ትሄዳላችሁ ፡ አላቸው ፡ ግዳይ ፡ እንጥላለን ፡ ብለን ፡ ብንሄድ ፡ ዳዊት ፡ ደጁን ፡ ዘግቶ ፡ በልጁ ፡ ሞት ፡ ያለቅሳል ፡ አሉት ፡ አትሂዱ ፡ ክዚህ ፡ ቄዩኝ ፡ ብሎ ፡ ሂዶ ፡ አንተ ፡ ጠላትህን ፡ እንጂ ፡ ወዳጅህን ፡ አያስወድድህም ፡ የዛሬ ፡ ድል ፡ በነአቤሴሎም ፡ እጅ ፡ በሆነ ፡ እንዴት ፡ በደረጉን ፡ ነበር ፤ ይልቁንም ፡ አንተ ፡ እንዴት ፡ በደረጉህ ፡ ነበር ፤ አሁንም ፡ ወጥተህ ፡ ግዳይ ፡ ትቀበል ፡ እንደሆነ ፡ ተቀበል ፡ ያለዚያ ፡ የምትወደውን ፡ መንግሥት ፡ በጠላትህ ፡ እጅ ፡ አድርጌ ፡ አሳይኻለሁ ፡ አለው ፤

እየተንቀጠቀጠ ፡ ወጥቶ ፡ የልጁን ፡ ቸብቸቦ ፡ ግዳይ ፡ ተቀብሏል ፤፡ ሳሙ ፡ ፲፱ ፡ ፩ - ፳ ።

ወማኅበረ ፡ አሕዛብ ፡ የዐውደከ ።

እንዲህ ፡ የተደረገ ፡ እንደሆነ ፡ ሴት ፡ ጌትያዊ ፡ በምስጋና ፡ ይከብሃል ፤ ማኅበር ፡ አለው ፡ ስድስት ፡ መቶ ፡ ራሱን ፡ ሆኖ ፡ አድሮለታልና ፤፡ ሳሙ ፡ ፲፮ ፡ ፲፰ ።

በእንተዝ ፡ ተመየጥ ፡ ውስተ ፡ አርያም ።

ትመሰገን ፡ ዘንድ ፡ ወደአርያም ፡ ተመለስ ፡ ማለት ፡ ፍረድ ፡ ሲል ፡ ነው ።

፮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይኩንኖ ሙ ፡ ለአሕዛብ

እኔ ፡ እቸኩላለሁና ፡ እንዲህ ፡ አልሁ ፡ እንጂ ፡ እግዚአብሔርስ ፡ በአሕዛብ ፡ ይፈርድባቸዋል ፡ የአቤሴሎም ፡ እናቱ ፡ ከአሕዛብ ፡ ወገን ፡ ናትና ፡ እንዲህ ፡ አለ ።

ፍታሕ ፡ ሊተ ፡ እግዚኦ ፡ አምላኪየ ፡ በከመ ፡ ጽድቅከ ።

አቤቱ ፡ ፈጣሪዬ ፡ እኔ ፡ እውነተኛ ፡ ነኝና ፡ እንደ ፡ እውነተኛነቴ ፡ ፍረድልኝ ፡ አልልም ፡ አንተ ፡ ግን ፡ እውነተኛ ፡ ነህና ፡ እንደእውነተኛነትህ ፡ ፍረድልኝ ፡ እልሃለሁ ፡ እንጂ ።

ወይኩንኒ ፡ በከመ ፡ የውሃትየ ።

እንደሞኝነቴ ፡ እንደቅንነቴ ፡ ይደረግልኝ ፡ ማለት ፡ ለመንግሥት ፡ ለደረሰ ፡ ልጅ ፡ ሥርዓት ፡ መንግሥት ፡ አውጥቶ ፡ ማሳየት ፡ የዋህነት ፡ ነውና ፤፡ ሳሙ ፡ ፲፭ ፡ ፲ - ፲፫ ። አንድም ፡ ሕግ ፡ እንደመጠበቁ ፡ ይሁንልኝ ፡ የዋህነት ፡ ዋጋ ፡ የሚያሰጥ ፡ ስለሆነ ።

፱ ፤ የኃልቅ ፡ እኩየ ሙ ፡ ለኃጥኣን ።

የኃጥኣን ፡ የነአቤሴሎም ፡ ክፋታቸው ፡ ያልቅባቸዋል ፤ ዝናም ፡ በላዬ ፡ አለቀ ፡ እንዲሉ ፤ ኃጢኣትማ ፡ ቢሠሩት ፡ ቢሠሩት ፡ ይፈጸማልን ፤ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ የማይሠሩት ፡ ስለሆነ ፤ አንድም ፡ በፍዳ ፡ ይፈጸምባቸዋል ፤

ወታረትዖሙ ፡ ለጻድቃን ።

ታሐይዎሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ጻድቃንን ፡ ታድናቸዋለህ ፡ አንድም ፡ ቅንነታቸውን ፡ ትገልጽላቸዋለህ ። ጠዋይኒ ፡ ኢይክል ፡ ረቲዐ ፡ እንዲል ፤ መክ ፡ ፭ ፡ ፲፭ አንድም ፡ ቀንተው ፡ እንዲሄዱ ፡ ታደርጋቸዋለህ ፡ ጠላት ፡ ያለበት ፡ ሰው ፡ አዩኝ ፡ አላዩኝ ፡ እያለ ፡ ተጎንብሶ ፡ ይሄዳልና ።

ይፈትን ፡ ልበ ፡ ወኵልያተ ፡ እግዚአብሔር

እግዚአብሔር ፡ ልብ ፡ ያሰበውን ፡ ኩላሊት ፡ ያጤሰውን ፡ መርምሮ ፡ ያውቃል ፡ እረ ፡ ሳይመረምርም ፡ ያውቃል ፤ ምሳ ፡ ፮ ፡ ፲፯ ። ኤር ፡ ፲፯ ፡ ፲ ። ሉቃ ፡ ፲፮ ፡ ፲፭ ። ግብ ፡ ሐ ፡ ፩ ፡ ፳፬ ። ራዕ ፡ ፪ ፡ ፳፫ ።

፲ ፤ አማን ፡ ይረድአኒ ፡ እግዚአብሔር ። ዘያድኅኖሙ ፡ ለርቱዓን ፡ ልብ ።

ቅን ፡ ልቡና ፡ ያላቸውን ፡ ሰዎች ፡ የሚያድናቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ በእውነት ፡ ይረዳኛል ፤ አማነ ፡ ብለህ ፡ ነው ፡ አንድም ፡ እውነተኛ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረዳኛል ።

፲፩ ፤ እግዚአብሔር ፡ መኰንን ፡ ጽድቅ ።
እግዚአብሔር ፡ ፈታሒ ፡ በጽድቅ ፡ ኰናኒ ፡ በርትዕ ፡ ነው ።
ኃያል ፡ ወመስተዓግሥ ።
ኃያል ፡ ነው ፡ ታጋሽም ፡ ነው ፤ ሰው ፡ ኃያል ፡ ቢሆን ፡ ትዕግሥት ፡ አይሰጠውም ፤ ተዓጋሢም ፡ ቢሆን ፡ ኃይል ፡ አይሰጠውም ፥ እሱ ፡ ግን ፡ ሁሉ ፡ ገንዘቡ ፡ ነውና ።
ወኢያመጽእ ፡ መንሱተ ፡ ኪሎ ፡ አሚረ ።
ትዕግሥቱም ፡ ሊታወቅ ፡ ሰው ፡ በበደለው ፡ ቍጥር ፡ መዓቱን ፡ ላምጣ ፡ አይልም ።
፲፪ ፤ እመሰ ፡ ኢተመየጥክሙ ፡ ሰይፎ ፡ ይመልሕ ።
እንዲህም ፡ ማለቱ ፡ ከገቢረ ፡ ኃጢአት ፡ ወደ ፡ ገቢረ ፡ ጽድቅ ፡ ከአምልኮተ ፡ ጣዖት ፡ ወደ ፡ አምልኮተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብትመለሱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ካልተመለሳችሁ ፡ ኃይሉን ፡ ሊያስታውቅ ፡ በሰብአ ፡ ትካት ፡ በሰብአ ፡ ሰዶም ፤ በሰብአ ፡ ገሞራ ፡ የመዘዘውን ፡ ሰይፈ ፡ መዓቱን ፡ በእናንተ ፡ ይመዘዋል ፤ዘፍ ፡ ፯ ፡ ፲፯፡ ፭፬ ። ፲፱ ፡ ፳፬ - ፳፭ ።
አንድም ፡ ወደኔ ፡ የቃጣው ፡ ሰይፈ ፡ መዓቱን ፡ ወደ ፡ እናንተ ፡ ይመልሰዋል ፥ (ይመልስ) ።
ቀስቶኒ ፡ ወተረ ፡ ወአስተዳለወ ።
ቀስቱን ፡ ቀፈረ ፡ አዘጋጀ ።ሶቃ፡፲፫፡፫
፲፫ ፤ ወአስተዳለወ፡ቦቱ፡ኀምዘ፡ዘይቀትል ነፍስ ፡ ከሥጋ ፡ የሚለይበትን ፡ መርዝ ፡ ቀባው ።ኢሳ ፡ ፭ ፡ ፳፯። የወዲያኛው ፡ ቀስቱን ፡ እያተባ ፡ እያጋለ ፡ መርዝ ፡ እየቀባ ፡ ይመጣል ፡ ይህን ፡ የወረወረው ፡ እንደሆነ ፡ ቀዳማዩን ፡ ከነደኃሪዩ፡ ሰውየውንም፡ ወግቶ፡ከመሬት ፡ የሚሰፋ ፡ ነው ፤ የወዲሁም ፡ እግዚአብሔር ፡ ጥበቡን ፡ ገልጾለት ፡ ጀባውን ፡ ወሀ ፡ ነክሮ ፡ ለጋሻው ፡ አልብሶ ፡ ይመጣል ፡ ግለቱን ፡ ወሀው ፡ ያቀዘቅዝለታል ፤ መርዙን ፡ ጀባው ፡ ይጠርግለታል ፡ ስለቱን ፡ ጋሻው ፡ ይመልስለታል ።
ወአሕማሁኒ ፡ እለ ፡ ይነዱ ፡ ገብረ ።
ኢዮአብ ፡ ቀስቱን ፡ የሚናደድ ፡ አደረገ ፤ ኢሳ ፡ ፭ ፡ ፳፯ ፡ ፲፬ ።
፲፬ ፤ ናሁ ፡ ሐመ ፡ ዐሚኒ ፡ በዐመፃሁ ።
አኪጦፌል ፡ አንድም ፡ አቤሴሎም ፡ ፅሮ ፡ ግሮ ፡ በመከረው ፡ ምክር ፡ ጠፋ ።
ፀንሰ ፡ በፃዕር ፡ ወወለደ ፡ ኃጢአተ ።
ፀንሰ ፡ ነቅዐ ፡ ሐልዮን ፡ ወወለደ ፡ ቍርፅ ፡ ሐልዮን ፡ አደረገ ።
፲፭ ፤ ግበ ፡ ከረየ ፡ ወደሐየ ።
ከረየ ፡ ነቢብን ፡ ደሐየ ፡ አፀና ፥ አንድም ፡ (ፀንሰ ፡ በፃዕር) ፡ አኪጦፌል ፡ አቤሴሎምን ፡ ባዕ ፡ ኀበ ፡ ዕቁባቲሁ ፡ ልበለው ፡ ብሎ ፡ አሰበ ፤ (ወወለደ) ፡ ባዕ ፡ ኀበ ፡ ዕቁባቲሁ ፡ አለው ፤ ፪ ፡ሳሙ ፡፲፮፡፳፪። ግበ ፡ ከረየ ፥ ሸህ ፡ ጦር ፡ ስጠኝና ፡ ቸብቸቦውን ፡ ቄር ጩ ፡ ላምጣልህ ፡ አለው ፡፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፯ ፩—፬ ።

ወይወድቅ ፡ ውስተ ፡ ግብ ፡ ዘገብረ ።

አቤሴሎም ፡ አንድም ፡ አኪጦፌል ፡ በመከረው ፡ ምክር ፡ ጠፋ ።

፲፯ ፡ ወይገብዕ ፡ ዓማሁ ፡ ዲበ ፡ ርእሱ ።

ፅሮ ፡ ግሮ ፡ የመከረው ፡ ምክር ፡ ወደ ራሱ ፡ ይመለሳል ፤ ደንጊያ ፡ ቢያጉኑት ፡ ተመልሶ ፡ ካናት ፡ እንዲሉ ።

ወትወርድ ፡ ዓመዓሁ ፡ ዲበ ፡ ድማኁ ።

ፅሮ ፡ ግሮ ፡ የመከራት ፡ ምክር ፡ ወደ ራሱ ፡ ትመለሳለች ። ዘፀ ፣ ፲፰፡፲፩ አኪጦፌል ፡ ምክሩን ፡ እንዳልተቀበለለት ፡ አይቶ ፡ እንግዲህማ ፡ አባትና ፡ ልጅ ፡ ታርቀው ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ አዕቅ ፡ ዓዕቄን ፡ እየቄረጡ ፡ ሲጫወቱብኝ ፡ ሊኖሩ ፡ አይደለምን ፤ አንድ ፡ ቀን ፡ እንኳ ፡ አያሳርፉኝ ፡ ብሎ ፡ ወፀፀነ ፡ ዓድጎ ፡ ወሐረ ፡ ውስተ ፡ ሀገሩ ፡ ጉናሄም ። ካገሩ ፡ ሄዶ ፡ ሦስት ፡ ልጆች ፡ ነበሩት ፡ በዚህ ፡ ዋሉ ፡ በዚህ ፡ እደሩ ፡ ብሎ ፡ ከባዶ ፡ ቤት ፡ ገብቶ ፡ ታንቆ ፡ ሞቷል ። ፪ ፡ ሳሙ ፡ ፲፯ ፡ ፳፫ ።

፲፯ ፡ እገኒ፡ለእግዚአብሔር፡ብከመ፡ጽድቁ

እንደ ፡ እውነተኛነቱ ፡ ለእግዚአብሔር እገዛለሁ ።

ወእዜምር ፡ ለስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ። መዝ ፡ ፯፪ ፡ ፯ ።

ልዑል ፡ ለሚሆን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አንድም ፡ ልዑል ፡ ለሚሆን ፡ ስሙ ፡ ምስጋና ፡ አቀርባለሁ ።

መዝሙር ፡ ፸፩ ።

፩ ፡ እግዚኦ ፡ እግዚእነ ፡ ጥቀ ፡ ተሰብሐ ፡ ስምከ ፡ በኵሉ ፡ ምድር ። ቁ ፡ ፱ ፡ ኢሳ ፡ ፮ ፩ ።

ትንቢት ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ። እንዲህ ፡ ያለው ፡ ደረቅ ፡ ሐዲስ ፡ ይባላል ። አዕሩግ ፡ ሕፃናት ፡ በአንድ ፡ ወገን ፡ ሆነው ፡ በዕለተ ፡ ሆሣዕና ፡ ሆሣዕና ፡ በአርያም ፡ እያሉ ፡ ሲያመሰግኑ ፡ ከጊዜው ፡ ሳይደርስ ፡ እንደደረሰ ፡ ሆኖ ፡ ተገልያለት ፡ አስቀድሞ ፡ ተናግሮታል ። አቤቱ ፡ ስምህ ፡ በራቱ ፡ ማዕዘን ፡ ፈጽሞ ፡ ተመሰገነ ።

አስመ ፡ ተለዓለ ፡ ዕበየ ፡ ስብሐቲከ ፡ መልዕልተ ፡ ሰማያት ።

ወቢይ ፡ ስብሐቲከ ፡ ሲል ፡ ነው ። ገና ፡ ነሣዕከ ፡ ተወከፍከ ፡ ተመጠከ ፡ ሲል ፡ ነው ። ገና ፡ ሰው ፡ ሳትሆን ፡ ሰው ፡ ሆነህ ፡ ተገለጥህ ፡ ሲል ፡ ነው ።

፪ ፡ እምአፈ ፡ ደቂቅ ፡ ወሕፃናት ፡ አስተዳለውከ ፡ ስብሐተ ። መዝ ፡ ፰፩ ፡ ፫ ።

ነሣዕከ ፡ ተወከፍከ ፡ ተመጠከ ፡ ሲል ፡ ነው ። ገና ፡ ሰው ፡ ሳትሆን ፡ ሰው ፡ ሆነህ ፡ ተገለጥህ ፡ ሲል ፡ ነው ።

ነው ፤ ከሕፃናት ፡ አንደበት ፡ ምስጋና ን ፡ ተቀበልህ ፤ ማለት ፡ በኢህ ፡ አንደ በት ፡ ተመሰገንህ ፤ ሕፃናት ፡ የሚላቸ ው ፡ የዓርባ ፤ የሰማንያ ፡ ቀን ፡ ደቂ ቅ ፡ የሚላቸው ፡ ያመት ፡ የሁለት ፡ ዓ መት ፡ ናቸው ፤ ይህስ ፡ አይደለም ፡ ተሐፅነ ፡ ያለበት ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ደቂ ቅ ፡ የሚላቸው ፡ የዓርባ ፤ የሰማንያ ፡ ቀን ፡ ሕፃናት ፡ የሚላቸው ፡ ያመት ፡ የሁለት ፡ ዓመት ፡ ናቸው ፡ ይሏል ፤ እኒህ ፡ በዕለተ ፡ ሆሣዕና ፡ ተገልያላቸ ው ፡ አንድም ፡ አመስግኙኝ ፡ ብሏቸ ው ፡ ዕጕለ ፡ ርግብ ፡ ዘውገ ፡ ማዕነቅ ፡ ይዘው ፡ ሆሣዕና ፡ በአርያም ፡ እያሉ ፡ አመስግነውታል ፤ ጥበብ ፡ ከሠተት ፡ አፈ ፡ ሕፃናት ፡ ወልሳነ ፡ በሐማን ፡ ረ ሰየት ፡ ርቱዐ ፡ ወነባቤ ፡ እንዲል ።

በእንተ ፡ ጸላኢ ።

ዲያብሎስን ፡ ደስ ፡ አይበለው ፡ ብለህ ።

ከመ ፡ ትንሥቶ ፡ ለጸላኢ ፡ ወለገፋኢ ።

፬ላዒ ፡ ገፋዒ ፡ የሚሆን ፡ ዲያብሎ ስን ፡ ትረታው ፡ ትመታው ፡ ዘንድ ፡ አስተዳሎከ ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ አምስ ት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ የሰውን ፡ ልቡ ና ፡ እንደ ፡ ዙፋን ፡ ሰውነቱን ፡ እን ደ ፡ ድንኳን ፡ ፍትወታት ፡ እኩያት ፡ ኃጣውእን ፡ እንደ ፡ አጥር ፡ እንደ ፡ ቅ ጥር ፡ አድርጎ ፡ ይገዛ ፡ ነበር ፤ ጌታ ፡ ሰ ው ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ እየወጣ ፡ ሄ ዲልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ አንድም ፡ (በ እንተ ፡ ፀላዒ) ፡ ቢፅ ፡ ሐሳዊን ፡ ደስ ፡ አይበለው ፤ ብለህ ፡ (ከመ ፡ ትንሥቶ ፡ ለጸላዒ ፡ ወለገፋዒ) ፡ ጸላዒ ፡ ገፋዒ ፡ የሚሆን ፡ ቢፅ ፡ ሐሳዊን ፡ ትረታው ፡ ትመታው ፡ ዘንድ ።

፫ ፤ እስመ ፡ ንሬኢ ፡ ሰማያተ ፡ ግብረ ፡ እ ፃ ብ ኃ ክ ።

የእጅህ ፡ የቃልህ ፡ ፍጥረት ፡ የሚሆ ኑ ፡ ሰባቱ ፡ ሰማያትን ፡ እናያለንና ።

ወርኀ ፡ ወከዋክብተ ፡ ዘሰላሕ ፡ ሣረርከ ።

አንተ ፡ የፈጠርካቸው ፡ ፀሐይ ፡ ጨ ረቃ ፡ ከዋክብትን ፡ እናያለንና ፤ ነግዕ ከ ፡ ምንት ፡ ውእቱ ፡ ማንሻ ፡ አንድ ም ፡ የእጅህ ፡ የቃልህ ፡ ፍጥረት ፡ የሚ ሆኑ ፡ ሰባቱ ፡ ሰማያትን ፡ እናያለንና ፤ (ወርኀ ፡ ወከዋክብተ) ፡ ፀሐይ ፡ ጨረ ቃ ፡ ከዋክብትን ፡ አንተ ፡ ፈጠርህ ፤ እ ንላለን ፡ እንጂ ፤ ሌላ ፡ ፈጠረ ፡ እንላ ለንን ፤ ምንት ፡ ውእቱ ፡ ማንሻ ፡ አን ድም ፡ የእጅህ ፡ የቃልህ ፡ ፍጥረት ፡ የሚሆኑ ፡ ሰባቱ ፡ ሰማያትን ፡ እናያለ ንና ፡ ፀሐይ ፡ ጨረቃ ፡ ከዋክብትን ፡ አንተ ፡ ፈጥረሃልና ።

፬ ፡ ምንት ፡ ውእቱ ፡ ሰብእ ፡ ከመ ፡ ትዝክሮ

ሰሚው ፡ ወልድ ፡ ነው ፤ ሰውን ፡ በራ ስህ ፡ ተዋህዶ ፡ ታስበው ፡ ዘንድ ፡ ም ን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ።

ወምንትኑ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ከመ ፡ ተሐ ውያ ።

ዕብ ፡ ፪ ፡ ፮ ።

ሰውን ፡ በራስህ ፡ ተዋህዶ ፡ ትጐበኘው ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ፤ መ ሬት ፡ አንተ ፡ ወትገብዕ ፡ ውስተ ፡ መ

ሬት ፡ ተብሎ ፡ የተፈረደበት ፡ ፈራሽ ፡ በስባሽ ፡ አይደለምን ። ዘፍ ፡ ፫ ፡ ፲፱ ።

፭ ፤ ሕቀ ፡ አኅፀፅኮ ፡ እመላእክቲከ ።

እንዲህ ፡ ሲል ፡ ያውካል ፡ አንድም ፡ ሰ ሚው ፡ አብ ፡ ነው ፤ (ምንት ፡ ውእ ቱ ፡ ሰብእ ፡ ከመ ፡ ትዝክሮ) ፡ ሰውን ፡ በልጅህ ፡ ተዋህዶ ፡ ታስበው ፡ ዘንድ ፡ ምን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ፤ (ወምንትኑ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ ከመ ፡ ተሐውየ) ፡ በልጅህ ፡ ተዋህዶ ፡ ትገ-በኘው ፡ ዘን ድ ፡ ምን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ፤ መሬ ት ፡ አንተ ፡ ወትገብዕ ፡ ውስተ ፡ መ ሬት ፡ ተብሎ ፡ የተፈረደበት ፡ ፈራ ሽ ፡ በስባሽ ፡ አይደለምን ። ልጅህን ፡ እጅግ ፡ ጥቂት ፡ ከሠላእክት ፡ አሳነስ ከው ፡ መላእክት ፡ ኢሐማምያን ፡ ኢ መዋትያን ፡ ናቸው ፤ እሱ ፡ ግን ፡ ም ንም ፡ በፈቃዱ ፡ ቢሆን ፡ ታሞ ፡ ሞ ቶ ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ ሌሊ ት ፡ በከርሠ ፡ መቃብር ፡ አድሮ ፡ ፈ ጥኖ ፡ ተነሥቷልና ፤ ወአኅፀረ ፡ ዕድ ሜ ፡ ለርእሱ ፡ እንዲል ።

ክብረ ፡ ወስብሐተ ፡ ከለልኮ ። ቆላ ፡ ፫ ፡ ፲፬ ።

ክብርን ፡ የክብር ፡ ክብርን ፡ ገንዘብ ፡ አደረግህለት ፡ አንድም ፡ መስቀል ፡ ቀኖትን ፡ ገንዘብ ፡ አደረግህለት ፤ ይ ትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘሰምየ ፡ ሕማማተ ፡ ወልዱ ፡ ክብረ ፡ ወስብሐ ተ ፡ እንዲል ።

፮ ፤ ወሚመኮ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ግብረ ፡ እ ደ ዊ ከ ።

በኻያ ፡ ሁለቱ ፡ ስነ ፡ ፍጥረት ፡ አሰለ ጠንኸው ።

ወኵሎ ፡ አግረርከ ፡ ለሙ ፡ ታሕተ ፡ እገ ሪሁ ። ዕብ ፡ ፪ ፡ ፮—፰ ።

ሁሉን ፡ በእጁ ፡ ጭብጥ ፡ በእግሩ ፡ እ ርግጥ ፡ አድርገህ ፡ አስገዛህለት ። መዝ ፡ ፻፱ ፡ ፩ ።

፯ ፤ አባግዓኒ ፡ ወኵሎ ፡ አልሕምቲ ።

ላሙን ፡ በጉን ፡ ሁሉ ፡ አስገዛህለት ።

ወዓዲ ፡ እንስሳ ፡ ዘገዳም ።

በበረኃ ፡ ያሉ ፡ ድኩላውን ፡ ብሆሩን ፡ አስገዛህለት ።

፰ ፤ አዕዋፈ ፡ ሰማይኒ ፡ ወዓሣተ ፡ ባሕር ።

በሰማይ ፡ የሚበሩ ፡ አዕዋፍን ፡ ንስር ን ፡ በባሕር ፡ የሚኖሩ ፡ ዓሣ ፡ አንበ ሪን ፡ አዞ ፡ ጉማሬን ፡ አስገዛህለት ።

ወዘኒ ፡ የሐውር ፡ ውስተ ፡ ፍኖተ ፡ ባሕር ።

በባሕር ፡ የሚመላለስን ፡ ሁሉ ፡ አስገ ዛህለት ። አንድም ፡ (ዓባግዓኒ) ፡ ነቢ ያት ፡ ካህናትን ፡ (ወኵሎ ፡ አልህም ተ) ፡ ሕዝቡን ፡ (እንስሳ ፡ ገዳም) ፡ አ ሕዛብን ፡ (አዕዋፈ ፡ ሰማይኒ) ፡ መላእ ክትን ፡ (ዓሣተ ፡ ባሕር) ፡ በደሴት ፡ የ ሚኖሩትን ፡ (ዘኒ ፡ የሐውር ፡ ውስተ ፡ ፍኖተ ፡ ባሕር) ፡ በባሕር ፡ የሚነግዱ ፡ ነጋድያንን ፡ አስገዛህለት ። አንድም ፡ (ዓባግዓኒ) ፡ ሐዋርያትን ፡ (አልሕምተ) ፡ ሰብአ ፡ አርድእትን ፡ (እንስሳ ፡ ገዳም ፡ ባሕታውያንን ፡ (አዕዋፈ ፡ ሰማይ) ፡ አ ጋንንትን ፡ (ወዓሣተ ፡ ባሕር) ፡ በመቃ ብር ፡ ያሉ ፡ ሥጋትን ፡ (ወዘኒ ፡ የሐው ር) ፡ በሲኦል ፡ ያሉ ፡ ነፍሳትን ፡ አስገ ዛኸው ፤ አንድም ፡ (አዕዋፈ ፡ ሰማ

ይኑ) ፡ በአየር ፡ ያሉ ፡ አጋንንትን ፡ ኢ
ትሕሚ ፡ ብዑላን ፡ ውስተ ፡ ቤትከ ፡
እስመ ፡ ያፈ ፡ ሰማይ ፡ ያወጽአ ፡ ለነገ
ርከ ፡ እንዲል ።

(ዓሣተ ፡ ባሕር) ፡ በባሕር ፡ በዱር ፡ ያ
ሉ ፡ አጋንንትን ፡ (ወዘኒ ፡ የሐውር) ፡
በውቅያኖስ ፡ ያሉ ፡ አጋንንትን ፡ አስ
ገዛህለት ። ማቴ ፡ ፮ ፡ ፴፮ ። ፲፩ ፡ ፳፯ ።
ዮሐ ፡ ፲፮ ፡ ፪ - ፬ ።

፬ ፤ እግዚኦ ፡ እግዚእነ ፡ ጥቀ ፡ ተሰብሐ
ስምከ ፡ በዅሉ ፡ ምድር ። ቊ ፡ ፭ ።

ቢያምረው ፡ ቢጥመው ፡ ቢርቀው ፡
ደገመው ።

መ ዝ መ ር ፡ ፬ ።

፩ ፤ እገኒ ፡ ለከ ፡ እግዚኦ ፡ በዅሉ ፡ ልብየ ።

በእንተ ፡ ርእሱ ፡ ነው ፤ በእንተ ፡ ገፋ
ሚ ፡ ወተገፋዒ ፡ ይላል ፤ ገፋሚ ፡ ዲያ
ብሎስ ፡ ሳኦል ፡ ስናክሬም ፡ ተገፋዒ ፡
አዳም ፡ ዳዊት ፡ ሕዝቅያስ ። ገፋዕያን ፡
ወተገፋዕያን ፡ ይላል ፤ ገፋዕያን ፡ አሕ
ዛብ ፡ አጋንንት ፡ ተገፋዕያን ፡ ፭ኤል ፡
ምዕመናን ፡ ይህንና ፡ አፈቅረከን ፡ ጠ
ላቶቹ ፡ ተከትተው ፡ ከጠፉለት ፡ መን
ግሥቱ ፡ ከተደላደለለት ፡ በኋላ ፡ ተና
ግሮታል ፡ ወዝንቱ ፡ ነገሩ ፡ ለዳዊት ፡
ምዕመን ፡ ሶበ ፡ ገብዑ ፡ ጸላዕቱ ፡ ታህ
ተ ፡ እገሪሁ ፡ እንዲል ። አቤቱ ፡ በፍ
ጹም ፡ ልቡናዬ ፡ አመሰግንሃለሁ ፤ የ
ምስጋና ፡ አገዛዝ ፡ እገዛልሃለሁ ።

ወእነግር ፡ ዅሎ ፡ ስብሓቲከ ።

ጌትነትህ ፡ ታምራትህን ፡ ሁሉ ፡ እነግ
ራለሁ ፡ አስተምራለሁ ።

፪ ፤ እትፈሣሕ ፡ ወእትሐሠይ ፡ ብከ ።

በንተ ፡ አምኜ ፡ በተሠራልኝ ፡ ሥራ ፡
አንድም ፡ በንተ ፡ በማመኔ ፡ ደስ ፡ ይ
ለኛል ።

ወእዜምር ፡ ለስምከ ፡ ልዑል ።

ልዑል ፡ የሚሆን ፡ ስምህን ፡ አመሰግ
ናለሁ ፤ ልዑል ፡ ለሚሆን ፡ ስምህ ፡ ም
ስጋና ፡ አቀርባለሁ ።

፫ ፤ ሶበ ፡ ገብኡ ፡ ጸላዕትየ ፡ ድኅሬሆሙ ።

ምን ፡ ጊዜ ፡ ነዋ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡
ጠላቶቼ ፡ አድኅ ፡ አነስ ፡ አድሮ ፡ አነ
ስ ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ ነው ።

ይድወዩ ፡ ወይትኃጐሉ ፡ እምቅድመ ፡
ገጽከ ።

የሞት ፡ ደዌ ፡ ይታመሙ ፡ ዘንድ ፡ ከ
በለሚልነትህ ፡ እንደወጡ ፡ ይቀሩ ፡
ዘንድ ፡ አንድም ፡ ይድወዩ ፡ የሞት ፡
ደዌ ፡ ይታመሙ ፤ ወይትኃጐሉ ፡ ከ
በለሻልነትህ ፡ እንደወጡ ፡ ይቅሩ ፡
ብዬ ።

፭ ፤ እስመ ፡ ገበርከ ፡ ሊተ ፡ ፍትሐየ ፡
ወበቀልየ ።

ፍርዴን ፡ ፍርድ ፡ በቀሌን ፡ በቀል ፡ አ
ድርገሃልና ፡ አንድም ፡ ፈጽመህ ፡ ፈ
ርደህልኛልና ፡ ተበቀል ፡ ሊተ ፡ እም
ዕድውየ ፡ እንዲል ።

ወነበርከ ፡ ዲበ፡መንበርከ፡መኰንን፡ጽድቅ ፈታሒ ፡ በጽድቅ ፡ ኰናኒ ፡ በርትዕ ፡ አንተ ፡ በዙፋንህ ፡ ላይ ፡ ተቀመጥህ ፤ ማለት ፡ ፈረድህ ።

፰ ፤ ገሠፅከሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ወተኃጕለ ፡ ረሲዓን ።

አሕዛብን ፡ መራሃቸው ፡ ቀፃሃቸው ፤ አንተን ፡ የዘነጉ ፡ ሁሉ ፡ ጠፉ ። አንድም ፡ (ገሠፅከሙ ፡ ለአሕዛብ) ፡ ረሲዓን ፡ አንተን ፡ የዘነጉ ፡ አሕዛብን ፡ መራሃቸው ፡ ቀፃሃቸው ፤ (ወተኃጕለ) ፡ ጠፉ ።

ወደምሰስከ ፡ ስሞሙ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ።

ስም ፡ አጠራራቸውን ፡ ለዘላለሙ ፡ አጠፋህ ።

፮ ፤ ፀርሰ ፡ ተገምሩ ፡ በኩናት ፡ ለዝሉፉ ።

ፀርሰ ፡ ስመ ፡ ጭፍራ ፡ ነው ፤ ፀርከ ፡ የሚባሉ ፡ ጠላቶች ፡ ተካትተው ፡ ጠፉ ፤ ወተገምሩ ፡ የዲዋ ፡ ዮርዳኖስ ፡ እንዲል ።

አንድም ፡ ጠላቶቼ ፡ እለሳአል ፡ ተካትተው ፡ ጠፉ ።

ወአህጉሪሆሙኒ ፡ ነሥትከ ።

አገራቸውን ፡ ፈታሕ ።

ወትሥዕር ፡ ዝክሮሙ ፡ ኀቡረ ።

ዝክሮሙ ፡ ኀቡረ ፡ ምስለ ፡ ሀገሮሙ ፡ በል ። ሀገራቸውን ፡ ከነስማቸው ፡ አጠፋህ ፤ ውሉድ ፡ ወሕንፃ ፡ ሀገር ፡ ያዓብዩ ፡ ስመ ፡ እንዲል ።

ጥንቱን ፡ ለልማዱ ፡ ይህ ፡ የዕገሌ ፡ ልጅ ፡ ነው ። ይህ ፡ የዕገሌ ፡ ግምብ ፡ ነው ፡ እየተባለ ፤ ስሙን ፡ ሲያስጠራው ፡ ይኖር ፡ ነበር ፤ እሊህ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ጠፉ ።

አንድም ፡ (ፀርሰ ፡ ተገምሩ ፡ በኩይናት ፡ ለዝሉፉ) ፡ አጋንንት ፡ በመስቀል ፡ በጥምቀት ፡ ጠፉ ፡ ማለት ፡ ድል ፡ ተነሡ ። (ወአህጉሪሆሙኒ ፡ ነሥትከ) ፡ ከማደሪያቸው ፡ ከሰው ፡ ልቡና ፡ አስወጥተህ ፡ ስደድካቸው ፤ (ወትሥዕር ፡ ዝክሮሙ ፡ ኀቡረ) ። ከማደሪያቸው ፡ ከሰው ፡ ልቡና ፡ አስወጥተህ ፡ እንደሰደድካቸው ፡ መመለካቸውንም ፡ አጠፋህ ።

፯ ፤ እግዚአብሔርሰ ፡ ይነብር ፡ ለዓለም ።

እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ለዘለዓለም ፡ ይኖራል ፡ ማለት ፡ አጥፊ ፡ ለጥፋት ፡ የሚለው ፡ የለም ፡ ሲፈርድ ፡ ሲያጠፋ ፡ ይኖራል ።

ወአስተዳለወ ፡ መንበሮ ፡ ለኰንኖ ።

ለመፍረድ ፡ ዙፋኑን ፡ አዘጋጀ ፤ በግሥ ፡ ተናገረው ። ንጉሥ ፡ ሲፈርድ ፡ ዘውዱን ፡ ደፍቶ ፡ ሕለተ ፡ ወርቁን ፡ ጨብጦ ፡ በዙፋኑ ፡ ተቀምጦ ፡ እንደሆነ ፡ ይፈርዳል ፡ ሲል ፡ ነው ።

፰ ፤ ወውእቱ ፡ ይኴንና ፡ ለዓለም ፡ በጽድቅ በውነቱ ፡ ለዓለም ፡ ይፈርድላታል ፤ በዓለም ፡ ይፈርድባታል ፤ ሁለት ፡ አርእስት ፡ ተናገረ ። ሁለቱንም ፡ ያመጣል ።

ወይኴንኖሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ በርትዕ ።

በአሕዛብ ፡ በውነት ፡ ይፈርድባቸዋል ፤ ይፈርድባታል ፡ ላለው ።

፱ ፤ ወኮኖሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስካዮሙ ፡ ለኀዳያን ።
እግዚአብሔር ፡ ለኀዳያን ፡ አምባ ፡ መፀጊያ ፡ ይሆናቸዋል ፤ ይፈርድላታል ፡ ላለው ።
ወረዳኢሆሙ ፡ ውእቱ ፡ በጊዜ ፡ ምንዳቤሆሙ ።
በመከራቸውም ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ዋስ ፡ እንደ ፡ ጠበቃ ፡ ሆኖ ፡ ይረዳቸዋል ።
፲ ፤ ወይትዌከሉ ፡ ብከ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ያፈቅሩ ፡ ስመከ ። መዝ ፡ ፭ - ፲፩ ።
ስምህን ፡ የሚወዱ ፡ ሁሉ ፡ በንተ ፡ አምነው ፡ ፀንተው ፡ ይኖራሉ ።
እስመ ፡ ኢተኃደጎሙ ፡ ለእለ ፡ የኀሡከ ፡ እግዚአ ።
አቤቱ ፡ በሕግ ፡ በአምልከ ፡ የሚሹህን ፡ በመከራ ፡ አትጥላቸውምና ።
፲፩ ፤ ዘምሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘየኀድር ውስተ ፡ ጽዮን ።
በጽዮን ፡ ሰማያዊት ፡ በጽዮን ፡ ምድራዊት ፡ አድሮ ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፡ አድሮ ፡ ለሚኖር ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ፤ አንድም ፡ ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ካምስት ፡ ቀን ፡ በማኅፀን ፡ ግርያም ፡ ያደረ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግኑ ፤ ለሱ ፡ ምስጋና ፡ አቅርቡ ።
ወንግርዎሙ ፡ ለአሕዛብ ፡ ምግባሮ ።
ሥራውንም ፡ ሁሉ ፡ ለአሕዛብ ፡ ንገሯቸው ፡ አስተምራቸው ። መዝ ፡ ፻፬ ፡ ፩ ።
፲፪ ፤ እስመ ፡ ተዘከረ ፡ ዘይትነሥሥ ፡ ደሞሙ
እንደፈሰሰ ፡ ይቅር ፡ የማይባል ፡ ደማቸውን ፡ አስቧልና ፡ አስቦ ፤ ጠላታቸውን ፡ አጥፍቷልና ። አንድም ፡ ደማቸውን ፡ የሚመራመር ፡ እግዚአብሔር ፡ አስቧልና ፡ አሰቦ ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ አጥፍቷልና ፡ አንድም ፡ ደማቸውን ፡ የሚፈላለግ ፡ ጠላታቸውን ፡ አስቦ ፡ አጥፍቷልና ። አንድም ፡ ጠላቱን ፡ በፍዳ ፡ የሚመረምር ፡ ደማቸውን ፡ አስቧልና ፡ አስቦ ፡ ጠላቶቻቸውን ፡ አጥፍቷልና ፡ እንደ ፡ ደመ ፡ አቤል ፡ እንደ ፡ ደመ ፡ ዘካርያስ ፡ ደመ ፡ አቤል ፡ መልአኩ ፡ ለጌናክ ፡ መካኒ ፡ ኃጥአንን ፡ እያዘረ ፡ ሲያሳየው ፤ ስት ካሰስ ፡ ስትንጸረጸር ፡ አየ ። ዘመንፈስ ፡ ዘሙኑ ፡ አለው ፡ ዘአቤል ፡ ዘቀተሉ ፡ እጉሁ ፡ ትሰኪ ፡ ኪያሁ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ይትጎጉሉ ፡ ደቂቁ ፡ እምገጸ ፡ ምድር ፡ በማየ ፡ አይኅ ። ወንድሙ ፡ ቃየል ፡ የገደለው ፡ የአቤል ፡ ናት ፡ ልጆቹ ፡ በጥፋት ፡ ወሀ ፡ ከምድር ፡ እስኪጠፉ ፡ ድረስ ፡ እሱን ፡ ስትከስ ፡ ትኖራለች ፡
ዘፍ ፡ ፬ ፡ ፭ - ፲፯ ።
ደመ ፡ ዘካርያስም ፡ በቤተ ፡ መቅደስና ፡ በዕቃ ፡ ቤት ፡ መካከል ፡ ሰብዓ ፡ ዘመን ፡ ሲፈላ ፡ ኑሯል ፤ ጥጦስ ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ሲያፈርስ ፡ ሲፈላ ፡ አይቶ ፡ ይህ ፡ ምንድነው ፡ አለ ፤ የደግ ፡ ሰው ፡ ደም ፡ ነው ፤ አይሁድ ፡ በግፍ ፡ አስገድለውት ፡ እንዲህ ፡ ሲፈላ ፡ ይኖራል ፡ አሉት ፤ ከገዳዮች ፡ ወገን ፡ ሰባት ፡ ሰዎች ፡ አስመጥቶ ፡ ቢያሳርድ ፡ አርፏል ። ፱ ፡ ሕፀ ፡ ፭፬ ፡ ፭፱ ። ማቴ ፡ ፳፫ ፡ ፴፭ ።

ወኢረስዓ ፡ ዐውያቶሙ ፡ ለነዳያን ።
የነዳያንንም ፡ ልመናቸውን ፡ ቸል ፡ አ
ላለምና ።

፲፫ ፡ ተሣሃለኒ ፡ እግዚኦ ፡ ወርኢ ፡ ዘከመ
የሐ ፡ ኒ ፡ ጸላእትየ ።
ጠላቶቼ ፡ መከራ ፡ እንዲያፀኑብኝ ፡ መ
ጠን ፡ እይ ፡ ተመልከት ። እንዲህ ፡ አይ
ተህ ፡ ተመልክተህ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ።

ዘያሌዕለኒ ፡ እምአናቅጸ ፡ ሞት ።
ሞት ፡ ገድሎ ፡ ከሚጥልበት ፡ ከመቃብ
ር ፡ በላይ ፡ የሚያደርገኝ ፡ እሱ ፡ ነው ፤
አንድም ፡ እንዳልሞት ፡ እንዳልቀበር ፡
የሚያደርገኝ ፡ እሱ ፡ ነው ። አንድም ፡
ምክንያተ ፡ ሞት ፡ ከሚሆኑ ፡ ከኃያላኑ ፡
በላይ ፡ የሚያደርገኝ ፡ እሱ ፡ ነው ፡
ማለት ፡ እለዚያን ፡ አጥፍቶ ፡ የሚያ
ድነኝ ፡ እሱ ፡ ነው ።

፲፬ ፤ ከመ ፡ እንግር ፡ ኵሎ ፡ ስብሐቲሁ ፡ በአ
ናቅጺሃ ፡ ለወለተ ፡ ጽዮን ። መዝ ፡ ፸፱ ፡ ፭፮
በኢየሩሳሌም ፡ አደባባይ ፡ ጌትነቱን ፡
ተአምራቱን ፡ እነግር ፡ አስተምር ፡
ዘንድ ፡ ጽዮን ፡ የዳዊት ፡ ከተማ ፡ ወ
ለት ፡ የሰሎሞን ፡ ከተማ ፡ እየቀደም ፡
እየሰፋ ፡ ሐዲልና ፤ አንድም ፡ ጽዮን ፡
የሰሎሞን ፡ ወለት ፡ የዳዊት ፡ ሰሎሞ
ን ፡ ያባቱ ፡ ከተማ ፡ ቢጠብበው ፡ ከ
ውጭ ፡ አስፍቶ ፡ አሠርቷልና ። ፭ ፡ ነገ
፫ ፡ ፭ ። አንድም ፡ ሕግ ፡ መጠበቅ ፡ በ
ሚገባቸው ፡ በምእመናን ፡ ጉባኤ ፡
እነግር ፡ አስተምር ፡ ዘንድ ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡
የሚያደርገኝ ፡ እሱ ፡ ነው ።

ወንትፈሣሕ ፡ በአድኅኖትከ ።
በትድግናህ ፡ ደስ ፡ ይለናል ፤ ንትፈ
ሣሕ ፡ ደስ ፡ ይበለን ።

፲፭ ፡ ጠግዑ ፡ አሕዛብ ፡ በጌጋዮሙ ፡ ዘገብሩ
አሕዛብ ፡ በሠሩት ፡ ሥራ ፡ ጠፉ ።

ወበይእቲ ፡ መሥገርት ፡ እንተ ፡ ኃብኡ ፡
ተሠገረ ፡ እግሮሙ ።
ሠውረው ፡ በመከሩት ፡ ምክር ፡ በሸ
መቁት ፡ ጦር ፡ ጠፉ ።

፲፮ ፤ የአምር ፡ እግዚአብሔር ፡ ገቢረ ፡
ፍ ት ሕ ።
እግዚአብሔር ፡ ፍርድን ፡ መፍረድ ፡
ያውቃል ። አንድም ፡ የፍርድ ፡ ገበሬ ፡
ነው ። አንድም ፡ (ፈሊጠ ፡ ፍትሕ) ፡
ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ ለይቶ ፡ መፍ
ረድ ፡ ያውቃል ። ሰው ፡ የሆነ ፡ እን
ደሆነ ፡ ካነጋገር ፡ ይፈረዳል ፤ ካያያዝ ፡
ይቀደዳል ፡ እንዲሉ ፤ የቃሉን ፡ ሰም
ቶ ፡ ይፈርዳል ። እሱ ፡ ግን ፡ የሐልዮ
ውን ፡ የነቢቡን ፡ የገቢሩን ፡ መርም
ሮ ፡ አውቆ ፡ ይፈርዳል ። ዮሐ ፡ ፭ ፡ ፲፩-፲፯
አንድም ፡ የስዲ ፡ ጳውሎስ ፡ ትርጓሜ ፡
(ይትአመር ፡ እግዚአብሔር ፡ በገቢረ ፡
ፍትሕ) ፡ ብሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ መ
ኖሩ ፡ እውነት ፡ በመፍረዱ ፡ ይታወ
ቃል ። በለጸጋውን ፡ ድኃ ፤ ድኃውን ፡
በለጸጋ ፡ በለጤናውን ፡ ድዉይ ፡ ድ
ዉዩን ፡ በለጤና ፡ ኃያሉን ፡ ደካማ ፡
ደካማውን ፡ ኃይለኛ ፡ በደረገው ፡
ጊዜ ፡ ያ ፡ የተበደለ ፡ ድኃ ፡ ለካ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ አለህን ፡ ይላልና ።

ወበግብረ ፡ እደዊሁ ፡ ተመሃረ ፡ ኀጥእ።

ኃጥእ ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔር ፡ በቃሉ ፡ በፈረደው ፡ ፍርድ ፡ ጠፋ ። አንድም ፡ እሱ ፡ ራሱ ፡ በመከረው ፡ ምክር ፡ ጠፋ ። በእጁ ፡ የተሠራ ፡ ጣዖቱን ፡ በማምለኩ ፡ ጠፋ ። አንድም ፡ ኃጥእ ፡ ሳአል ፡ በእጁ ፡ በተያዘ ፡ ሰይፍ ፡ ጠፋ ። ከአሕዛብ ፡ ጋራ ፡ ሲዋጋ ፡ ውሎ ፡ ወደ ማታ ፡ አንዱ ፡ መርዝ ፡ ቀብቶ ፡ በቀስት ፡ ወጋው ፡ እንደ ፡ አሳት ፡ ቢያቃጥለው ፡ ብላቴናውን ፡ ቁም ፡ ላዕሌየ ፡ ወቅትለኒ ፡ በኢህ ፡ በቄላፋን ፡ እጅ ፡ ክሞት ፡ ግደለኝ ፡ አለው ። ቀደህ ፡ ያለበስከኝ ፡ ቈርሰህ ፡ ያጐረሰከኝ ፡ ጌታዬን ፡ አብሬህ ፡ እሞትን ፡ እገድልህ ፡ አይሆንም ፡ አለው ። ወመልሐ ፡ ሰይፎ ፡ ወተረግዘ ፡ ለሊሁ ፡ በገዛ ፡ ሰይፉ ፡ ወድዶ ፡ ገብቶበታልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ፪፡ላሙ ፡ ፴፭ ፡ ፫ ፡ ፬ ።

፲፯ ፡ ይግብኡ ፡ ኃጥአን ፡ ሙስተ ፡ ሲኦል ተማጥኖተዋለሁ ፡ ኃጥአን ፡ መሰሉ ፡ ወደ ፡ መቃብር ፡ ይውረዱ ።

ወሶሎሙ ፡ አሕዛብ ፡ እለ ፡ ይረስዕዎ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ማን ፡ ማን ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡ እገሌ እገሌ ፡ ምን ፡ አሰኝቶኝ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በሕግ ፡ በአምልክ ፡ የሚዘነጉ ፡ ሁሉ ፡ ይውረዱ ፡ እንጂ ።

፲፰ ፡ እስመ ፡ አኮ ፡ ለዝሉፉ ፡ ዘይትረሳዕ ነዳይ ።

ነዳይ ፡ ዳዊት ፡ አንድም ፡ ማናቸውም ፡ ድኃ ፡ የሚዘነጋ ፡ አይደለምና ፡ ለጊዜውም ፡ ቢዘነጋ ፡ እንደተዘነጋ ፡ አይቀርምና ።

ወኢየኀጕሉ ፡ ትዕግሥቶሙ ፡ ነዳያን ፡ ለዓለም ።

ነዳያን ፡ ለዘላለሙ ፡ ዓስበ ፡ ትዕግሥታቸውን ፡ አያአጡምና ።

፲፱ ፡ ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ ወኢይጽናዕ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ።

አቤቱ ፡ በሥራ ፡ በመፍረድ ፡ ተነሣ ሰው ፡ በሰው ፡ አይጽና ።

ወይትኰነኑ ፡ አሕዛብ ፡ በቅድሜክ ።

አሕዛብም ፡ በፊትህ ፡ ይጠፉሉ ፡ ይጥፉ ።

፳ ፡ ሚ ፡ እግዚኦ ፡ መምሕረ ፡ ሕግ ፡ ላዕሌሆሙ ።

አቤቱ ፡ በዕድ ፡ ንጉሥ ፡ አንግሥባቸው ።

ወያእምሩ ፡ (የአምሩ) ፡ አሕዛብ ፡ በእሙ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ እሙንቱ ።

እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ተገኝ ፡ እንደሆኑ ፡ ያውቃሉ ፡ ይወቁ ። አንድም ፡ (ሚ ፡ እግዚኦ ፡ መምሕረ ፡ ሕግ ፡ ላዕሌሆሙ) ፡ ሞትን ፡ አምጣባቸው ፡ መምር ፡ አለው ፡ መምር ፡ እንዳያደላ ፡ ሞትም ፡ አያደላምና ፤ መምህር ፡ ወመገሥፅ ፡ ዘኢያድሉ ፡ ለገጽ ፡ እንዲል ።

አንድም ፡ ሞት ፡ መምጣቱ ፡ ሕግ ፡ በመፍረሱ ፡ ነውና ፤ ወበትእዛዘ ፡ ሕግ ፡ ተሠርዓ ፡ ሞት ፡ እንዲል ።

አንድም ፡ መምር ፡ መክሮ ፡ አስተምሮ ፡ ወደገዳም ፡ እንዲወስድ ፡ ሞትም ፡

ከአኃው ፡ አንዱን ፡ ንጽል ፡ አድርጎ ፡ የወሰደው ፡ እንደሆነ ፡ ለዚህ ፡ ፡ ዕድሜያችን ፡ እያሉ ፡ ወደገዳም ፡ ይሄዳሉና ፤ (ወየአምሩ ፡ ከመ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው ፡ እሙንቱ) ፡ እንዲህ ፡ የሆነ ፡ እደሆነ ፡ ፈራሽ ፡ በስባሽ ፡ እንደሆኑ ፡ ያውቃሉ ።

ጽዕ ፡ ለምንት ፡ እግዚኦ ፡ ቆምከ ፡ እምርኁቅ ።

አቤቱ ፡ ለምን ፡ ርቀህ ፡ ቆመሃል ፡ በጌታ ፡ መራቅ ፡ መቅረብ ፡ ኑሮበት ፡ አይደለም ፡ መራዳቱን ፡ መቅረብ ፡ አለመራዳቱን ፡ መራቅ ፡ ብሎ ፡

ወትትሜወር ፡ በጊዜ ፡ ምንዳቤየ ።

በመከራዬከ ፡ ቀን ፡ ለምን ፡ ቸል ፡ ትለኛለህ ።

ጽጀ ፡ በትዕቢቱ ፡ ለኃጥእ ፡ ይውዒ ፡ ነዳይ ።

በባለጸጋ ፡ ጎጢአት ፡ ትዕቢት ፡ ድኃው ፡ ከእሳት ፡ እንደገባ ፡ ሽማት ፡ ያርራል ፡ ይኰማተራል ። እምተሀብ ፡ ለኃጥእ ፡ ሀብ ፡ ለጻድቅ ፡ እንዲል ። እንድም ፡ ለምንት ፡ እግዚኦ ፡ ቆምከ ፡ እምርኁቅ) ፡ አምስት ፡ ሺህ ፡ አምስት ፡ መቶ ፡ ዘመን ፡ ምሉ ፡ ለምን ፡ ርቀህ ፡ ቆምህ ፡ (ወትትሜወር ፡ በጊዜ ፡ ምንዳቤየ) ፡ በመከራ ፡ ነፍሴ ፡ ጊዜ ፡ ለምን ፡ ቸል ፡ ትላለህ ፡ ሰው ፡ ሆነህ ፡ ሥጋ ፡ ለብሰህ ፡ አታድነንም ፡ (በትዕቢቱ ፡ ለኃጥእ ፡ ይውዒ ፡ ነዳይ) በዲያብሎስ ፡ ክፋት ፡ አዳም ፡ ከእሳት ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ሽማት ፡ ይቃጠላል ፡ አሁን ፡ በዲብሎስ ፡ ክፋት ፡ አዳም ፡ የሚጐዳ ፡ ሆኖ ፡ አይደለም ፡ መስሎ ፡ ቢሠራው ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ግብሩ ፡ አንድ ፡ ነው ፤ የሁሉም ፡ አምላክነቱን ፡ መሻት ፡ ነውና ፡ በትዕቢቱ ፡ ለዲያብሎስ ፡ ተኩነ ፡ አቡነ ፡ አዳም ፡ እንዲል ።

ወይሠገሩ ፡ ባው ፡ ኃጥኦሙ ፡ እንተ ፡ ሐለዩ ።

አስበው ፡ በሠሩት ፡ ሥራ ፡ ጠፉ ፡ ይጥፉ ።

ጽቮ ፡ እስመ ፡ ይትዌደስ ፡ ኃጥእ ፡ በፍትወተ ፡ ነፍሱ ።

ኃጥእ ፡ ሰው ፡ ወድዶ ፡ በሠራው ፡ ኀጢአት ፡ ይመሰገናል ። ይህ ፡ ሴባ ፡ ነው ። ሲመሽ ፡ ጎመዱን ፡ ነጥቆ ፡ ገመዱን ፡ ጠቅልሎ ፡ ይሄዳል ፤ ውሻ ፡ ሳይጮኽበት ፡ አጥር ፡ ሳይሰበርበት ፡ ግምቡን ፡ ምሶ ፡ ግድግዳውን ፡ አፍርሶ ፡ ከልጅነት ፡ እስከ ፡ ዕውቀት ፡ ያጠራቀመውን ፡ ገንዘብ ፡ ንቅስ ፡ አድርጎ ፡ ይዘበት ፡ ይሄዳል ፤ ወዲያው ፡ ተነሥተው ፡ ባዲስ ፡ ፍለጋ ፡ ተከትለው ፡ ይሄዳሉ ፡ አጥተው ፡ ይመለሳሉ ፤ ከሆነስ ፡ ሆነና ፡ ያን ፡ አጥር ፡ ያን ፡ ቅጥር ፡ ያን ፡ ውሻ ፡ ያን ፡ ጋሻ ፡ ምናቡ ፡ ጉልማሳ ፡ እናትህ ፡ ትውለድ ፡ መልሳ ፡ መልሳ ፡ ብለው ፡ ይመርቁታል ።

ወኅማኒኒ ፡ ይትባረክ ።

ዓመፀኛም ፡ በሠራው ፡ ሥራ ፡ ይመረቃል ፡ ይህ ፡ ቀማኛ ፡ ነው ፡ ከፀፈቀ ፡ ዱር ፡ ከጕድጓዳ ፡ ምድር ፡ ቆይቶ ፡ ሲቀማ ፡ ይውላል ። ማታ ፡ መሰሎቹን ፡ ጠርቶ ፡ የሠባ ፡ አርዶ ፡ የጠራ ፡

አውርዶ ፡ ሲያበላ ፡ ሲያጠጣ ፡ ያመ
ሸል ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ እየሆኑ ፡ እየ
ተነሡ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ አብላ ፡ አጠጣ ፡
እንጀራ ፡ ከሌማትህ ፡ ሥጋ ፡ ከገበ
ታህ ፡ ጠጅ ፡ ከማቶትህ ፡ አይጥፋ ፡
እያሉ ፡ ሲያመሰግኑት ፡ ያመሸሉና ፡
እንዲህ ፡ አለ ። ኢሳ ፡ ፭ ፡ ፲፩ ።

ወሀከ ፡ ታዋእ ፡ ለእግዚአብሔር ።
እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ አወከው ፡ እንዳያጠፋው ፡
ያበላል ፡ ያጠጣል ፤ እንዳይምረው ፡
ይሠርቃል ፡ ይቀማል ፡ እንግዲህስ ፡
ብሎ ፡ አይተወውም ፡ ብሎ ፡ በሥ
ራው ፡ ሁሉ ፡ አወከው ፡ አንድም ፡
ወሀከ ፤ ቀሰቀሰው ፡ ቅሠፈኝ ፡ ቅመ
ፈኝ ፡ አለው ፤ ጎጢአት ፡ ሠርቶ ፡
ንስሓ ፡ አለመግባት ፡ እግዚአብሔ
ርን ፡ ቅሠፈኝ ፡ ማለት ፡ ነውና ።

፲፬ ፡ ወኢይትነሥ ፡ በከመ ፡ ብዝኃ ፡
መዓቱ ።
ጌታ ፡ እንደመዓቱ ፡ ብዛት ፡ አንድም ፡
እንደ ፡ ሰውየው ፡ ጎጢአት ፡ ብዛት ፡
አይመረመረውም ፡ ምናልባት ፡ ይመ
ለስስ ፡ እንደሆነ ፡ ብሎ ፡ እንዳይመለ
ስስ ፡ ያውቃል ፡ ብሎ ፡ ምክንያት ፡ ለ
መንሣት ፡ እገሌ ፡ እንዲህ ፡ እስካሁን ፡
ኑሮ ፡ ቢሆን ፡ ንስሓ ፡ በገባ ፡ ነበር ፡
እንዳይሉ ።

ወአልቦ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቅድሜሁ ።
እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ ፈት ፡
የለም ፡ ማለት ፡ ያይብኛል ፡ ይሰማ
ብኛል ፡ አይለውም ።

፲፭ ፡ ወርዝስ ፡ ኵሉ ፡ ዮናዊሃ ።
የዚህ ፡ ሰው ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡ ርኩስ ፡
ነው ፡ ማለት ፡ አይቀበለውም ፡ አን
ድም ፡ የጎጢአት ፡ ሥራው ፡ ሁሉ ፡
ርኩስ ፡ የተጠላ ፡ ነው ።

ወንሡት ፡ ሀነኔከ ፡ በቅድሜሁ ።
አንዱን ፡ ይዘ ፡ ይሄዳል ፡ ሕግህ ፡ በ
ዚህ ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፡ የፈረሰ ፡ ነው ፡
ማለት ፡ አይጠብቀውም ።
ወይቀንየሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ አላዕሉቱ ።
እስካሁን ፡ በሽፍትነት ፡ ያደረገውን ፡
ሲናገር ፡ መጥቶ ፡ ነበር ፡ እንግዳ ህ ፡
ወዲህ ፡ ተሾሞ ፡ የሚያደርገውን ፡ ያመ
ጣል ፡ እንዲህ ፡ ያለው ፡ ሰው ፡ ጠላቶ
ቹን ፡ አስጨንቆ ፡ ይገዛቸዋል ፤ ምነው ፡
ተጥዶ ፡ አይፈላ ፡ ተሹሞ ፡ አይበላን ፡
አለ ፡ ቢሉ ፡ በቂም ፡ በበቀል ፡ ይገ
ዛቸዋል ፤ ኢትሰአል ፡ በጎበ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ መንግሥተ ፡ ወኢትሰአ
ል ፡ በጎበ ፡ ንጉሥ ፡ መንበረ ፡ ክብር ፡
ወኢትፍቅድ ፡ ከሢነ ፡ መኰንን ፡ የ ፡ ጊ ፡
ኢትክል ፡ ተበቅሎዶ ፡ ለዘአበሰ ፡ እ
ንዲል ። ሲራ ፡ ፯ ፡ ፬ ፡ ፮ ።

፲፮ ፤ ወይብል ፡ በልቡ ፡ ወኢይትሀወክ ፡ ለት
ውልደ ፡ ትውልድ ፡ ወኢይረክበኒ ፡ እኩይ
አረተው ፡ እግዚአብሔር ፡ ያጠፋህ
ል ፡ ቢሉት ፡ በልቡ ፡ አስቦ ፡ በቃሉ ፡
ምንም ፡ ምን ፡ መከራ ፡ የለብኝም ፡
በልጅ ፡ ልጅ ፡ በልተህ ፡ ጠጥተህ ፡
ና ፡ ብሎኛል ፡ ይላል ።

ጽኂ ፣ ምሉዕ፡አፉሁ፡መርገመ፡ወጽልሑተ

አንደበቱ ፣ ክዳት ፣ ሸንገላን ፣ መርገ
ምን ፣ የተመላ ፣ ነው ።

ታሕተ፡ልሳኑ፡ዓማ፡ወሕማም፡ሮሚ፡ቮ፡፲፬

ታሕተ ፣ መንጸፍ ፣ እንዲል ፣ በንደበ
ቱ ፣ ሰውን ፣ እግዚአብሔርን ፣ መር
ገም ፣ አለ ። አንድም ፣ አንደበቱ ፣ ሰ
ውን ፣ እግዚአብሔርን ፣ መርገምን ፣
የተመላ ፣ ነው ።

ጽጅ ፣ ይጸንሕ ፡ ወይገዐ ፡ ምስለ፡ብዑላን

እስካሁን ፣ ተሹሞ ፣ የሚያደርገውን ፣
ሲናገር ፣ መጥቶ ፣ ነበር ፣ እንግዲህ ፣
ተሽሮ ፣ የሚያደርገውን ፣ ያመጣል ፣
ይሸምቃል ፣ ከባለጠጎች ፣ ጋራ ፣ ደጅ ፣
ይጠናል፡ወደቤቱ፡ልሒድ፡አይልም።

ከመ ፣ ይቅትሎ ፣ ለንጹሕ ፣ በጽሚት ።

ድኃውን ፣ ይጐዳው ፣ ዘንድ ፣ ንጹሕ ፣
አለው ፣ ድኃውን ፣ ሳይጣላው ፣ ይጣ
ላዋልና ፣ ብላዕ ፣ በሐፈ ፣ ገጽከ ፣ ያለ
ውን ፣ ይዘ ፣ ይኖራልና ፣ ገንዘብ ፣ የለ
ውምና ፣ ዘፍ ፣ ፫ ፣ ፲፯ ።

ወአዕይንቲሁኒ ፡ኀበ ፡ኑዳይ ፡ያስተሐይዓ

ዓይኖቹም ፣ ድኃውን ፣ ይመለከታሉ ፣
እገሌ ፣ መጣ ፣ ምን ፣ ሊናገር ፣ ይሆን ፣
ይላል ።

ጽፀ ፤ ይጸንሕ ፡ ወይትኀባእ ፡ ከመ ፡ አን
በሳ ፡ ውስተ ፡ ግብ ።

አንበሳ ፣ ከጸፈቀ ፤ ዱር ፣ ከጐድጓዳ ፣
ምድር ፤ ቆይቶ ፣ እንዲደፍጥ ፣ እሱ
ም ፡ የበለጸጋውን ፡ ቤት ፣ እንደ ፡ ዱር ፡
አድርጎ ፣ ይደፍጣል ።

ይጸንሕ ፡ ከመ ፡ ይምሥጦ ፡ ለኑዳይ ።

ነገር ፣ በመሥራት ፣ ደኻውን ፣ ይጐ
ዳው ፡ ዘንድ ፣ ይደፍጣል ።

ይመሥጦ ፡ ለኑዳይ ፡ ወይስኀቦ ።

ነገሩን ፣ ይነጥቀዋል ፣ ከነገሩ ፣ ያገባ
ዋል ፣ ማሩን ፣ ሙክቱን ፣ ይዘ ፣ ይመ
ጣል ። ርስቴም ፣ ከዚህ ፣ ግብሬም ፣
ይህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ይሰጣል ። ያ ፡ ሰው ፡
እገሌ ፡ እንዲህ ፡ ትላለህን ፡ ርስትህም ፡
ከዚህ ፡ ከዚህ ፡ ግብርህም ፡ እንዲህ ፡
እንዲህ ፡ ነው ፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ እን
ዲህ ፡ ያለ ፡ ውርርድ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡
ዳኝነት ፡ አለብህ ፡ ብሎ ፡ ለዳኛ ፡ ይ
መራል ።

ወያኀሥሮ ፡ በመሥገርቱ ። ዘፀ ፡ ጽፌ ፲፬ ።

ነገር ፡ በመሥራቱ ፡ ያዋርደዋል ፤ ወ
አውፅአ ፡ ከመ ፡ ያኀሥሮ ፡ በመስገር
ቱ ፡ እንዲል ፤ አንድም ፡ የዓሥሮ ፡
ይላል ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ ዳኛው ፡ በሰ
ንሰለቱ ፡ ያሥረዋል ፤ አንድም ፡ ያዓ
ሥሮ ፡ ይላል ፡ አጅሬ ፡ በዚህ ፡ ታሥ
ሮ ፡ ነው ፡ ገንዘብ ፡ የሚወጣው ፡ እረ ፡
የኔ ፡ አንድ ፡ አይፈታሽ ፡ ጅቦ ፡ አለ ፡
ብሎ ፡ ከድጉ ፡ ፈትቶ ፡ ሰጥቶ ፡ ያ
ሣስረዋል ። ኢሳ ፡ ጽ፱ ፡ ጽኗ ።

ፀ ፤ ይትቀጸዕ ፡ ወይወድቅ ፡ ሰብ ፡ ቀኒዖ
ለ ኑ ዳ ይ ።

አሁን ፡ ለ ፡ አይረባም ፡ ቀነዮን ፡ ሲ
ያይ ፡ የመጣ ፡ ነው ፡ አስጨንቆ ፡ አ
ስጠብቦ ፡ ባጋዘው ፡ ጊዜ ፡ ድኃው ፡
ይወድቃል ፡ ይነሣል ።

፬፩ ፤ ወይብል ፡ በልቡ ፡ ይረሥዓኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ።
በልቡ ፡ አስቦ ፡ በቃሉ ፡ ምን ፡ አደር ጋለሁ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ረሥቶኛል ፡ ላውስ ፡ ላጐንብስ ፡ እን ጂ ፡ ይላል ።

ወሜጠ ፡ ገጸ ፡ ከመ ፡ ኢይርአይ ፡ ለግሙራ
እኔን ፡ እንዳያይ ፡ ገጸ ፡ ምህረቱን ፡ ወደዚያ ፡ መልሶታል ፡ ይላል ። አን ድም ፡ (ይትቀጸዕ ፡ ወይወደቅ ፡ ሶበ ፡ ቀነዮ ፡ ለነዳይ) ፡ ለ ፡ ይህን ፡ ጊዜ ፡ ነው ፤ ባለጸጋው ፡ በድኃው ፡ መከራ ፡ ከአጸናበት ፡ በኋላ ፡ በሱ ፡ መከረ ፡ መጥቶበት ፡ ፈንታውን ፡ ይወድቃ ል ፡ ይነሣል ፤ (ወይብል ፡ በልቡ ፡ ይረ ሥዓኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ በልቡ ፡ አስቦ ፡ በቃሉ ፡ ለጊዜው ፡ እግዚአ ብሔር ፡ ረሥቶኛል ። (ወሜጠ ፡ ገጸ ፡ ከመ ፡ ኢይርአይ ፡ ለግሙራ) ፡ ገጸ ፡ ምሕረት ፡ ገጸ ፡ ረድኤቱን ፡ ከሌላው ወደኔ ፡ መልሶታል ፡ ይላል ፤ አንድም ለካ ፡ እግዚአብሔር ፡ አልረሳልኝ ፡ ኑሯል ፡ ገጸ ፡ ምሕረቱንም ፡ ወደዚያ ፡ መልሶታል ፡ ይላል ።

፬፪ ፤ ተንሥእ ፡ እግዚኦ ፡ አምላኪየ ፡ ወትትለዓል ፡ እዴከ ።
አቤቱ ፡ በሥራ ፡ በመፍረድ ፡ ተነሥ ተህን ፡ ሥልጣንህን ፡ ግለጸው ።

ወኢትርሥዖሙ ፡ ለነዳያን ።
ነዳያንን ፡ አትዘንጋቸው ፡ ለጊዜውም ፡ ብትዘነጋቸው ፡ እንደዘነጋሃቸው ፡ አ ያቅሩ ።

፬፫ ፤ በእንተ ፡ ምንት ፡ አምዕየ ፡ ኀጥእ ለእግዚአብሔር ።
ኀጥእ ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ በም ን ፡ አሳዘነው ፡ ብትል ፡ (ቢሉ) ።

እስመ ፡ ይብል ፡ በልቡ ፡ ኢይትኀሠሥኒ
በልቡ ፡ አስቦ ፡ በቃሉ ፡ አይመራም ረኝም ፡ ስላለ ፡ አይዶለምን ፡ አንድ ም ፡ ስላለ ፡ ነዋ ።

፬፬ ፤ ትሬኢኑ ፡ ከመ ፡ ለሊከ ፡ ትኔጽር ፡ ዓማ ፡ ወመዓተ ።
በለጸጋውን ፡ ነው ፡ በድኃው ፡ ጻማ ፡ መዓትህን ፡ አምጥተህበት ፡ ፈንታ ህን ፡ ጻማ ፡ መዓትህን ፡ እንድታይ ፡ ታ ያለህን ።

ወከመ ፡ ትሚጥዎ ፡ ውስተ ፡ እዴከ ።
በእጅህ ፡ በትረ ፡ መዓትን ፡ ለእግዚ አብሔር ፡ እንድትሰጠው ፡ ታያለህ ን ፤ እንደ ፡ ደረቅ ፡ ሴት ፡ ከባሏ ፡ የ ተጣላች ፡ እንደሆነ ፡ ወንዶ ፡ አታደ ርገውምን ፡ ግንባሬን ፡ ብላ ፡ ማማሰ ያዋን ፡ ትሰጠዋለችና ።

ላዕሌከኑ ፡ እንከ ፡ ተገድፈ ፡ ነዳይ ።
ይህ ፡ ድኃ ፡ ባንተ ፡ ፈቃድ ፡ የተፈ ጠረ ፡ መስሎሃልን ፤ ተገድፈ ፡ ማለ ት ፡ ሰው ፡ የሚፈጠር ፡ ከባት ፡ ዘር ፡ ከናት ፡ ደም ፡ ተከፍሎ ፡ ነውና ።

ወአንተኑ ፡ ረዳኢሁ ፡ ለዕጓለ ፡ ማውታ ።
የድኃውስ ፡ ረዳቱ ፡ አንተ ፡ ነህን ፡ ወ ተዓቅበ ፡ እምእሳት ፡ ወማይ ፡ እንዲ ል ፡ የበላችው ፡ እንዳይጫነው ፡ የጠ

ጣችው ፡ እንዳያነዝዘው ፡ የምትጠብቀው ፡ አንተ ፡ ነህን ።

አንድም ፡ (ትሬኢኑ ፡ ከመ ፡ ለሊሁ ፡ ይኔጽር ፡ ጸማ ፡ ወመዓተ)፡ ጌታን ፡ ነው ፡ እንደ ፡ ጌትነትህ ፡ እንደ ፡ ፈታሒነትህ ፡ ድኃውን ፡ ለባለጸጋ ፡ አሳልፈህ ፡ ሰጥተኸው ፡ ጸማ ፡ መዓትን ፡ እንዲያይ ፡ ታያለህን ፡ (ወከመ ፡ ትሜጥዎ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ)፡ እንደተሸጠ ፡ ባሪያ ፡ ለባለጸጋው ፡ አሳልፈህ ፡ እንደሰጠኸው ፡ ታያለህን ፡(ላዕሌከኑ ፡ እንከ ፡ ተገድፈ ፡ ነዳይ) ፡ እምኔከኑ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ እኔስ ፡ በባለጸጋው ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡ መስሎኝ ፡ ነበር ፤ ካንተም ፡ ዘንድ ፡ ተለይቷልን ፡(ወአንተኑ ፡ ረዳኢሁ ፡ ለእጓለ ፡ ማውታ)፡ የባለ ፡ ጸጋውስ ፤ ረዳት ፡ አንተ ፡ ነህን ፡ በጥንተ ፡ ግብሩ ፡ ዕጓለ ፡ ማውታ ፡ አለው ፡ ሲወለድ ፡ ያንገት ፡ ፈትል ፡ ድርጎ ፡ እህል ፡ ይዞ ፡ አልተወለደምና ፡ ዕራቁየ ፡ ወፃዕኩ ፡ እምከርሠ ፡ እምየ ፡ ወዕራቁየ ፡ እገብእ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ እንዲል ። ኢዮ ፡ ፩ ፡ ፳፩ ።

ፀሊኤ ፡ ቅጥቅጥ ፡ መዝራዕቶ ፡ ለኃጥአ ፡ ወለአኩይ ።

እኔስ ፡ የድኃው ፡ ረዳት ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ የባለጸጋውን ፡ ረዳት ፡ አይደለሁም ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡ የባለጸጋውን ፡ ሥልጣን ፡ አጥፋ ።

ወትትኃሠሥ ፡ ኃጢአቱ ፡ በእንተ ፡ ወኢትትረከብ ።

ድኃውን ፡ ስለበደለ ፡ የባለጸጋው ፡ ኃጢአት ፡ ትመረመራለች ፡ ትትረከብ ፡ በዝታ ፡ ተርፋ ፡ ትገኛለች ፡ (ኢትትረከብ)ከቊጥር ፡ በዝታ ፡ ተርፋ ፡ ልኳ ፡ አይታወቅም ። አንድም ፡ ድኃውን ፡ ስለበደለ ፡ የባለጸጋው ፡ ኀጢአት ፡ ትመረመራለች ፤ ኢትትረከብ ፡ እሱን ፡ ከተፈተለ ፡ ገመድ ፡ ከተተከለ ፡ ግንድ ፡ ከተቈፈረ ፡ ጉድጓድ ፡ አድርሰው ፡ አትገኝም ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ወፎ ፡ ተዋሺኝ ፡ እንዲሉ ፤ አንድም ፡ ባለጸጋውን ፡ በደለ ፡ ስለማለት ፡ የድኃው ፡ ኀጢአት ፡ ትመረመራለች ፡ ኢትትረከብ ፡ አትገኝም ፡ ድኅ ፡ ይበደላል ፡ እንጂ ፡ አይበድልምና ፤ ትትረከብ ፡ ጥቂት ፡ ትገኛለች ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡ የማይበድል ፡ እንጨት ፡ ሁኖ ፡ የማይጤስ ፡ የለምና ፡ ባይበድልም ፡ እንዲያውስ ፡ አቶ ፡ እገሌን ፡ ከሰው ፡ ፊት ፡ ታቆመውን ፡ አውስ ፡ አጎንብስ ፡ ይሉታልና ፡ አንድም ፡ ወትትኃሠሥ ፡ ኃጢአቶ ፡ ይላል ፤ የባለጸጋውን ፡ ኃጢአት ፡ ትመረምራለህ ፡ ትትረከብ ፤ በምልዓት ፡ ትኖራለህ ፡ ትፈርዳለህ ፤ኢትትረከብ ፡ በፍዳው ፡ እለፍ ፡ የሚልህ ፡ የለም ።

ወኢኃ ፡ ይነግሥ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለዓለመ ዓለም ። ዘፀ ፡ ፲፭ ፡ ፲፰ ።

እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ ይነግሣል ፡ ማለት ፡ የመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ሲሠራ ፡ ይኖራል ።

ወይትነሥኡ ፡ አሕዛብ ፡ እምድር ።

አሕዛብ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ አንድም ፡ ከሰው ፡ ተለይተው ፡ ይጠፋሉ ።

ፀ፯ ፤ ፍትወቶሙ ፡ ለነዳያን ፡ ሰምዐ ፡ እግዚአብሔር ።
ነዳያን ፡ ወድደው ፡ የለመኑትን ፡ ል መናቸውን ፡ ሰምቷልና ።
ወኅሊና ፡ ልቦሙኒ ፡ አጽምዓት ፡ ዕዝኑ ።
አስበው ፡ የለመኑትን ፡ ልመናቸው ን ፡ እዝነ ፡ ፈቃዱ ፡ ሰምታለችና ።
ፀ፯ ፤ ፍትሑ ፡ ለነዳይ ፡ ወለዕጓለ ፡ ማውታ
አባት ፡ እናት ፡ ለሞቱበት ፡ ለድኃ ፡ ፍረዱ ፡ አሁን ፡ አድልታችሁ ፡ ፍረ ዱ ፡ ማለት ፡ አይደለም ፡ እውነት ፡ ፈረዳችሁ ፡ ቢረታ ፡ ዳኝነት ፡ ቢረታ ፡ ማማለጃ ፡ አትቀበሉ ፡ ሲል ፡ ነው ።
አንድም ፡ ድኃ ፡ በደሉን ፡ ለእግዚአ ብሔር ፡ መንገሩ ፡ ፍርዱ ፡ ነው ።
ለእግዚአብሔር ክልነገረ ፡ ለማን ፡ ይን ገር ። ዘፀ ፡ ፳፫ ፡ ፩ ፡ ፫ ።
ከመ ፡ ኢይደግሙ ፡ እንከ ፡ ዕጓለ ፡ እመሕያው አዕብዮ ፡ አፉሆሙ ፡ በዲበ ፡ ምድር ።
አጥፊን ፡ ዘርግተን ፡ መልሰን ፡ ቀል ሰን ፡ እንናገራለን ፡ ማለትን ፡ እንዳይ ደግሙ ፡ አንድም ፤ አልዕሎ ፡ ቃሎ ሙ ፤ ገንታ ፡ ብለን ፡ እንናገራለን ፡ ማለ ትን ፡ እንዳይደግሙ ።

መዝሙር ፡ ፲፩ ።

፩ ፤ በእግዚአብሔር ፡ ተወከልኩ ፡ እፎ ፡ ትብልዋ ፡ ለነፍስየ ።
በሳኦል ፡ ጊዜ ፡ ስለራሱ ፡ ተናግሮታ ል ። ሲሞን ፡ ኢያሶን ፡ የሚባሉ ፤ መ ስተዋድያን ፡ ነገር ፡ ነበሩ ፤ ሳኦል ፡ በ መንግሥት ፡ ያለ ፡ ነውና ፡ ለጊዜው ፡ ይሾመናል ፡ ይሽልመናል ፡ ብለው ፡ ዳዊት ፡ ከዚህ ፡ ውሏል ፡ ከዚህ ፡ አድ ሯል ፡ አገኘኸውም ፡ ዛሬ ፡ አጣኸውም ፡ ዛሬ ፡ ነው ፡ እያለ ዓነግታሩል ፤ ዳዊ ትም ፡ እንደ ፡ ተቀባ ፡ ያውቃሉና ፡ ኋላ ፡ ይሾመናል ፡ ይሽልመናል ፡ ብለ ው ፡ ዛሬ ፡ ሳኦል ፡ ሊይዝህ ፡ ይመጣ ል ፡ ከሚሠውርህ ፡ ዱር ፡ ከሚያጠል ቅህ ፡ ባሕር ፡ ግባ ፤ ካደርህበት ፡ አት ዋል ፡ ከዋልህበት ፡ አትደር ፡ እያሉ ፡ ይነግሩታል ። ፩ ፡ነገ ፡ ፳፫ ፡ ፲፱ ።
ሲሞን ፡ ኢያሶን ፡ በእግዚአብሔር ፡ አምኖለሁ ፡ ሰውነቴን ፡ ምን ፡ በይ ፡ ትሏታላችሁ ።
አዓይል ፡ ውስተ ፡ አድባር ፡ ከመ ፡ ያፍ።
ወፍ ፡ ካንዱ ፡ ተራራ ፡ ወዳንዱ ፡ ተራ እንዲዞር ፡ እኔም ፡ ከሀገሬ ፡ ወጥቼ ፡ ከዘመዴ ፡ ተለይቼ ፡ በረሀ ፡ ለበረሀ ፡ እንከራተታለሁ ፡ ሰውነቴን ፡ ምን ፡ በይ ፡ ትሏታላችሁ ። አንድም ፡ የሲዲ ፡ ጳውሎስ ፡ ትርጓሜ ፡ ብሎ ፡ እኽያዬ ን ፡ አስራለሁ ፡ አቦንም ፡ አምናለሁ ፡ እንዲሉ ። እኔ ፡ አም ናለሁ ፡ ሰውነቴን ፡ ምን ፡ በይ ፡ ትሏ ታላችሁ ፡ (ሲሊኑ) ፡ እንደ ፡ ወፍ ፡ ብር ፡ ብለሽ ፡ ጥፊ ፡ ትሏታላችሁን ።
፪ ፤ እስመ ፡ ናሁ ፡ ኃጥኣን ፡ ወሰቁ ፡ ቀ ስ ቶ ሙ ።
ሲሞን ፡ ኢያሶን ፡ ቀስት ፡ ምክራቸ ውን ፡ ቀፍረዋልና ።

ወአስተዳለዉ ፡ አሕፃቲሆሙ ፡ ውስተ ፡ ምጕንጻቲሆሙ ። ኢሳ ፡ ፲፫ ፡ ፲፮ ።

በጕራንጕሬ ፡ ልባቸው ፡ ቀስት ፡ ምክራቸውን ፡ አዘጋጅተዋልና ።

ከመ ፡ ይንድፍዎሙ ፡ ለርቱዓን ፡ ልብ ፡ በጽሚት ።

ቅን ፡ ልቡና ፡ ያላቸው ፡ የዳዊትን ፡ ወገኖች ፡ በምክራቸው ፡ ይጐዷቸው ፡ ዘንድ ፡ ይንድፍዎ ፡ ይላል ፡ ቅን ፡ ልቡና ፡ ያለው ፡ ዳዊትን ፡ ይጐዱት ፡ ዘንድ ፤ አንድም ፡ እስመ ፡ ናሁ ፡ ኃጥኣን ፡ ወሰቁ ፡ ቀስቶሙ ፡ እለ ፡ ሳአል ፡ በቁሙ ፡ ቀስታቸውን ፡ ቀፍረዋልና ። (ወአስተዳለው ፡ አሕፃቲሆሙ ፡ ውስተ ፡ ምጕንጻቲሆሙ) ፡ ፍላጻቸውንም ፡ በሸፋፍ ፡ ሸፍነዋልና ፤ (ከመ ፡ ይንድፍምሙ ፡ ለርቱዓን ፡ ልብ ፡ በጽሚት) ፡ የዳዊትን ፡ ወገኖች ፡ ይገድሏቸው ፡ ዘንድ ፡ ይንድፍዎ ፡ ይላል ፡ ዳዊትን ፡ ይገድሉት ፡ ዘንድ ።

፫ ፤ እስመ ፡ ናሁ ፡ ዘአንተ ፡ ሠራዕከ ፡ እሙንቱ ፡ ነሠቱ ።

ጻድቁ ፡ ኢትቅትል ፡ ያልከውን ፡ አፍርሰዋልና ።

ወጻድቅሰ ፡ ምንተ ፡ ገብረ ።

ጻድቅ ፡ ዳዊትማ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ይህስ ፡ አይደለም ፡ አስቀድመው ፡ ያልጠበቁትን ፡ በሱ ፡ ጊዜ ፡ ይጠብቁታልን ፡ ብሎ ፡ (እስመ ፡ ናሁ ፡ ዘአንተ ፡ ሠራዕከ ፡ እሙንቱ ፡ ነሠቱ) ፡ አፍቅሩ ፡ ጸላእትክሙ ፡ ያልከውን ፡ አፍርሰዋልና ፤ (ወጻድቅሰ ፡ ምንተ ፡ ገብረ) ፡ ጻድቅ ፡ ዳዊትማ ፡ ምን ፡ አደረገ ፡ ማለት ፡ ጠላትን ፡ ሊሹት ፡ የተገ

ባ ፡ ነው ፡ እኔ ፡ ዳዊትማ ፡ ወዳጃቸው ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ ጠላታቸው ፡ ነኝን ፡ አንድም ፡ (እስመ ፡ ናሁ) ፡ አፍቅር ፡ ቢፀከ) ፡ ያለውን ፡ አፍርሰዋልና ፡ ወጻድቅሰ ፡ እንዳለፈው ።

፬ ፤ እግዚአብሔር ፡ ውስተ ፡ ጽርሐ ፡ መቅደሱ ።

ወሰቁ ፡ አስተዳለዉ ፡ ብለህስ ፡ ነገር ከኝ ፤ ጌታ ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ ምን ፡ አለ ፡ ዝም ፡ አለን ፡ ትለኝ ፡ እንደሆን ። እግዚአብሔርስ ፡ በሰማያዊት ፡ መቅደሱ ፡ አለ ።

እግዚአብሔር ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፡ መንበሩ ፡ በሰማያዊት ፡ መንበሩ ፡ አለ ፡ ማለት ፡ ይፈርዳል ፡ ዝም ፡ አይልም ።

ወአዕይንቲሁኒ ፡ ኀበ ፡ ነዳይ ፡ ይኔጽራ ።

ዓይኖቹም ፡ ዳዊትን ፡ አንድም ፡ ማናቸውንም ፡ ድኃ ፡ ይመለከታሉ ።

ወቀራንብቲሁኒ ፡ የሐቶ ፡ ለዕጓለ ፡ እመሕያው ።

ዓይኖቹም ፡ ሰውን ፡ ይመረምራሉ ። በቀራንብት ፡ መላው ፡ በሕርዩ ፡ ማወቁን ፡ መናገር ፡ ነው ። አንድም ፡ (ወቀራንብቲሁኒ ፡ ለእጓለ ፡ እመሕያው) ፡ ነው ፡ ሰው ፡ በይን ፡ ጥቅሽ ፡ በከንፈር ፡ ንክሽ ፡ የሚሠራውን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቃል ።

፭ ፤ እግዚአብሔር ፡ የሐትዖ ፡ ለጻድቅ ፡ ወለኃጥእ ።

የሐቶም ፡ ይላል ። እግዚአብሔር ፡ ጻድቅ ፡ ዳዊትን ፡ ኀጥእ ፡ ሳአልን ፡ ይመረምራል ። አንድም ፡ ጻድቁን ፡ ኃጥኡን ፡ ይመረምራል ፤ መርምሮ ፡ ለጻድቁ ፡ ዋጋውን ፡ ይሰጠዋል ፤ በኃጥኡ ፡ ፍዳ ፡ ያመጣበታል ።

ዘሰ ፡ አፍቀራ ፡ ለዓመፃ ፡ ጸልዐ ፡ ነፍሶ ።
ኢሳ ፡ ፭ ፡ ፲፰ ።
ዓመፅን ፣ የወደደ ፡ ሳኦል ፡ ሰውነቱ
ን ፡ ጠላ ፡ በል ።

ኄ ፡ ይዘንም ፡ ወሣግር ፡ ላፅለ ፡ ኃጥአን ።
መሣግር ፡ ካለ ፡ ይዘንማ ፡ ይዘንም ፣
ካለ ፡ መሥገርት ፡ ቢል ፡ በቀና ፡ ነበ
ር ፡ ልማደ ፡ መጻሕፍት ፡ ነው ፡ መዓ
ቱ ፡ በነሳኦል ፡ ይዘንምባቸዋል ፡ ምነ
ው ፡ ምንዳቤያትሰ ፡ ኢኮና ፡ ርሑቃ
ተ ፡ እምኔከ ። አላ ፡ ይነቅዓ ፡ እምታ
ሕተ ፡ እግርከ ፡ ይል ፡ የለምን ፡ እ
ምሰማይ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ የመዓቱን ፡
ብዛት ፡ መናገር ፡ ነው ። አንድም ፡
ከጌታ ፡ ስለታዘዘ ፤ አንድም ፡ በቁመ ፡
ከሰማይ ፡ የሚወርድ ፡ መዓት ፡ አለ
ና ፡ እንደ ፡ ሰብአ ፡ ትካት ፡ እንደ ፡
ሰብአ ፡ ሰዶም ፡ እንደ ፡ ሰብአ ፡ ገሞራ ፡
አንድም ፡ ለአፍርሆ ፡ ለአደንግያ ፡
ሰው ፡ ጦር ፡ ተወረወረብህ ፡ መርግ ፡
መጣብህ ፡ ሲሉት ፡ ይፈራልና ፡ እን
ደ ፡ ወገርሰም ፡ እንደ ፡ ሰማርድ ፡ መ
ሬት ፡ ቆፍረው ፡ ደንጊያውን ፡ ጸፍ
ጽፈው ፡ ዕንጨቱን ፡ ረብርበው ፡ ሥ
ጋውን ፡ ከውስጥ ፡ አድርገው ፡ ይሔ
ዳሉ ፡ አውሬ ፤ ሳብ ፡ ያደረገው ፡ እን
ደሆነ ፡ በላዩ ፡ ይደፋበታልና ።

እሳት ፡ ውተይ ፡ መንፈሰ ፡ ዐውሎ ፡ መክ
ፈልተ ፡ ጽዋያሙ ።
እሳት ፣ የሰብአ ፡ ሰዶም ፡ ተይ ፡ ነገው
ን ፡ ሊጠፉ ፡ እንደ ፡ ዛሬ ፡ መላእክት ፡
ድኻ ፡ ሲነሰንሱበት ፡ ታይተዋል ። ዘፍ፡

፲፱፡፳፬። መንፈሰ ፣ ዓውሎ ፡ ጥቅመ ፡
ሰናያርን ፡ ያጠፋበት ፡ ነው ። ይህን ፡ የ
መሰለ ፡ ሁሉ ፡ በነሳኦል ፡ ተደርጎባቸ
ዋልና ፤ አንድም ፡ እሳት ፡ ቋዱ ፡ ሲቃ
ጠል ፡ ተይ ፡ ከደኃራው ፡ ሲገናኝ ፡ መ
ንፈሰ ፡ ዓውሎ ፡ አካለ ፡ ዓውሎ ፡ ሲል ፡
ነው ፣ ፍጥነቱን ፡ ሲያይ ። አንድም ፡
ነፋስ ፡ አይቶ ፡ ይተኩሰዋል ፡ መጥቶ ፡
ሲጥል ፡ በጌላቡሄ ፡ የተደረገውን ፡
መናገር ፡ ነው ። ሳሙ ፡ ፴፩ ፡ ፭-፲፫ ።

እስመ ፡ ጻድቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወጽ
ድቀ ፡ አፍቀረ ።
እግዚአብሔር ፡ ዕውነትን ፡ ይወድዳ
ልና ፣ አንድም ፡ ዕውነትን ፡ የያዘ ፡ ሰ
ውን ፡ ይወድዳልና ።

ወርትዕሰ ፡ ትሬእዮ ፡ ገጹ ።
ርትዕ ፡ ዳዊት ፣ ግን ፡ በባለሟልነት ፡
ጸንቶ ፡ ይኖራልና ። አንድም ፡ ወራ
ትዓንሰ ፡ ይሬእዩ ፡ ገጸ ። ራትዓን ፡ የዳ
ዊት ፡ ባለሟሎች ፡ ግን ፡ በባለሟልነ
ት ፡ ጸንተው ፡ ይኖራሉና ። ወአዕይ
ንቲሁኒ ፡ ጎበ ፡ ነዳይ ፡ ይኔጽራ ፡ ላለ
ው ። አንድም ፡ እስመ ፡ ጻድቅ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ወጽድቀ ፡ አፍቀረ ። እ
ግዚአብሔር ፡ ዕውነትን ፡ ይወድዳል
ና ፣ አንድም ፡ ዕውነትን ፡ የያዘ ፡ ሰው
ን ፡ ይወድዳልና ። ወርትዕሰ ፡ ትሬእ
ዮ ፡ ገጸ ። ርትዕ ፡ ዳዊት ፡ በባለሟል
ነት ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ። አንድም ፡ ወ
ራትዓን ፡ ይሬእዩ ፡ ገጸ ። ራትዓን ፡ የ
ዳዊት ፡ ወገኖች ፡ በባለሟልነት ፡ ጸን
ተው ፡ ይኖራሉ ።

« ስብሐት ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለዓለም ፡ መስዓልመ
ዓለም ። » ኣሜን ።